ቦታዎች

ምስጢር

P.② ከ 101-201



t.me/BooksandYou

. . . . አምባ ጊዮርጊስ ሲያርሱ ከመንደሩ ጻርቻ ላይ አንድ ትልቅ ፣ ሁለት ትናንሽ የግር ቤቶች ወደ አሱበት አንድ አጥር ግቢ አመሩ ። አስቀድመው የወሰኑ ወይም የተሰናዳበት ይመስል ፣ ታንጉትን ከአንደ ኛው አነስተኛ ጉጀ አስገቡዋት ። ወይዘሮ ደብሬ ወደ ትልቁ ቤት ሔደው ከጥቂት ጊዜ በኋላ የገብስ ቆሌና ኮረዲ ጠላ ራሳቸው ይዘው ተመለሱ ። '' እንግዲህ ከዚሁ ቆይ ፣ ማንም አያስቸግርሽ ፤ እኔ ቤተ ክርስቲያን ተሳልሜ ልምጣ ! '' በማለት ብቻዋን ተዋት ። ጊዜው አልጎሎ ብዓት ጣሪና ግድግዳ ስትቀባር ፣ የኩታዋን ሚኙ እየተረተረች እንደገና መልሳ በትጂው ቆየች ። ውሎ መሰላት ። እንደዚሁ ከመጠበቅ በስተቀር የፍርሃትም ይሁን የጮጮት አንጻችም የለየለት ሐሳብ አይሰማትም ነበር ። ወደ ግታ ገደግ ወይዘሮ ደብሬ እንደገና ሲመጡ ፣ እንጀራ በክክ ውኖና አረቄ ይዘው ነበር ። 'አይዞሽ ' አሏት ያመጡትን እያቀረቡ ። '' ኮረፈው ብቻ ሆድሽን ይነፋዋል ፣ አረቄውን ጠጭበት ፣ ደሞም ፍርሃት ሽን ያጠፋልሻል ፣ '' ሲሙሽ ' በይ እንግዲህ ፀረፍ በይ '' አሉና በጨለማው ውስጥ ብቻዋን ተለዋት ሔዱ ። አሁን ልብዋ ከፉኛ ይመታ ጀመር ። ካለ ዐመልዋ አረቄውን እንድ ሦስት መለኪያ ስትጠጣ ለት ሞቅታ ተሰማት ። ' ምናለበት ! ' ስትል ራሷን አደፋፈረች ። ከት ልቁ ቤት ጠበል ጠዲት መኖሩን የሚያበሥረው የሰዉ ውካታ እየቀነሰ ሔዶ ጨርሶ ሲጠፋ ታንጉት መቀነቷን ፈታችና ከጠናር እልጋው ላይ ተጋደመች ። መጀመሪያ የሰው ድምፅ በሩቁ ሰማች ። ጆሮዋን እንቅታ ስታዳምጥ ጫነ ፣ ጫነ የሚለው ኮቲ እየቀረበ መጣ ። ገርበብ ብሎ የነበረው በራፍ ሲከፈት በውጭው ደብዛዛ የከዋክብት ውጋጋን የሰውዬው ቅርጽ ዋላ መሰሎ ታያት ። ትንፋሽዋን ያዝ አደረገችው ። ልብዋ ደረትዋን ተርትር የሚወጣ መስሏት ነበር ። ከአልጋው ጠርዝ ተቀምጦ ልብሱን ሲያወላልቅ ፣ ' ምነው ዛሬ ይሀንን አረቄ ዝም ብላ ጋተችኝ እባካችሁ ! ' አለ ሰውዬው ከራሱ ጋር ፣ መጠጥ ትንሽ ባሰረው እንደበት ። ከአልጋው ላይ ወጥቶ ሲጋደም ነበር ሌላ ሰው መኖሩን ያወቀው ። 'እህ !' አለ በመገረምም በመደንገጥም ። ታንጉት እንቅልፍ የወሰዳት መስላ ዝም አለች ። ለማረጋገጥ በእጁ ዳበስ ዳበስ አድርጎ ቁንጣላዋን ሲነካ እንደ ገና 'እህ' አለ ። ' ተነሥቶ ይሔድ ይሆን ! ' የሚል ሐሳብ መጣባት ። ግን አልሔደም ። የጋለ ሰውነቱ ተጠጋት ፣ በእንቅልፍ ይብ ዐይኑት አስተኛ ገደችው ፣ ዶሮ ሲጮህ አቅራቢያም ሁለተኛ ጊዜ እንደዚሁ ። ታንጉት ባትደሰትበትም እንደ ፈራችው አላስፈራትም ፣ አልቀፈፋትም ፣ የሰው ዐይን ለማየት የፈራ ይመስል ገና ወፍ መንጫጫት ስጀምር ተነሥቶ ሔደ ። ቀይ ይሁን ጥቁር አላየችውም ፣ እሱም እላያትም ፣ ከረፋዱ ላይ ወደ ጉንደር ተመለሱ .....

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ፣ '' እግማ ደብሬ መሆኑ ነው መሰለኝ! '' አለቻቸው ፣ የደስታ ፈገግታ እያሳየች ።

'' እሰየው ! እሰየው ! ስለቴን አስገባልኝ ! '' አሉ ወይዘሮ ደብሬ ፣ እንደ ልጅ መፈንደቅ ታሳቸው ።

'' ይኸው አራት ቀን ዐለፈኝ እንግዲህ ። ለገብርዬ ልንገረው ! '' ስትል በጥርሣሬ መልክ ጠየቀች ።

'' ትንሽ ቆይ ፣ ያያርስሻል ! ''

''ግን እንዲያው እንዳችም ፍንጭ አይወጣም ብለው ነውን ''

'' በምን መንገድ ። እኔን እንጂ አንቺን አላየሽ ! ግን መሆንሽን ወያቅ ! ይፍርም አይናገረው እንጂ ! '' በዋያቱ አስተያየት ተመለ ከተቻቸው ። ''ጸያቄን ነበራ !''

'' ምን ! '' ታንጉት በመብረቅ እንደ ተመታ ክው አለች ።

'' እይዞሽ አትደንግጭ ! ማፍረሱም የማይቀር ነበር ። '' ታሪኩን ነገሩዋት ። '' ምስት ልጆች የወለደችለት ሚስቱ ከሞተች ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው ። እንቱ ሌላ ሚሽት እንዲያገባ ትፈልጋለች ። በዚህ ዕድ ሜው ምን በወጣው ! አያቀስስ ! አይመነኩስ ባይ ናት ።''

'' ግን እንቲቱን ምን ብለው አማከሯት ! ''

''ወንድ የማያስወጋ ዐይነ ጥላ ያስቸገራት አንዲት እኅቱ ነበረች ፣ ወቲ ብንወይት ምሽቱ የሞተችበት ካህን ይገፍላታል አለን አልኳታ፣ ወቅርውንም የወንድሟ ነገር ሲከነክናት ቆይቶ ኖር ይስታውንም አል ቻለችው ። ''

''እንዲት መሣልዎ እንደዚህ ያለው መላ እቴ ! '' በመገረም ራስ ኖን እያወዛወዘች .....

በዚያው ሰሞን ግን ፣ ጋረድና አክሊሉ የተጨዋወቱት ስለ አምባ ጊዮርጊሱ ምሥጢር ነበር ።

ከጋረድ ቤት ጠጅ እየኮመኮሙ በመጠጥ ኃይል ተከራርቶ ፣ '' ራስ ታልኩት መቸ እነሰውና '' እያለ ከአገው ንጉሤ ጋር ስለሚያደርጉት ሰምንት ፣ ስለ ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር ላይ መከተም ሲያወጉ ነገሩን በመሻል ያነሣው አክሊሉ ነበር ።

'' ኧረ እንዲያው አንድ ነገር ሰምቸ ! '' አለ አክሊሉ መገረሙን ለግለጽ ወይኑን ጨንቄር አድርጎ ።

'' ምን ! ''

'' የአምባ ጊዮርጊሱን አለታ መንከር ታውቃቸዋለህ ?'' ጋረድ በአለታ ራሱን ነቀነቀ ። ''ወዳጄ ናቸው ። ዛሬያ በቀደምለታ በጨዋታ

ጨዋታ እንድ የሚያስደንቅ ወሬ ነገሩኝ ። ሚሽቱ የሞተችበት እንድ ካህን ነበር ፣ በጣም የሚያቀርቡት ። እንዲያውም እሳቸው ትልቅ ገዳም የተሾሙ እንደሆነ አለቅነቱን ይይዛል ብለው ያመኑበት ። ዛሬያ የጊ ዮርጊስ ግማሥት ድንገት አፈረሰኩ አይላቸው መሰለህ ! ”

“ሲሸንፍ መቸስ ምን ያድርግ ? ” አለ ጋረድ ።

“ መሸነፉስ ይሸንፍ ። ላያስበው እኮ እንዲት ቤት አሳተችኝ ነው የሚለው ። የሚገርመው ደግሞ ቤትየዋን አያውታትም ።”

“ ታላወቃት እንዴት ?” ጋረድ ጥያቄውን እንጠልጥሎ ተወው ።

“ጠበል ጠዲቅ ሲል መሽቶበት ተእጎቱ ቤት አድሮ ታልጋ ላይ እገኝሁዋት ነው የሚለው ! ”

“ በዕንጨት ለቀማ ፣ በልብስ አጠባ ፣ በውሃ ቅዳት ጊዜ ዐልፎ ዐልፎ የሚያስትም ያጋጥማል ” አለ ጋረድ ነገሩን በማታለል መልክ ።

“ዛዲያ ተመንደሩ ማን እንዳደረ ታውታለህ ? ” ሲል አክሊሉ ጉጉት በሚቀሰቅስ አነጋገር ጠየቀውና መልሱን ወዲያው ሰጠው ።

“ ወይዘሮ ደብሬ ! ”

“ ኧረ ! በዚህ ዕድሜያቸው ! ” ጋረድ የግራሜ ሣቅ መጣበት ።

“ እሳቸውማ እይደሉም ። ሌላ ነው ነገሩ ። እሳቸውን ጥቂት ጥቂት ያውታቸዋል ። በዚህ ላይ ቤትየዋ ቁንዳላ መሆንዋን ዐውቋል ። ገምት እስቲ ! ” ሲል አክሊሉ ጠበቀው ።

ጋረድ ጥቂት እንደ ማሰብ አደረገ ። “ ታንጉት ናት እንዳትለኝ !”

“ ሌላ ማን ሊሆን ይችላል ? ሁለቱ እንደሆነ አይለያዩ ። መቁረ ቡንስ የጠላችው ዐመሏን ስለምታውቅ ሳይሆን ይቀራል ?”

“ እንከፍ ! ” ጋረድ ገብርዬን በሌለበት ሰደበው ። “ ይህንን ጉድ እናውጣና እናፋጃቸው ! እሱ እንደሆነ እንዳስብነው ተወጥመዳችን እል ገባልን ። እውነትም እንከፍ ! ”

“ ቆይ እንደሱም እይደለ ! አትቸኩል ልጅ ጋረድ ። ነገርን እስኖ ነው ። እነሱ ቢጣሉ እኛን ምን ይጠቅመናል አሁን ! ”

“ አላድጊያታለሁ ፣ ልጂ ማለት ናት ይል የለ ! ቴዎድሮስና ገ ርዱም በዚሁ ምህኖት ይቀያየማሏ !”

“ እይመስለኝም ። ጥፋቱ የሷ ተሆነ ቴዎድሮስ ለገብርዬ ነው የሚ ያደላው ። ትክክለኛ ፍርድ እያለ የሚመጻደቅበት ነገር አለ እደለ !”

“ እና ፣ ዝም እንበል ነው የምትለው ?”

“ ለጊዜው ! ለጊዜው ! ይህንን ጉድ የምንጠቀምበት መንገድ እስትናገኝ በምሥጢር እናቆየዋለን ። ”

—5—

ታንጉት ፣ እርግጠኛ ከሆነች በኋላ እንድ ቀን የምሥራቹን ለገብርዬ ስትነግረው ፣ “እሁን ለሱ ቸርነት ምን ዋጋ ይከፈለዋል !” እያለ ዐሥር ጊዜ ከማመስገን በቀር ደስታውን የሚገልጥበት ሌላ ቋንቋ አጣ ። ደብረ ታቦር ሔዶ ለቴዎድሮስ እስኪነግራቸው ድረስም ተቻኮለ ። ከእርሱ ያላ ነስ ደስ እንደሚላቸው ይሰማዋል ። ነገር ግን ፣ ታንጉት ጪት ጪት እያ ሞለመለ ያስታውካት ስለ ጀመረ ፣ ወይዘሮ ደብሬ ብዙ ጊዜ ባይለዩ ቀትም በእንደዚህ ያለ ወቅት ከባለቤት የሚቀርብ አይገኝም ና ትቷት ከመሔዱ ይልቅ ፣ ሲባል እንደ ሰማው ቪሉ እስኪረጋ መቆየቱ የተሻለ መስሎ ታየው ። የጪት ሕመምዋ እያደረ ቀለል ሲልላት ደግሞ ታንጉት እዲስ ሁናቴ ተፈጠረባት ።

ምናልባት በማሕፀንዋ ያለው ፅንስ የራስዋን የልጅነት ዘመን ስላስታወሳት ይሁን ፣ ወይም ደግሞ እርግዝናዋን በወጸደ ነፍስ ለሚገኙት እናትዋ ለማሳየት እንዳች ሥውር ፍላጐት አድሮባት ፣ ብዙ ጊዜ ሐሳብዋና ትዝታዋ ዐፈር ፈጭታ ውሃ ተራጭታ ወደ አደገችበት ትውልድ ሀገ ርዋ ጭልጥ ብሎ ይሔድባታል። በዚህ ጊዜ ፈጽሞ ያላሰበችው እምሮት ይይ ዛታል ። “ ወቸው ጉድ ” ትላለች በመገረም ከራስዋ ጋር ። ይህ አዲስ እምሮት እየበረታባት ሲሔድ ለወይዘሮ ደብሬ አማከረቻቸው ።

“ ዛዲያ ችግሩ ምንድን ነው ? ” አሏት ።

“ እህ ! ገብርዬ እሺ አይል እንደሆነ ብዬ ነዋ ! ”

“ እህ ! ሁለት ወዶ አይሆንም ።”

ይሥቅብኛል አያለች ስታቅማማ ሰንብታ ፣ “ ምነው ሆድሽ አላ ደነም ልጂ ! ” ብሎ አንድ ቀን ሲዳብሳት ነበር ደፍራ የጠየቀችው ። የውስዋ ጉጉቷ ከፊቷ ላይ ይነበባል ። “ አንድ ነገር እያማረ አስቸግ ሮኛል ፣ እሺ ትለኛለህ ? ” አለችና ጠየቀችው ።

“ እምቢ እንዳልልሽ ነው ዛዲያ ! ወገኛ ነሽ ! ”

“ አገሩ ሩቅ ቢሆንስ !”

“ ተቅርብ ተለለ ! እኔ ምንተዳዬ ! ”

“ ዋልካ አማረኝ ! ” አለች ታንጉት የመጨነቅ ሣቅ እየመጣባት ።

“ ዋልካ ! ዋልካ ዛዲያ ጉራንባ ወረድ ሲል ምን የመሳሰለ ጥቁር ዋልካ ተርፎ የለ ! ብቻ ልጂን ጥቁር እንዳታረጊው እንጂ ! ”

“ እኔን ያማረኝ ደሞ የወይኒ ዋልካ ነው ። ልጅ ሆኝ የነበርኩበት ተወደኒ ወንዝ ዳር እንድ ዝርግብ አለ ፣ ልጆች ሆነን የምንጫወት

በት ። ዛሪያ ሲርበንም ይውን እያማመን የዘሀን ገረንም ብ ዋልካ እን በላዋለን ፣ እንጻንድ ቀን ሆኖችን እስቲሩ ድረስ ። ተዘያ በኃላግ እ እያሱ ግግጥ ነዋ ! ድርቅ ብሎ ነው የሚወጣው ። እና ምን ቸገርን ! ነገም እገበላዋለን ። እውንም ባይኔ ላይ የሚንከራተተው የዘያ ዋልካ እምርት ነው ። ”

“ ሌላ ዋልካ ቢሆን እምርትሽን ?... ” ጥያቄውን እንዲጨ እንደሚ ጨርሰው ንብርቡ ጠሩበት ።

“ረጉም ! ለዘያ - ለዘያማ እንተን ተግስቸገር ብቡ በዘያው ሰሞነ እንገረብ ወደ ታች በኩል ዋልካ ታለበት ሌደን ቀምኜ ነበር ። ሊያስ ታውስኝ ደረስ ።”

“ሌላው ታልሆነማ መቸስ እንሌለና !” የንብርቡ እነጋገር ትንገ የቅሬታ ታና ነበረበት ። ደብረ ታቦር ላይመለስ እስከ አሁን የቀየው ላ ንስ አሁን ቢጨመርበት ደግሞ ቴዎድርስ ምን ይሰማዋል ? ለጀመኝ ይፈልገው ይሆናል ። በመልእክተኛ እንዲያሳውት ምክንያቱ የሚያሥ ቅበት ወይም እጉል ሆኖ የሚታይበት መስለው ። በኃላ እንዲያው ግስ ረዳቱ የሚሻል መሰለው ። “ እንግዲህ ስንቅሽን አሰናሽ ! ” አለ በመ ጨረሻ ።

ከመይዘር ደብረ በቀር ግንም ላያውት ከሠራተኛ በለውን ብቻ ይዘው አንድ ቀን ጧት በላውና በር ከጉንደር ወጡ ።

እነ ንብርቡ ፣ የት እንደ ሌዱ ላይረጋገጥ ከጉንደር መተፋታቸውን ጋረድና አክሊሉ ሲሰሙ ትንሽ እንቆቅልሽ ሆነባቸው ። ወደ ደብረ ታቦር ከሆነ እንድያውን ንዙን ነቅሱ መሌድ ነበረበት ። ባለሟሉን ስንኳ አላስከተለም ።

“ እንግዲያው ደብረ ታቦር እንሌለን ! ” የሚል ሐሳብ አክለሌ አቀረበ ። ጋረድ በተያቂ መልክ ትኩር ብሎ አየው ።

“ እዎ በቶሱ ደብረ ታቦር መሌድ አለብን !”

ጋረድ አሁንም ያልገባው እንደ መሰለ ቀረ ።

“ እየህ ንብርቡ ደብረ ታቦር ተሌለ ፣ ተነሚሽቱ የት አባቱ እንደ ጠፉ ግወቅ አለብን ። ደብረ ታቦርም ሌዱ እንደሆነ እንዱ ብልያት መላ ትን ተዐይን አለግራት ነው ። ከዐይን ተጠፉ ፣ ተጆሮ ተራቀ መምጣው አይታወቅም ይባላል ። ንብርቡ ፣ ድንገት ተነሥቶ የሌደው ለነገር ቸኩሎ ተሆነ ፣ እኛ ደሞ ነገራችንን ግዘጋጀት ነው ። ”

ሁለቱም ድንገት የመርካት ስሜት አድርባቸው እየተያዩ ተግግቱ ፣

ለጊዜው ያሰለፉትን መጠነኛ ሠራዊት ያለው ጋረድና አክሊሉ ደብረ ታቦር ሲደርሱ ፣ ከተማዋ ያሌት በመንተል ፣ ወይም በመ ትኩል ላይ ያለ የሚተራግመስ ሾር ሠፈር መሰሙ አገኙት ። ከመድኃኔ ሥም ቤተ ክርስቲያን ጥግ አንሥቶ ፣ የመሀሪቹ መንደር እየተባለ ወደ ሚሠራው ወደ ጋፋት በሚወስደው ረዣዥ መሬት ላይ ብዙ ድንኳን ተገ ተገቢል ። ጸሐ ጸሩን ይዞ ቢቶች ይመራሉ ። በዘህ መከከል ከሸዋንገር ንር የሰንጋ ሌር የተመራውና በወርቀ ዘቦ የተከፈፈው የቴዎድርስ ድን ኳ እንደ ደማብ ጉብ ብሏል ።

በየድንኳኑ ውስጥና በየድንኳኑ መካከል ሴቶችና ሙሌዎች የልሰቱ ሥራቸውን ያከናውናሉ ። አብዛኛው ሠራዊት ግን በመሬሩ አልነበረም ። በርቱት ያሉ ወታደሮች ተሰብስበው የሚታዩት ከቴዎድርስ ድንኳን አክሊል ነው ። ጋረድና አክሊሉ ድንኳናቸው እስኪተከል ሰው ጠያይ ቀው ምክንያቱን ወጡ ። ደጃች ዓለሜ ፣ ወረኢሉ እንደ ገና ገፍተው ፣ ዘመቻ ሌደዋል ። ራስ እንግዳ ወደ አገው ምድርና ወደ አቸለር ወርደዋል ። ገልው ወደ ብጅና ተልኳል ። ሌሎች ሾር እበጋዞች በዘህም በዘያም የተ ነሣ መንደሌ ለመምታት ፣ የሸፈተ አገር ለመቅጣት በየሥፍራው ተበ ታትነዋል ። የቀረው ግን ፣ ጧት ጧት ቴዎድርስን ተከትሎ ወደ ጋፋት እያሌረ አብር የሚመለሰው ጣምሻውን ነው ። ተዋበች ታመው ከእልጋ ሊ ከኖሉ ሰንብተዋል ።

ግንት የመቢቶች መንደር እየተባለች የእጅ ባለሙያዎች ይኖሩባት የነበረችው መንደር ፣ በኃላ ከውጭ አገር የመጡ የወንጌል ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ተሰብስበው መኖሪውቢታል ። ቴዎድርስ ፣ ጋፋት የሌ ረገጀት መንደር እንድትሆን ያደረጉት ዋንትም ግረሻው ፣ ወገሉ ፣ ካራው ሌላም ብረታ ብረት ይመራበት እንደነበር ሁሉ አሁን ለሀገራቸው የሚሥሩ ፣ የእጅ ተበብ ግናለቂያና ምሳሌ እንድትሆን ነበር ። ብዙ ያኙ የውጭ አገር ሰዎች የማይግናትና የቀለም እንጂ የእጅ ጥበብሙያ የዘንም ብለው ለጊዜው ቢያኮረመሙም ፣ በቴዎድርስ ውትወታ ፣ በወ ግሬት የሚመራ የዕንጨት መሰንጠቂያ መንኩራኩር ፣ የእህል ወፍጮ ፣ የብረታ ብረት ግቅለጫ ፣ የናራ መሥሪያ ፣ የተሻሻለ የሸማኔ መሠር ሌላም ሌላም የእጅ ሥራ ግከናወኛ መግሪያ በያይነቱ አዳ ቱመውት ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ ታይቶ የማያውቅ የሥራ እንቅስ ቃሴ የሚኬዱባት መንደር ሆናለች ። መዘውሩ ሲሽከረከር ፣ ብረት ግቅለጫው ምድጃ ሲንቀለቀል ፣ ወናፉ ፣ አሸንዳው ሲንፎለፎል ፣ ብረት ከዚረት ሲፉጭ ፣ ቴዎድርስ ይህንና ሌላውንም እንቅስቃሴ ሲመ ለከቱ ፣ በሚደርሳቸው መጥር መጥር ወረ ፣ ከዘሥዶች የንበረው መንፈሳ ችው ትልል ደለቀል ። ሕልማቸው እንደ እውን ፍንቅው ብሎ ይታያቸ የል ። ‘ሬታቸው እንደ ተኬላ ወርቅ ይፈካል ይላሉ ፣ የሚያስተውሏቸው ሰዎች ፣ እንደ ሁናቴያቸው በዘህ እንደ ዋሉ ቢያድሩ የሚወዱ ይመስላል ።

ግን ፣ ኪታመሙት ሚሽታቸው እጠዝ ለመሆን ግምሻውን ወደ ሥር ይመለሳሉ ።

ጋረድና እክሊሉ ፣ ሌላም ወሬ አገኙ ። ንብርዱ ደብረ ታቦር እል መጣም ነበር ። " የት እባቱ ተሠወረ ! መንገድ ላይ ሰዎች እደጋ ጥለው ድራሹን እጠፉት ! ምናልባት የሚሽቱን ጉድ ሰምቶ ሣካ ውስጥ እንቋት እንደ ተራ ሰው ተሠውር ለመቀመጥ ታገር ጠፋ ! ወይንስ እንዳ የው ሕልም ሸፈተ ! ' እያሉ ተጠያየቁበት ።

ንብርዱ ፣ ከጉንደር ስንኳ መነሣቱን ቴዎድሮስ እንዳልሰሙ በበነጋው ከእረፍገው በኋላ ፣ ጭር ሲል ወደ ጓር ወጣ እያሉ ብዙ ተመካከሩበት ፣ ተወያዩበት ፣ ተከራከሩበት ።

በመንገድ ላይ ወንበዴ ገድሏቸው ከሆነ ምን ይጠቅማቸዋል ! ምንስ ይጉዳቸዋል ! በጠቅሜታ ረገድ እንደኛ እነሱን የጠረጠረበት ምሥ ጢር ከቴዎድሮስ ጆር ሳይደርስ ይቀራል ። ሁለተኛ ፣ ቴዎድሮስ እንድ ጉበዝ ጦር እዝማቹን ያጣል ። በሌላ በኩል ግን ፣ የንብርዱ ሠራዊት በሌላ ጦር እዝማች ሥር ከቴዎድሮስ ጋር ስለሚቀር ፣ የሠራዊቱ ኃይል የሚ ቀንስበት እይሆንም ። ተራ ሰው ሆኖ ለመኖር ተወውር ከሆነ ውጪቱ ያው የሞተ ያህል ነው ። በቴዎድሮስ ላይ ሸፍቶ ከሆነ ግን ነገሩ ድብ ልቅ መልክ ይኖረዋል ። እንደኛ ፣ የቴዎድሮስን ኃይል ይቀናንሰባቸዋል፡ ንብርዱ ፣ ከነባሮቹም ሆነ አዲስ ከሚመለምላቸው ብዙ የሚከተለው ወሬ ዊት እያጣም ። ቴዎድሮስን በቀላሉ ማሸነፍ ባይችልም ፣ በእርግጥ ያጫ ምላቸዋል ። ግንኮ ንብርዱ በሸፍትነቱ እየበረታ ከሔደ የጋረድንም ዕድል ሊያውክ ይችል ይሆናል ። ይህን ሲደርስ ያዩታል ። አሁን እያስጨነ ቃቸውም ።

" አሁንም የሆነ እንደሆነ ፣ ይሙትም በሕይወት ይኑር ፣ ይሸፍት ወይም ዐውቆ ይተፋ ፣ ጥቂት ጊዜ ካገኘን ... ጥቂት ጊዜ ካገኘን ... ጥቂት ጊዜ ካገኘን " እክሊሉ መጻጠሪያው ግሥ እንደ ጠፉበት የቅኔ ተማሪ የመጨረሻውን ቃላት ደግሞ ደጋግሞ ወዝር ተወው .....

ቴዎድሮስ ፣ ከጋፋት ሲመለሱ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፉት ተፃ በችን በማስታመም ስለሆነ ፣ አጋፋሪው ጋረድን ሲያቅርበው የቻለ ደብረ ታቦር በመጡ በአራተኛው ቀን ነበር ። በሰንበት ቀን ወደ ጋፋት እይ ሔዱም ። ከቤተ ክርስቲያን መልስ ቁርስ ከቀማመሱና ተዋበችን ከአ ጨዋወቱ በኋላ ፣ ከድንኳኑ በራፍ ላይ አቤቱታ ይሰማሉ ። ባለጉዳይ ይቀ በላሉ ፣ እጅ ያስነሣሉ ፣ አክሊሉን ወደ ኋላ በመተው ጋረድ ቀርቦ እጅ ሲነሣ የተቀየሙበትም የተቆጡትም ወይም የተደሰቱ ሳይመስሉ ፣ ወገብ ሰበር ላደረገ እጅ እነሣው ፣ እንገታቸውን ቀልበስ በማድረግ አጸፋውን መለሱለትና የወገራ ግዛቱ እንዴት እንደሆነ ጠየቁት ። ከተሾመ ጊዜ አንሥቶ ወገራን የረገጠው እንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም ፣ ከዚያው እንደ ፉ

አጉም ሰላም እንደሆነ አስመስሎ ተናገረ ። ግን ፣ እክክሊሁም በተኛና አፋሙጡም ። ከድንክ ወንበር ላይ ተቀምጠው ከጉናቸው የፋመውን የሽየውን ምርኮኛ ምኒልክን እየደባበሱ ሐሳባቸው ወደ ሌላ ርቀ የሔደ ይመስል ወልር ወልር በሹክሹክታ ያናግሩታል ። ቤጠባቸው ያሉት ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ፣ ቆንስል ፕላውዲንና ሌሎች ጥቂት ሰዎች ፣ የቴዎ ድሮስን ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ይመስላሉ ። የወትሮው የሞቀ ጭውውት አልነበረም ። ' የሚሽቱ ሕመም እንደሆነ ለምን ድፍት ብለ አብርሞት አይደፉም ለኔ ብሉ ! ' አለና በሆጹ ከአባቱ ጋር ወደ ራስ አሊ ገቢ ሲመላለስ ፣ እሱም ለተዋበች ተሰምቶት የነበረው ፍቅር ላንፃ ፍታ ታወሰው ። ግን ቅንጣት እጩኔታ ኃልተሰማውም ። እንዲያውም ኣማ የአባቱን የደጃች ከንሱን ፈቃድ እየፈጸመ እንዳይቀየሙት ብሎም ይሁን ፣ ከልቡ ለጋረድም ከበሬታ እየሰጠ አብረው ማደጋቸውን አከሊሉ ባለደረባት የምኞት ዐይን ፣ ከአውኑ ደጅ ጥናቱና እጅ አነሣሙ በአጸፋው ከተደረገለት የንቀት አቀባበል ጋር ሲያስተያየው ቁጭቱ እንደ ሬት መርር ተሰማው .....

" ጊዜ ! ጊዜ አልከኝ ? " አለ ጋረድ ሁናቴውን ለእክሊሉ ከነገረው በኋላ ፣ ዐይነ ልቦናው ከቴዎድሮስ ሬት ትርዕይት ተተከሎ ቆይቶ ነበርና ድንገት ከሐሳቡ ነቅቶ ።

"እዎ ፤ የጥቂት ሳምንት ጊዜ—" ሲል እክሊሉ ራሱን እየነቀነቀ መለሰለት ።

" ለምኑ ? "

" ለሁሉም ነገር ጊዜ ይበጃል ። እየህ ፣ ' ሲርሙ የታጠቁት ሲርሙ ይፈታል ' ነው ። እሁንም የሆነ እንደሆነ ንብርዱ የት እንደ ደረሰ ፣ ወይም ምን እንደ ነካው አጥርተን ማወቅ አለብን ። ከዚያ በኋላ ደሞ ባወቅነው ነገር መሠረት የሚያስፈልገውን ለማድረግ... "

ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ፣ " ጊዜ ? ጊዜ አልከኝ ? " ሲል ጋረድ በሕ ልም ዐይነት ተናገረ ።

" እዎ ! እዎ " አለ አክሊሉ ፣ መልሱን ከመሬት አፍርጦ የሚያወጣ ይመስል ደቅ ደቅ እያደረገ በመርገጥ ። ' ቦ ጊዜ ለሡሱ ' ብሏል መጽ ሐፉ ። " ድንገት የመጣለት ጥቅስ ከጉዳያቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ባይረዳውም ፣ በግዕዝ በመነገሩ ብቻ አንድ ዐይነት ምሥጢራዊ እምነት እንደሚያሳድርበት ተሰማው ። " ' እዎ ! ቦ ጊዜ ለሡሱ ! ' ለሁሉም ጊዜ አለው ሲል ነው ። ለመሾም ፣ ለመሻር ፣ ለሁሉም ጊዜ አለው ። ሰው ጊዜ ካገኘ በጊዜው የፈለገውን ያደርጋል ፤ ያገኛል ሲል ነው ። ለመሆኑ በጉሩ ከብት ሽምጥመህ ጉንደር ደርሰህ ለመምጣት ስንት ቀን ይፈጅብሃል ? "

ጋረና ጥፍት አለች፡፡ "ከዚህ ታላቅነሙሀኝ አራት እምነት ተነሳ

" መንገዱ ላይ ተቁመሮ ይገደ እስቀየርከም ቢሆን፡ደግን ርዲ እንፍራህ እንደሆነ ያንተው ነው ፡"

" ምነኛት አለ የሞልርበት ?"

"ትወርት የልርበትን ለማውት ነዋ፡ የሚያውት ቢናር መደወር ደፈፈ ናቸው ፡ "

"ቀዲያ እቶቸው መሲያቸውን እንደምታውቀው ነው ፡ ለትንኩ ብን ተተዳሉ መቆ ትንፍሽ ይሉና ?"

"ሶኖ ባዝራ ሲጀቸው ታውጣውልሃ ፣ መርጀህ አልነባረች ፣ እሱ ንም ቆንጠየ ታጂርት ያው ነው ፡ "

"እዲስ አትትትኝም ! " አለ ጋረና በስራት ፡

"ተዚያ በኋላ እናያለን ፣ ጀግንነቱን ላንተ ፣ መላውን ለኔ ተውልኝ ሲጅ ጋረና !" አለው አክሊሉ በእረግመሩ እየተከራከረ ፡

አረጅም ጊዜ ሳይነጋጡ ዝም ብለው ወደ ድንኳናቸው ተገቡ ፡ እያንዳንዳቸው በየራሳቸው ፡ ሶሮ ቂማቸውን በሚወጡበት በየራሳቸው የልቅብ ሳጋር ስተመው ነበር ፡

ምዕራፍ አራት

ቱምድርስ ፣ ማመን የሚያችተው መርዶ የተነገራቸው ከራት ላይ እንደ ተቀመው ነበር ፡ ራቱ ከዘወትሩ የተለየ ድግስ ሳይናርስትም ፣ ተቀ ሙት ትነገ ሽል ብቷቸው እንደ ምንም ከአዲጋ በመነጣት ገዜታ ላይ ቀር ሙው ስለነበር የንጅ ሥራ ልውተት ለማስፍሩት ፡ የማህርን ሥራ ለማ ቋም ስለሚመጡት የአንግሊዝ የዋቂዎች ከቆንስል ፕካውሩንና ከሊቀ መኳስ ቦልንስ ጋር ያደረጉት ውይይት ትልት ተስፋ እሳድርባቸዋል ፡

ቱምድርስ ፣ በዚሙ ሁለ እንደ መርዳት ብለው ፣ ' በኳሣ ሞት እንዲ ሳሚኝ ' እያለ ወሳጀን ስላቆሳመው ወታደር ሲቀልዱ ፣ ብዙ ጊዜ የሚፈሰቸው የአልቅኝ አገዜራቸው ጉበቱ አቶን በመሳቱ ጋርና ጀጀ ርቁቸው ጅከ አለ ፡

እንደና እንዲንግራቸው በማለት እንጂታቸውን ወደ ርሱ አዞረ ፡ አውንም በጅከጅከታ ነገራቸው ፡


"ለምን ሥህ ብለህ አትነግረኝም ፡ ወይስ ከኖድ ምሥጢር ነው?" ፈታቸው ባንዲ ተጠየመጠ ፡ አጀከርቹው እንደ መደናገጥና እንደ መፎ ናገር ብሎት ቆመ ፡

" ምንድነው የምትለኝ ?" ሊሉ መልስው ጠየቁት ፡ የተናገረውን የነው ቢሆንም ጆርአቸውን ተጠራጥረው ፡ ላመል ያህል ድምውን ከፍ አድርገ ለምስትኛ ጊዜ ነገራቸው ፡

" ጅረ እንድ በሉኝ ይህን ሰው ! ወናም አልያዝው ?" የቱም ድርስ እነጋገር የተያቱ ሳይሆን የተጭጠጽ ወይነት ነበር ፡ ውሎም እንደ ሚጠቂ ጅርውን አቆመ ፡ መጠጠም ምግቡም ላንዳፍታ ተረሳ ፡ መገ ናኘቱ ፡ ቁውውቱ በነፋስ እፍ ተብሎ የጠፋ መሰለ ፡

"ምንድን ነው አባ ታጠቅ ?" በማለት ከአጠገባቸው ከሙስተኛዉ መነብ የተቀመጠው ሊቀ መኳስ ቦልንስ ጠየቁ ፡

"ደቀሞብራል ! " አሉ ቱምድርስ እጃቸውን በማወራጨት ፡



“ እረ እውነት ነው ጃንሆይ !” አለና አሽከርዮው በመጨነቅ እጁን አፋተገ ።

“ ገብርዬ ! ? ” የቴዎድሮስ እንጋገር የጥያቄ ሳይሆን የመገረም አጋኖ ነበር ።

የእልፍኝ አሽከሩ በማፈጋገጥ ራሱን ላይና ታች እወዛወዘ ።

ጸጥ ባለው ድንኳን ውስጥ የተዋበች ድምፅ ጮልቶ አስተጋባ ። “ ምን ሆነ ገብርዬ ?”

“ አሆሆ! ጀሮ አይሰማው የለ !” ቴዎድሮስ ከመገረም ሌላ፣የሰ ሙት ነገር ከጀሮዋቸው እንዳይገባ ለመከላከል ያመስል ፣ ሁለት ጀሮግ ንዳቸውን በመዳፋቸው ደገፉ ።

ተዋበች ዘንበል አሉና ዳበስ አደረጉዋቸው ። “ምንድን ነው ፣የኔ ጌታ ? ”

“ አሆሆ ! ገብርዬ ሽፈተኮ ነው የሚለኝ !” አሉ ቴዎድሮስ ፣ ድን ገት እንደ መወራጨት እየሞከራቸው ። እንደ መነሣት ታጡና መልሰው ተቀመጡ ። በድንኳኑ ውስጥ ንግግር አይሉት ትንፋሽ አንድ ዐይነት መስገምገም እስተጋባና መልሶ እርጭ ፣ጸጥ አለ ። ላንዳፍታ ዝምብ ሲበር የሚሰማ መሰለ ። እንገቶች በያሉበት በመሶቡ ላይ አቀረቀሩ ።

ተዋበች ማባበልም ፣ መጨነቅም በሚገልጽ አኳኋን የባላቸውን ክንድ ጨበጥ አደረጉ ።

“ እንተ ደሞ እያደር የምትሠራውን እታውቅም ! ስንት ጊዜ ነገ ርኩህ ?” ሲሉ አሽከርዬውን ተቆጡ ። ቴዎድሮስን ሊያስቆጣ የሚችል ጉዳይ ሲሆን ፣ አስቀድሞ እርሳቸውን እንዲያግክር ደጋግመው ነግረውት ነበር ። አለዝበው የሚያቀርቡበትን መንገድ ያወ ቁታል ።

“መቸ አጣሁት !” አለ አሽከርዬው ፣ በይቅርታ አጠያየት ወገቡን ሰብሮ ፣ አንገቱን ደፍቶ ። “ ቢጨንቀኝ ነው ፣ እጅግ የሚያጣድፍ ከባድ ጉዳይ ስለመሰለኝ ። ”

“ ደግ አረገ ! እውነቱን ነው ” የቴዎድሮስ ሰውነት በመኮሳተር ፍርጥምጥም አለ ። “ በመጥፎ ወሬ መበርገግ ከያዝኩማ ፣ ምኑን ሰው ሆንኩት ! እንኳን ኢትዮጵያን አንድ ግድረግ ፣ እንኳን ትልት ግድረግ ቀርቶ ለራሴውም ርባና የለኝም ማለት ነው ። ብቻ ነገሩ አስገረመኝ ፡ የማይታመን ሆነብኝ እንጂ !” መልሰው ትክዝ አሉ ። “ግን፣ ገብርዬ ለመሆኑ ተረጋግጧል ?”

“ አዎ ! አዎ ! ” አለ አሽከርዬው ፣ አሁንም መዳፉን እያፋተገ “ ወሬውን ያመጣው መልክተኛ አሁንም ተውሎ አለ ። ተርሱም በኋላ

ሌላ ሰው መጥቶ ገብርዬ መሸፈቱን ላባ ታጠቅ ንገር ብሎ ሔደ ። ሰውዬው እንደ ተናገረው ነጋራትም እያስመታ ነው አሉ ። ”

“ ለመሆኑ የት ላይ ነው ?”

“ ሚልጋን ወልፎ ወይኒ ላይ ።”

“ እሀ ! ተሚሽቱ አገር መግባቱ ነው ?” ቴዎድሮስ በመገረም እንደ መንከትከት ኪታጣቸው በኋላ በትካዜ ተዋጡ ። እገሜቸውን በቀኝ መዳፋቸው ላይ አስደግፈው ፣ በግመንና ባለግመን መካከል የሚ ሚገቱ ይመስል ላመል ራሳቸውን እያወዛወዙ ቆይተው ፣ “ አሆሆሆ ! ገብርዬም ? ገብርዬም ?” የተነጋገሩት ከራሳቸው ጋር ነበር ። ድምፃ ቸው ለሌሎቹ መሰማቱ አልታወቃቸውም ። በራሳቸው የትዝብት ባሕር ሰጥመው ነበር ። ድንገት መንጥቆ ያወጣቸው የደጃዝማች ቢሆንኝ ድን ፋታ ነበር ።

“እኔ ያንተ አሽከር ፣ ያንተ ቡችላ ! ያንን አህያ ፣ መጅ እሸከሚ እምጥቼ ከፊትህ ባላንበረክከው እኔ ቢሆነኝ ሱራ አላጠለኩም ! ሒድ በለኝ ! ላዙኝ አሁኑኑ !” እያሉ ቆመው መርካከር ሲያምሩ ፣ በደንኳኑ ውስጥ የፈዝ ሁካታ ተነሣ ።

ቴዎድሮስ እንደማይልኩዋቸው ፣ ቢዘምቱም ገብርዬን ድል አድ ርገው እንደማይመለሱ ሁሉም ያውቁት ነበር ። ደጃዝማች ቢሆንኝ ፣ በጐልማሳነታቸው ጉበዝ የነበሩ ቢሆንም ፣አሁን ዘመቻ ላይ ከዋሉ ረጅም ጊዜ ያለፋቸው ፣ ሠራዊትም ግዛትም የሌላቸው ፣ ወደ ሰባ ዓመቱ የተ ጠጋቸው ሽማግሌ ናቸው ። ሰውነታቸው ደካክሟል ፣ የተንገርገገ ገብስማ ጺማቸውን እያሻሹ በአደባባይ ፣ በሰው መካከል ሲገኙ ፣ ለሽም ግልናና ለምክር የተሠየሙ ይመስላሉ ። ግን በቅርብ የሚያውቋቸው ብዙ ሰዎች ለጨዋታ እንጂ እስከዚህም ለቁም ነገር አይመድቧቸውም ። እን ዲያውም ፣ በነገራቸው ላይ ውሸት ስለሚጨምሩ ተረብና ፉከራ ስለሚያ በዙ ፣ በትንሹ በትልቁ “እኔ የካሣ አሽከር” ማለትን ፈሊጥ ስላደረጉት ፣ “ የሽማግሌ ተላል ” እያሉ የሚያሚቸው አሉ ። ብቻ በክፋት የሚያስ ባቸው የለም ።

ቴዎድሮስም ቢሆኑ ፣ ደካማ ጠባያቸውን በማወቅ ቁም ነገር ላይ ባያውሏቸውም ፣ ቋራ በሽፍትነት ሳሉ የሠሩላቸውን ውለታ በማስታወስ ሽምግልናቸውንም በማሰብ ፣ ፍሬ ፈርስኪ ጨዋታቸውን ወልፎ ወልፎ እየተዝናኑበት ለሰሙ ያህል የደጃዝማች ቀሚስ ሰጥተው እንደ ፈለጉ በእ ጠባቸው እንዲገኙ ፈቅደውላቸዋል ።

ቴዎድሮስ ፣ በደጃች ቢሆንኝ ሁናቴ ትንሽ ፈገግ አሉ ። “ባትነግ ረንም ስላንተ ታማኝነት እናውቀዋለን ። ግን ገብርዬን አንተ ነህ . . . ? ” ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ራሳቸውን ነቀነቁ ።

"እኔ ቢሆንኝ ! እኔ ያባ ታጠቅ እሸከር ! ያንን ፈ ፈ . . . " እየተነ ቆራጠጡ ታሱን ለመጨረስ ሲቃጡ ፣ ቴዎድሮስ በድንገት እጃቸው ። የታሱ መጨረሻ ጉዟቸው ነበር ።

"ተው ! ተው በል ቢቀህ !" አፈጠጡባቸው ። "አሁን ምንም ጠላት ቢሆን ጉብርዱ በግንም እፍ የሚለደብ ሰው አይደለም ። ከፊቱ ላይ የማትተነፍሰውን ለምን ትወሻክታለህ ?"

" እኔ ያንተ እሸከር ! " አሉ ደጀች ቢሆንኝ ፣ ወመል ሆናባቸው አሁንም እንደሚፈክር ሰው ከተቀመጡበት እንደነና ብድግ አሉ ።

" እኮ ቢቀህ ! " በግለት ቴዎድሮስ ከፍ ባለ ድምፅ ተቆጡ ። " ደግሞስ ዘር ቆጥሮ መሳደቡ ምን ዋጋ አለው መስላችሁ ? "አሉ ድም ፃቸውን መለስ አድርገው ። "እኛ ጥቁር ፣ ወይም ፣ የቀይ ዳማ ፣ ቀይ እያ ልን ፣ የጨዋ ዘር ፣ የምንቱስ ልጅ እያልን እንለያለን ። ፈረንጆች ደግሞ ሁላችንም በመደዳ አንድ አድርገው ነው የሚቆጥሩን ! "

' ደጀዝማች ቢሆንኝ ፣ መጫወቻው እንደ ተወለደበት ሕፃን አቀር ቅረው የስርቆሽ እያዩ ዝም ብለው ተቀመጡ ። ድንኳኑ ጸጥ ፣ ረጭ አለ ። ቴዎድሮስ ፣ በየገቢታው ሁሪያ የተቀመጡትን ባለሟሎቻቸውን ተራ በተራ በወይናቸው ታኙ ። ከዚያም ለጥቂት ጊዜ ትክዝ ብለው ከቆዩ በኋላ ፣ ቢታከተ ስሜት ከተቀመጡበት እየተነሡ ፣ " ተናንተ ደሞ ግን ይሆን የሚከዳኝ ?" አሉና ወደ እልፍኛቸው አመሩ ። ተዋበች ሊከ ተሉዋቸው ፣ ሌሎችም መኳንንት ገበታውን እየተዉ ወጡ ።

ተዋበች ፣ የባላቸውን የንዴት ፣ የደስታ ፣ የሐሳብም ሆነ የትካዜ ስሜት እንዴት ማለዘብ እንደሚችሉ ከብዙ ዓመታት አብሮ መኖርና ማስተዋል ዐውቀውታል ። ለምሳሌ ፣ በሽፍትነት በነበሩበት ጊዜ ቢኃይል ሲናደዱ ፣ ከምንጭ ይሁን ከእንስራ እንደ ምንም ከአቅራቢያ ባገኙት ውሃ ፊታቸውን ረሜጭተው ፣ እፋቸውን ተጉማምጠው ና ትንሽ ተጉ ንጭተው ፣ "እፎይ ! እፎይ ! " ይሉና ቀለል ይላቸዋል ። ከውስጣቸ ውም የሚቃወለውን እሳት ጨርሶ ባያጠፋውም በረድ የሚያደርግላ ቸው ይመስላል ። ይህንን የተገነዘቡት ተዋበች የባላቸው ቁጣ በገነፈል ጊዜ ከሰው መካከል ገለል አድርገው ይወስዱና ፊታቸውን በውሃ ለት ልቀው የሚጉነጩት ይሰጧቸዋል ። ከዚያም መቀነታቸውን እያላ ሉ ጨርሶ የሚያበርዱበት ሌላ አቀራረብ አላቸው . . . ትካዜ በተ ጫናቸው ጊዜ ደግሞ ፣ ሊያታልሉላቸው የሚሞክሩበት መንገድ ከዚህ የተለየ ነው ። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተጠቀሰው ሳምሶን ፣ የስሜት ኃይ ላቸው ከጸጉራቸው ላይ ያለ ይመስል ፣ ወይም ኃጣውን ሊደባብሱት ገራም እየሆነ እንደሚሔድ እንበላ ፣ በለዘብታና በሹክሹክታ እያጨ ዋወቱ ፣ ሹርባቸውን ፈትተው እንደነና ይሠሩላቸዋል ። ወይም መፈታት የጀመረውን ያስተካክሉላቸዋል ።

ቴዎድሮስም ትካዜያቸው መለስ እያለ ፣ " እረ ተይ ! ነጨሽኝ እኮ " እያሉ በሙቀደ ብድራቸውን መቆንጠጥ ይጀምራሉ ።

አሁን ግን አልሠራም ። ተዋበች የባላቸውን ሹርባ አስተካክ ለው ከሠረሉ በኋላ ፣ በሐሳብ እንደ ተዋጡ መቅረታቸውን ሲመለከቱ ፣ " ኡጭ እቴ ! ምን መጨነት ነው ! የሸፈተ እንደሆነስ ዛሬያ ! " አሉ ነጡን ያታለሉ በመሰለ ። በሆጻቸው ግን ጸሎት ይዘው ነበር ። ' እባክህ ፈጣሪ የኀላግውን ፣ የምኞቱን ቅንነት እይተህ እርዳው ። ተግለደው ፣ አትግለው ፣ ሐሳቡን ላልተረዱት እንተው በተበብህ ከሥ ትላቸው ' እያሉ ።

" ግን ! እኔ ነኝ የምጨነቀው ! አላወቅሽኝም ልበል ተዋቡ! ወይስ እያደር ደም ዘነጋሽኝ ! ለምን ሞት ራሱ ሥጋ ለብሶ አይመጣም ! እኔ የመይሳው ልጅ !" እነጋገራቸው ግን ፣ የጉራ ወይነት ሳይሆን የቁርጠኝ ነት ርጋታ ነበረበት ። " ብቻ ነገሩ አስገረመኝ እንጂ ! "አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

" ምኑ ነገር የኔ ጌታ ! "

" እህ ! የጉብርዱ መሸፈት ነዋ ! መላ መኳንንቱና ሠራዊቱ ቢከ ዳኝ እይደንቀኝም ነበር ። ግና እንደራሴው የማምነው ጉብርዱ! ራሴ በራሴ ላይ የሸፈትኩ ነው የመሰለኝ ። ምን አረገኝ ብሎ ይሆን ! " ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁና መልሱን አሰላሰሉ ። " እንደ እንግዳ ፣ ራስ ስላላልኩት ተቀይሞ ይሆን ! ግን ተስሙ ምን አለው ? የመር አዝማች ያረኩት አሉን ወይንስ ታንጉትን ምክንያቱን ሳልገልጽለት አሳድጌ ስለ ዳርኩለት ፣ ለብቻም ስለማነጋግራት ሌላ ነገር መስሎት ? እንዲሆማ ታሰበ በማም የዋህ ነው ። "

ለሁሉም የጉብርዱን ጠባይ እንደሚያውቁት ፈት ለፈት ይወይ ቃቸው ነበር እንጂ አኩርፎ ሹልክ የሚል ሰው አልነበረም ። ከመጀ መሪያው ያመኑትም በዚህ ግልጽነቱ ነበር ። ዕድሉን ከእርሳቸው ዕድል ለማቆራኘት መጥቶ መጀመሪያ የተገናኘችው ጊዜ ትዝ አላቸው . . .

በራስ አሊ ላይ ሸፍተው ፣ መላውን ቋራ ፣ ሜቆን ፣ አዳጎ አገርን እስከ አለፋ ጣቁላ ድረስ ይዘዋል ። አንድ ቀን ማምሻ ላይ ወታደሮች አንድ ሰው ያቀርቡና እጅ ይነሣል ። ' ለምን በዚህ ሠፈር መጣህ ? ' አሉት በጥርጣሬ መልክ ።

' ዝናህን ሰምቶ ታንተ ዘንድ ለማደር ! ' ሲል ደፈር ባለ አንጋገር መለሰላቸው ።

' አገርህ የት ነው ?'
' ዙራምባ !'
' ጋይንት ? '
' እም ! ደብረ ታቦርም አወለዳለሁ !'

‘ ባዲያ ተጋይንት ነው እዚህ ድረስ የመጣኸው ? ወሬዬንስ እን ዴት ሰማህ ? ’ ትኩር ብለው ተመለከቱት ። ‘ ደብረ ታቦርም ፣ ጋይ ንትም የእነራስ አሊ ግዛት ነው።ተነሡ ተልከህ ...’ አጠያየታቸው እንደ ዋዛ ነበር ። ሰውዬውን ግን ከቆመበት ያነጠረው መሰለ ።

‘ እኔ ገብረ ሕይወት ነኝ ፣ለነ አሊ የምሰልለው ! ጉበዝ አገኘሁ መስሉኝ ነው እንጂ ! ’ አለና ዙሪያውን ያለውን ወታደር ሁሉ ከምንም ሳይቁጥር ጣጥሶ ለመሔድ ወደ ኋላ ዞረ ።

‘ቆይ እስቲ ! ’ አሉት በመገረም ። በሐቀኝነት የሚፈታተኑ ይመ ስል ላንዳፍታ ተፋጥጠው ተያዩ ። ‘ እምኝሃለሁ ፣ ገብረ ሕይወት ነው ስሜ አልከኝ ? እኔ ደሞ ተዛሬ ጀምሮ ‘ ገብርዬ ’ ብየሃለሁ ። ’

ከዚያን ቀን ጀምሮ ሐቅንና እምነትን አንድም ቀን ትንጣት ሳያ ጓድል የኖረ ሰው ነበር .....

“እሆሆ ! ጉድኮ ነው !” አሉ ቴዎድሮስ ከሐሳባቸው እንደ ተመ ለሱ ፣ ሳይታወቃቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ።

“ እሁን እስቲ ወረፍ በል የኔ ጌታ ። ግንኙውንም ነገር ነገ እንደርስ ቢታለን፣ጪት መኳንንቱ እንዲሰባሰቡ ላድርግ?” ሲሉ ተዋበች ጠየቋቸው።

ቴዎድሮስ በእወንታ ራሳቸውን ነቀነቁ ። እሁንም ከሐሳብ ትካዜ መውጣት አልቻሉም ።

በበነጋው ጪት ፣ በደብረ ታቦር የሚገኙት ጦር አበጋዞች ተሰብስ በው ጉባኤ ተደረገ ። ቴዎድሮስ ፊታቸው ጠውልጎ ፣ አስተያየታቸው ታክቶ ፣ በወይናቻቸው ዙሪያ ቀጫጭን መሥመሮች ወጥተው ፣ ፅረፍትና እንቅልፍ እጥተው ማደራቸው ያስታውቅ ነበር ። አሁንም ቢሆን በነ ብርዬ ላይ ስለሚደረገው ዘመቻ ጉባኤ መሰብሰቡ ራሱ የባሰውን እላ ዝኗቸዋል ፣ አስጠልቷቸዋል ። “በገብርዬ ላይ ከሌላ ሰው ጋር ልምከር” ሲሉ ከራሳቸው ጋር ተገረሙ ። ነገር ግን ፣ የመጨረሻው ውሳኔ የራሳቸው ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስለ ግንኙውም ከፍተኛ ጉዳይ ከሌሎች ጋር መመካከር ተገቢና አስፈላጊ መሆኑን እየተገነዘቡት ሔደው ነበር ።

በአብዛኛው የሊቀ መኳስ ዮሐንስ ሐሳብና ምክር ነው ። ስለ እን ግሊዝ ምክር ቤት ተርኮላቸው ነበር ። የፓርላማ አወራርና የዲሞክራሲ ፍልስፍና እምብዛም በጥልቀት ባይገባቸውም የመመካከርን ጠቃሚ ነት ተገንዝበውሊታል ። መሠረተ ሐሳቡ ለኢትዮጵያውያንም አዲስ እዩ ደለም ። ‘ከአንድ ፈጣሪ ብዙ መካሪ ’ ፣ ‘ አንድ አይነድ ፣ አንድ እያፈረድ ’ የሚለት ምሳሌዎች የሚያረጋግጡት ይኸንኑ ነው ። የሚጉደለው ሥር ዓትና መልክ ማሲያዝ ነው ።

ሁለም ከንፈሩን የሚነክስ መስሉ ቢታይም ፣ በጉባኤ ላይ ከተቀ መጡት መኳንንት ምናልባት በልባቸው የተደሰቱ ይኖራሉ ። ጀግንነ ቱና የቴዎድሮስ በጣም ቅርብ መሆኑም ያስቀናቸው ብዙ ናቸው። መው ደቁን አይጠሉትም ። ከዚህም የገብርዬ መወገድ ከፍት የሹመት ቦታ ስለሚፈጥር ፣ የእርሱንም ባይሆን ፣ በእርሱ የሚተካውን ሰው ሹመት የሚመኝና ለማግኘትም ተሰፋ የሚያደርገው ብዙ ነው ።

የምክክሩ ዋና ጉዳይ በገብርዬ ላይ ስለሚዘምተው ጦር መሪ ነበር ። ቴዎድሮስ ፣ ራሳቸው እንዲያዘምቱ የቀረበውን ሐሳብ ብዙዎቹ እልተሰ ማሙበትም ። ቴዎድሮስ ራሳቸው ሐሳቡን ለመነሻ ያህል አቀረቡት እንጂ ፣ ሌላ የመጨረሻ ምርጫ ከሌላቸው በስተቀር ቂርጠው እንደማይ ዘምቱ ይሰማቸው ነበር ። በገብርዬ ላይ መዝመቱን እንዳንድ ነገር ተጸ የፉት ።

‘ደጃች ብርዬ እንዲዘምት’ የሚል ሌላ ሐሳብ ቀረበ=‘‘ እንተስ ምን ይመስልሃል ? ብርዬ ’’ ሲሉ ቴዎድሮስ መለሱ ።

“ ጌታዬ እንዳለ ’’ ሲል መለሰ ። ግን እምቢ ላለማለት እንጂ የሚ ጓጓለት ዘመቻ አለመሆኑን ከአነጋገሩ ያስታውቅ ነበር ። ቴዎድሮስም ቢሆኑ ፣ ስለ ተጠቀሰ ጠየቁት እንጂ የደጃች ብርዬን መዝመት ከልባቸው የሚደግፉት አልነበረም ፣ በሁለት ምክንያት ። እንደኛ ፣ ሁለቱን የት ርብና የልብ ጓደኞሞች እንዲዋጉ ማድረግ በደል መስሎ ታያቸው ። በሌላ በኩል ፣ ከገብርዬ ወዲያ የሚያምኑት ካልነበራቸው ብርዬስ በዚ ያው ከንደኛው ጋር ቢተላቀልስ የሚል ቅንጣት ጥርጣሬ ተሰማቸው ።

“ የለም ፣ እንተ እንዲያውም ወሎ ዘምተህ ፣ መሐመድ በሽርን ላይ ቱሙ ቅጣት ብትተጣልኝ ነው የሚሻለው ’’ አሉ ቴዎድሮስ ።

የሌሎችም መኳንንት ስም በየተራ ተጠቀሰ ። ግን በሚጠቀሱት ሰዎች ላይ ጉባኤው በቅላሉ ከስምምነት ለመድረስ አልቻለም ። እንዳን ዶች ራሳቸው ለመዝመት በመፎካከር የሌላ ስም ሲጠራ ልዩ ልዩ ምክ ንያት እየሰጡ ይከራከራሉ ። ሌሎች ፣ የሚጠሉት ሰው ከገብርዬ ጋር ሊኖ እንዲሞትላቸው ፣ ደጀዝማች እገሌ ቢያዘምት እኖሉ አስተያየት ይሰነዝራሉ ። ሌላው በሌላ ምክንያት ይታመማቸዋል ። እንዲህ እያለ የብዙ መኳንንት ስም ተነሥቶ ከተጣለ በኋላ የጋረድ ስም እንደ ዋዛ ተጠቀሰ ።

ጋረድ፣እንደ ሌሎቹ ለጉባኤው ይታደም እንጂ መደ ፍር ዋጋ ይኖ ነበር የቀቀጠላው ። ለሌሎች ሲናኩሩ ፣ በሆዱ እየፈገግላቸው በትዝብት

ከመመልከት በስተቀር እንዳችም አስተያየት አላቀረበም ። በስብሰባ ደረጃ ከእነርሱ ጋር መክራከሩን እንደ ውርደት በመቁጠር ብቻ ሳይሆን እንደበቱን አላልጦት ነገር እንዳይስት በመሥጋት ዝምር ነበር ። ስሙ ሲጠቀስ ሁሉም በወይኑ ይፈልገው ጀመር ። ቴዎድሮስም እንገታቸውን ስገግ እድርገው ዙሪያውን ቃኙ ። ሳያስበው ከተቀመጠበት ተነሣ ። ' ግን ያውቃል ! ምናልባትም እንተ ዝመትበት ትባል ይሆናል ' ሲል አክሊሉ ቀደም ሲል የገመተ ቢሆንም ፣ ጋረድ በበኩሉ እስከዚህም ተስፋ አድርጎ ስላልነበረ በሁኔታው ድንገተኝነት ትንሽ ተደናገረ ።

ጋረድ ፣ የቴዎድሮስንና የሌሎችን መካሪዎች ፊት ሲመለከት ፣ ከርከራቸው ከእርሱ ላይ እንደሚያቢቃ ታወቀው ።

ቴዎድሮስ ፣ ለምን በጋረድ ላይ እንደ ወሰኑ ምክንያቱ ለራሳቸውም ግልጽ አልነበረም ። ምናልባትም እግራሞ ስላጡ ይሆናል ። ምናልባትም የደጃች ከንፉ ውለታ ሳይታወቃቸው ተሰምቷቸው ሌላ የተሻለ ሹመት ለመስጠት መፈተናቸው ይሆናል ። ወይም ደግሞ ፣ ያመኑትን ከዳተኛ በሚጠረጥሩት ዘመድ ሚጋጠሙ ልዩ የሰሜት ትርጉም ሰተ ታቸው ይሆናል ። በንብርዬ መክዳት ሕሊናቸው በጣም ተጎክቶ ስለ ነበር ፣ ስለ ምርሚቸው የምክንያት ምርምር ለማድረግ አላስቻላቸውም ።

'' በል እንግዲህ ተዘጋጃ !'' ብለው ጉባኤውን በተኑ ።

—2—

በሰፈሩ ለጋረድ የሚደረገው አመለካከት በአንድ ጊዜ ተቀየረ ። መኳንንት ሥራዬን ብለው ስላምታ ይሰጡታል ፣ ያጎጋሩታል ፣ ተራው ወታደርና ነፍጠኛ ብድግ እያለ እጅ ይነሣዋል ፣ ወይዛዝርት አንገታቸውን አቀርቅረው የጉሪዋ እያዩ ስለ እርሱ ይንሾካሾካሉ ። ከቴዎድሮስ ቀጥሎ የሁሉ ዐይን የሚያተኩርበት ሆነ ። ከዚህም የበለጠ እንደሚሆን ተሰማውና ትከሻውን ገልበጥ ፣ ደረቱን ነፋ ፣ ቋንጃውን ሳብ እያደረገ መራመድ ያዘ ።

ድንኳኑን ብዙ መኳንንት ያዘወትረው ገባ ። እንኳን ደስ አለህ ለማለት ፣ ምክርና አስተያየት ለመለገስ፣ ለመሸንገት ፣ ጉራ የሚለው በዛ። እንግዶቹን የሚጋብዝበት ግን አልቸገረውም ። ከዚህም ከዚያም የተቀጣጠለ የአንድ ፈታውራሪ ወራዊት ተሰየቶት ስለነበር ፣ ዘመቻ ከመነሣቱ በፊት ግብር የሚያስገባበት ፍሪዳው ፣ እንጀራው ፣ ጠጅ ጠላውና እሪቴው ከቴዎድሮስ ተልኮለታል ። በተጨማሪም በከረጠት የተቆመረ ጠገራ ብር የግምጃ ቤቱ ሹም ራሱ አምጥቶ ሰጥቶታል ። ያለም ምሥላ ሰሞነ አደረሰበትና ፣ ' አንም ጉርሻ የምልክበት ቀን ይመጣል ' ሲል አሰበ ። የራሱ መነሀር ብቻ ሳይሆን ሌሎቹን ለነገብር ሲያበቃ ታየው ።

'' እንዲያው ግን ፣ ነገሩ ሁሉ እንዲህ መሳኩቱ ያንቆሻል '' አለው ጋረድ አክሊሉን ። በበነጋው ጧት ሊዘምት እንደ ባሬ ፣ የተመደበለትን ወራዊት ግብር አጣልቶና ጥቂት መኳንንት በድንኳኑ ውስጥ ሲጋብዝ አምሽቶ ከሸኘ በኋላ ፣ ይሞቀት ከሚዘምተው የጭን ገረዱ ጋር ምሱቱ ብቻ ቸውን ነበሩ ። ጋረድ በዕድሉ የመደሰቱን ያህል በመጠውም ሞቅታ ተሰምቶት በአሰቸኳይ አፈላልጎ ያስመጣትን የጋሚ ቆንጆ አክሊሉን ሳያፍር እየደባበሰ ያሽኮራምማታል ። ሌላ ጊዜ እንደዚህ ያለ ሁናቴ ሲመለከት አክሊሉ ፣ ብርቱ ሥቀቱን የሚሰማው ቢሆንም አሁን ግን ደንታ አልሰጠውም ። እሱም በበኩሉ ሞቅ ብሎት በራሱ ርካታ ተዝ ናንቶ እንደ ዋዛ ይመለከታቸዋል ።

'' እመነኝ አላልኩም !'' አለ አክሊሉ በመኩራራት ።

'' አልተጠራጠርኩም ነበር ። ግን ዋና ቡዳ ነህ አክሊሉ ! ''

'' ተአምረኛ ግለቱ አይሻልም !'' አለው አክሊሉ ። በሐሳቡ ግን ምንም ወይነት ተአምር እንደሌለበት ያውቀው ነበር።ቅኔ እንደ መድረስ ፣ በግሰብ ፣ በግሰላሰል ፣ ለክፉም ሆነ ለደግ አእምሮን በግስጨነት ፣ በግስ ጠበብ የተገኘ ውጤት ነው ።

ስለ ንብርዬ መሠወር የአክሊሉ ምርምር መጀመሪያ ያተኮረው ፣ ሸፍቷል በሚለው ጥያቄ ላይ ነበር ። በጥሞና ሲያስበው የንብርዬ መሸ ፈት እውነት አልመስለው አለ ። ሰዎች እንደ ጠባያቸው የአሸፋፈት ወይነት አላቸው ። አንዳንዱ አንገረብና ቀሃ ወንዝ እንዳለፈ ጉና ምኑንም ሳይ ዘው ፣ ድል አድርጎ እንደ ግረኛ ያህል ኑጋሬት እያስጉሰመና እያስርከረ ጉራውን ይለቀዋል ። አንዳንዱ በሥውር ይወጣና አመቺ እስኪመስለው ድረስ ሪጅም ጊዜ አድፍጦ ይቆያል ። እንዲያውም ካልተመቸውማም ለሚ ፣ ራሱን ግዳኛ እንዲሆነው ' ገዳም ገባ ፣ መነነ ' እያለ ያስወራል ።

ንብርዬ ፣ እንደ መጀመሪያው ወይነት አጉል ጉረኛ ፣ እንደ ሁለ ተኛው ወይነት ፈራ ተባ ሳይ ሳይሆንም ፣ አክሊሉ ጠባዩን እንደ ገመተው መሸፈቱ ወይም አኩርፎ በረሃ መግባቱ እንዲታወቅበት ማድረጉ የማ ይቀር ነበር ። በሽፍትነት ጊዜ አጋር የሚገኘው ፣ ከቅርብ ባልንጀራ ብቻ ሳይሆን ከባላጋራ - ባላጋራ ነውና ፣ ቀድሞ የሚያግከረው ፣ ያም ቢቀር በረሃ ከገባ በኋላ በመላከተኛ የሚያስጠይቀው ሰው ቢኖር ፣ በሹ መቱ ምክንያት በቴዎድሮስ ላይ የተነሣው ጋረድ በሆነ ነበር ። ዛሬያ ካልሸፈተ ፣ ምን በላው ? ምን ዋጠው ? የት ደረሰ ?

አክሊሉ ፣ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ አእምሮውን ሲያስጨንቅ ቆይቶ ጋረድ ከወይዘሮ ይብሬ ልጅ ናንዲን ካመጣለት በኋላ ፣ መሬ ግዛመቱ መልእክተኛ በገንዘብ ገዝቶ እንዲሰገር ማድረጉ ቀላል ነበር ። ከዚያ በኋላ ለሚሆነው በጣም እርግጠኛ አልነበረም ። ብቻ ፣ ንብርዬ በጀ ግንነቱ ስለሚፈራ ፣ እንዲመጣው የሚላክበት አዝማች ነገሩን ሳያጣራ ተቆቀጻያም አደጋ ያጋልበታል ብሎ ነበር ተስፋ ያደረገው ። እሱን ግን ነገሩ የበለጠ ሠመረ ።

“ ቡዳምኮ በሥውርና በረቂቅ ኃይል ያሰበውን የሚሠራ ተአምረኛ ማለት ነው ! ” አለ ጋረድ አውንም እንደገና በአድናቆት ። የገብርዬ መሸፈት በሠፈሩ እንዲወራ ለቴዎድሮስ እንዲነገር ከመመካከራቸው በስተቀር ፣ የአክሊሉ ብልሃት እንደዚሁ ግልጽ ሆኖ አልታየውም ነበር ።

“ ለእንተ ለወዳጇ እንኳንስ ቡዳ ሰይጣንስ ብሆን ምንተዳዬ ! ” አለው አክሊሉ በሞቃት መኩራራትና መዝናናት እንደ መንጠራራት እየቃጣው ።

“ ሲኦል ትወርዳለሃ ! ”

“ ፈረሴን ይገር ነዋ !” እንደ ፈረስ የመሰለው፣ እርሱን ራሱን መሆኑ ጋረድ አልገባውም ።

“ ብቻ ውጊያው የሚያሠጋን ይመስልሃል !” ሲል አክሊሉን ጠየቀው ።

“ የምን ውጊያ አመጣህብኝ? ከኮረዳው ጋር ተቃቅፎ ሲያንቀላፋ ነው የምንደርስበት ። እንዲያውም እሱን ለኔ ተውልኝ እስቲ ። ኮረዳውን ሸልሜሃለሁ ፣ ለዚች ድላል ” አለ አክሊሉ ፣ ጋረድ በሚያሻሻት ልጅ ላይ ዐይኑን በቀልድ እያጉረጠረጠ ።

“ ችግሩ ገብርዬ ላንተም ሆነ ለኔ አልተተወም ።”

“ እንዴት ?”

“ ተነሕይወቱ አምጣልኝ ተብያለሁ ። ”

“ ተነሕይወቱ ? እህ - እህ - እህ ” አክሊሉ በማሾፍ እንደ መን ከትከት አለ ። “ እኛ ገብርዬን በሕይወት ስናስረክበው ፣ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ የኛን ሞንትቅላት ደሞ በሰፌድ ልናቀርብለት ! እንደዚህ ያለውን ጅል ነገር ለጅላጅሎቹ ይንገረው ።”

“ ዛዲያ ምን እናርግ ትላለህ ?”

“ ወቸው ጉድ ! ቀላል ነው ። እጁን አልሰጥም ብሎ ሲዋጋ ሞተ።”

“ ሲዋጋ ሞተ ! ” ጋረድ ራሱን እየነቀነቀ ተቀበለው ።

“ ሲዋጋ ሞተ !! ” አሉ ፣ እንደ ዝማሬ ሁለቱም ባንድነት ።

በበነጋው ጧት ፣ ጋረድ ሺህ ሠራዊት አሠልፎ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጋሪት እያስጐሸመ ከደብረ ታቦር ሲነሣ ፣ ፈረሱን ባንድ ጊዜ መውጣት አቅቶት እርካቡን እንደ ረገጠ ሁለት ሦስት ጊዜ ያህል ፣ ላይ ታች ሲል አክሊሉ ተመለከተውና ከት ከት ብሎ ሣቀበት ።

“ ምነው ?” አለ እሱም ሳይታወቀው እየሣቀ ።

“ ምን ያህል ወገብህ ዶቅ ቢያድር ነው ወንድሜ ?” አለው ። የአክሊሉ አነጋገር የቅናት ቃና አልነበረበትም ። የበቀል ዕቅዱ እየተቃረበለት ሲመጣ ወትሮ በእንደዚህ ያለው አጋጣሚ ያቃጥለው የነበረው ሙቀቱን እየጠፋለት ፣ በምትኩ አንድ ልዩ የሆነ ሥነ ልቡናዊ የመሲብ እርካታ እየተሰማው ሔዶ ነበር ። ጋረድም ቢሆን ፣ እንኳን በእንደዚህ ያለው ቀልድ በምር ቢሾፍበት ፣ ስንኳን ሙሉ ትሬታ ፣ የትሬታ ሜዳ ከማይደርስበት የመኩራራት ጣሪያ ላይ ወጥቶ ነበር ።

—3—

ለገብርዬ ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ቆይታው ከብዙ ዓመታት ወዲህ እግኙቶት የማያውቀውን የዕረፍትና የመዝናናት ዕድል ሰጠው ። ቤተ መንግሥት ለመሔድ ፣ ባለ ጉዳይ ለማነጋገር ፣ ጠያቂ እንግዳ ለመቀበል ፣ ሠራዊት ለመጐብኘት ወይም ለሌላ ጉዳይ በጧት መነሣት ፣ የዕለት ውሎውን በዓታቤ ሰዓት መመደብ አልነበረበትም ። ቢፈልግ ቀኑን ሙሉ ተኝቶ መዋል ይችል ነበር ። ነገር ግን ፣ ተኝቶ ማርፈድ ያልለመደበት ሆኖ በጧት መንቃቱ አልቀረም ።

ከግልሰት እንድ ቀን ገብርዬ ፣ ከፀሐይዋ ቀድሞ ከጐጇው ይወጣና ቁልቁለቱን ወርዶ ከፈሩው ጐን ከሚገኘው መዋት ሲታጠብ ቆይቶ ይመለሳል ። ሌላ ቀናት ከጐጇው ታዛ ይቀመጥና የጧትዋ ጀንበር በወይኒ ጋራ የደቡብ ጐን ብት እያለች ጨረርዋን በረባዳው መሬት ላይ ስትዘረጋ ፣ ሴቶች እንስራቸውን አዝለው ወደ ወንዝ ሲወርዱ ፣ ወንዶች እርፋቸውን ተሸክመው በሬዎቻቸውን አስቀድመው ወደየማሳቸው ሲያመሩ ፣ ልጆች እየተጨዋጨዋሁ ፣ እየዘፈኑና እያቈጨ ከብቶችን ወደ ጨፈ-ቀመሱ መስክ ሲነዱ በአንክሮ ይመለከታል ። በነፋሻው አየር ፣ በጸጥታው ፣ በአካባቢው ግርማ ሞገስ ይመሰጣል ። ይማረካል ። ከዚህ ፣ የቤተ መንግሥት ግርግር ሁካታና ነጋሪት የለም ። ከዚህ ፣ የግድያና የጦርነት ዜና የለም ። የሚያድምና የሚያሜር የለም ። ሁሉም የዕለት ተግባሩን ብቻ ያከናውናል ። የጅራፉ ጩኸት ከኮረብታ ጋር ሲያስተጋባ እንደ ጥይት ተኩስ ሞትን አያረዳም ። የወራሹ ሽለላ ፣ የቁጣ ፣ የንዴትና የግዳይ መግለጫ ሳይሆን በሬውን ማባበሉ ነው ። የወፎች ዝማሬ ፣ ከአዝማሪ ቁልምጫ የበለጠ ለጆሮ ይጣፍጣል ። ዕድሉ ከቴዎድሮስ ዕድል ጋር ባይጋጠም ኖሮ ሕይወቱ ይህንን መሳይ ሆኖ በቀረ ነበር ። ጥቁር ዐፈር የሚገፋው ትሑት ገበሬ ሕይወት ሳይሻል ይቀራል? የሚል ሐሳብም ይመጣበታል ። የራሱ ሕይወት የሚያውቀው ፣ ሰልፍ ፣ ትጥቅ ፣ ዘመቻ ፣ ግድያ ፣ ምርኮ ነው ። በገደሉ ቁጥር መሳቀቅ እለ ። ሲሸነፉ ደግሞ መጨነቅ ነው ። ችግር ድካምና ልፋት ቢኖርበትም ፣ ከጥቁር እፈር ጋር ሲታገል የሻከረ መዳፍ ሰይፍና ጠመንጃ እንደሚጨብጥ እጅ የሰውም የለበትም ። ሐሳብ ቢኖር ፣ ጠሉ እንዲለግስ ፣ አድባር ፣ አውድማውን

እንድትሳርክ ነው ። ዛሬያ ያንቺ ሳይሻለኝ ይቀር ነጀል ፤ ይልና ገብርዬ በመጣችነት ጀምሮት የነበረው የግብርና ሕይወት ትዝታ ያመጣበታል ።

በሠራዎታ ግርያም ይብር የታወቁትን አባቱን የሚተካ ይኖና ዐረገ መሆን እንደ ያመረ ፣ በሰው አደላልነው ከሞር ደንጋይ ኮሚኖ ቤተ ሰዎች አንዲት ቀንጃ ልጅ ያገሰይታል ። ገና ሲያያት ውክክ ያለላት በል ነክ ያለች ቀይ ናት ። የመርጥ ዕለት ፣ የሕግ ሚስቡን ተረክቦ መደ ሠራ ምባ ሲመለስ ፊስ አለ ፤ በደብረ ታቦር ላይ የቆሙዋቸው ጀጃዝማች እሸ ከርች ከመንገድ ላይ ለመንጠቅ አምባገር ያስነግሉ ። ተኩስ ይከፈታል ፣ ከሥቱም በኩል ሰዎች ይጉላሉ ። እንደ ምንም ፣ የሰው ሠፈራቸው ይፋ ርሳሉ ። በበንጋው በጳስ ውስዋ እንጻሉ ፣ መንት ሠራዊት ድንገት ይደ ርስና ይብልቅልቁን ያወጣዋል ። ከአባቱ ጋር ብዙ ሰዎች ይገደላሉ ። መንደሩ በሙሉ ይታጠላል ። ገብረ ሕይወት በናጅቱ መካከል እንዴት እንደ ወጣ ሳይታወቀው ያመልጥና ፣ የሕግ ሚስቡንና ከብቶቻቸውን ዘርፈው ሲሔዱ በሩቁ ይመለከታል ። ዋርሱን ነክሶ ፣ ደግሞ ይጋግሞ ፣ በራስ አለና በሰዎቻቸው ላይ በቀል ይምልና ወደ አሞራ ገደል ይወርዳል . . .

ከዚያ በኋላ ወደ ገብርናው ሕይወት አልተመለሰም ። እጁ ከዕ ርፍ ይልቅ ለጉራዴና ለንፍጥ የታደለ ሆነ ።

ከራሱ የጥንት ትዝታ ጋር አውን የወይኒ ገበሬዎችን የዕለት ተዕ ለት እንቅስቃሴ በእርጋታ ሲያስተውል ፣ ዕርፍ የመጨበጥ ፣ ከበሬ ጋር የመንጋገር ፍላጐት እንደ መሳብ እደረገው ። ጊዜውን የሚያሳልፍበት ሌላ ሥራ ደግሞ አልነበረውም ።

የዕለት ኑሮዋቸው በጣም ቀላልና የተወሰነ ሆነ ። ከረፋዱ ላይ ታን ጉት የኪዳን ምሕረትን ቀዝቃዛ ጠበል በመጀመሪያ አቅምላው ቁርስ ታቀርብለታለች ። ከዚያም ፣ የነረገምብ ዋልካ አምሮቷን ለመወጣት ብቻዋን ትሔዳለች ። በመገረም ፈገዙ ያያት የመጀመሪያው ቀን ብቻ ነበር ። ከዚያ በኋላ ግን አፍራ ፣ አስከትላው አታውቅም ። ትዝታዋን ሌላ እንዲጋራት የማትፈልግ ይመስል ፣ በልጅነቷ የምታውቀውን ሥፍራ ሁሉ የም ትጐበኘውም ብቻዋን ነው ። ይህ ገብርዬን አላስገረመውም ። ትንሽ ያስገረመው ሌላ ነገር ፣ ታንጉት የተወለደችውና እንደምትለውም ዐሥር ዓመት እስኪሆናት ድረስ የኖረችው በዚህ መንደር ቢሆንም ፣ የምታውቀውና የሚያውቃት ዘመድ አለመቅረቡ ነው ። ራሷም ቢሆን የሥጋ ዘመድ እንዳላት ለማጠያየቅ የምትፈልግ አይመስልም ። ገብርዬ ፣ ነገሩ ትንሽ ከንክናት ሊጠይቃት አሰበና ፣ " የሥጋ ዘመዶቼ ሁሉ በድንገት አልቀው አባ ታጠቅ ወስዶ አሳደገኝ " ብላ ነግራው ስለ ነበር ፣ አውቃቂ ትዝታዋን እንዳይቀሰቅስባት በማለት ተወው ።

ከሳምንት ያህል በኋላ ፣ ከቤቱ ያረፈበት ገበሬ ማሳ ወደሚገኝበት አብሮ ወረደ ። ለጥቂት ጊዜ አየ ። " አስቲ ! " አለና ዕርፉንም ፣ ጅራቱ ንም ተቀበለው ። ግን ሰው ኑሮውን ይመስላል እንደሚባለው ከገብር

ግው ሕይወት ምን ያህል ተለያይቶ እንደነበር ወዲያው ሲያየው ከመገረም በልዩ ተሳሃደ ። እንደ ጊዜ ፣ ምንም ያህል ጅራፍ ቢያመሃ ቢያላ ጉም በርቱ የማያመቁት ባለ ከንላቸው መሣሩን የተማከሩ ይመስል ከቀንበራቸው ሥር አንገታቸውን ላመል ያህል እያንቀሳቀሱ ግብር ይላሉ ። ሌላ ጊዜ ግረሻው ይቸኩልበታል ። በሰንት መንት ሲንቅለው ደግሞ ላይ ላዩን ይሞርበታል ። ወይ ደግሞ ቅልሙ እንደ ሰካራም ኮቴ ተወዲያ ተወዲህ ያመላነደበታል ። እንደ ሙር ሚጸ ወንዙ እልህ ተጋ ብቶ በየዕለቱ ሲጋተረው ፣ እየተለማመደው ፣ እየቀለለው ሔደ ።

የዕለት ሥራ አልቆ ሁሉም ወደ ሠፈሩ ሲመለስ ፣ ብዙዎቹ የጉረ ቤት ሰዎች እነ ገብርዬ ወደ ዐረቆብት ቤት ይመጡና ከደጅ ተሰብስበው አብረውት ሲያወጉ ያመሻሉ ። ከአባ ታጠቅ ካህ ጋር ስለ እያረጋቸው ዘመቻዎች ፣ ስለ ጉንደር ከተማና ስለ ቤተ መንግሥት ሕይወት ያለ መታከት ይጠይቁታል ፣ ያወጋሳቸዋል ፣ ያለ መሰልቸት ያዳምጡታል ። ከወንዶቹ ጥቂት ፈቀቅ ብሎ ታንጉት ከጠናር ድኳ ላይ ተቀምጣ ትፈ ትላለች ። ወይም ጥጥ ታባዝታለች ። ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ከሙሉ እን ሥቶ ከታንጉት አጠገብ የማትለየው የገበረው ቤት ልጅ ከሥርዋ ተሸ ጉማ ፣ ወይ ቅልሞሽ ትጫወታለች ፣ ወይ ተረት ስታጫውታት አፍዋን ከፍታ የሚያማምሩ በያኖቿን በአድናቆት እያቁለጨለጨች ትሰማለች ።

ገብርዬና ታንጉት ፣ ከገበረው ቤት ያረፉት በቢችው ልጅ ምክ ንያት ነበር ። ጉንደር በተነሙ በአራተኛው ቀን ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ደርሰው ፣ ድንኳናቸውን ተክለው ያደሩት ከደብሩ ጥቂት ራቅ ብሎ ከሚ ገኘው ገላማና ይልዳላ ሥፍራ ላይ ነበር ። ድንኳኑ የማን መሆኑ እንደ ታወቀ ፣ የታጠቅ ጦር አዝማች ገብርዬ መጣ የሚለው ወሬ እንደ ቋያ እሳት ምስት አራት ሰበካ የሚሆን አዳርሶ አድሮ ናሮ ፣ ጭት ቤተ ክርስቲያን የመ ጣው ሕዝብ ብዛት ታቦት የሚነግሥበት ዓመት በዓል ያህል ሆነ ። ቅድ ስቱና ቅኔ ማኅሌቱ በተሳላሚ ብዛት ቢጨናነቅም ፣ ለገብርዬ በሰሚን በኩል ፣ ለታንጉት በደቡብ ከቅድስቱ ሥፍራ ተሰጥቷቸው ሰዉን ከአ ጠባባቸው ገለል የሚያደርግ አስተናባሪ ተመድቦላቸው ነበር ። ገብርዬ እንደ ሰጪ ከሰው ጋር መጋፋቱን እንጂ ይህንን አልፈለገውም ነበር ። የደብሩ ገበዝ ግን ፣ ጨርሶ አይሞከርም ብለው ስላሰቸገሩ ፈቃዳቸውን መፈጸም ግድ ሆነበት ። ሙሉ ማኅሌት ቁቆመ ። የክቱ ልብስ-ተክህና ወጥቶ በሰባት ተቀደሰ ። በዚህ ሁሉ መካከል የሰው ዐይንና ሐሳብ ያተኮረው ግን ፣ ከቅዳሴውና ከጸሎቱ ይልቅ በሁለቱ እንግዶች ላይ ነበር ። ቅዳሴው አልቆ ፣ " ሑሩ በሰላም " እንደ ተባለ ገብርዬና ታንጉት ወደ ድንኳናቸው ሲመለሱ ፣ ብዙው ሰው እንደ እቺቢ ግር ብሎ ተከተላቸው ። ከዚያም እጅ እየነሣ ክብ ሠርቶ በመቆም ይመለከታቸው ጀመር ። ገሚሱ እጅ ነሥቶ፣ዐይኑ እስቲጠግብ አይቶ፣በሆዱ የታንጉትን ውበት፣የገብርዬን ጉብዝና እድንቆ ሲሔድ ሌላው ይተካል ። ረዘም ላለ ጊዜ ቁሞ የሚቆየው አብዛኛው ለጌታ የማደር ሐሳብ ያለው ጉረምሳ ነበር ። ገብርዬና ታንጉት

ከሌሎቹ ነጥለው አላስተዋሉትም እንጂ ፣ አንድ መካከለኛ ዕድሜ ያለው ገበሬ ዘጠኝ ዓመት የሚሆናት ሴት ልጅ ይዞ በመቅረብ እጅ ከነሣ በኋላ ፣ እሱ ለመሔድ ሲል እቢ እጅዋን እዬጐተተች እምቢ ስትለው ረዘም ላለ ጊዜ ቆይቶ ነበር ።

በሰው መከበባቸው ገብርዬን ትንሽ አስጨነቀው ። ተገናንቶ ማረፍ አልቻለም ። በሕዝብ ዐይን የታፈነ መሰለው ። ገርነታቸው ደግሞ ደነቀው ። በእነሱ ቤት እኔን ከሰው የተለየሁ ፣ ከሰው በላይ የሆንኩ ግድ ረጋቸው ነው እኮ እለ በሆዱ ።

ወደ ማምሻው ገደማ ፣ የወይኒ ኪዳነ ምሕረት ሰበካና የአካባቢው ሰው ፣ እጅ መንሣቱ ፣ በአድናቆት መመልከቱ ተዳርሶት ጕልማሳው ክብት ለማስገባት ፣ ሴቱ ራት ለማስናዳት ወደየመንደሩ ሲበተን ሠፈሩ ሞር አለ ። ለመጀመሪያ ጊዜም ገብርዬና ታንጉት ከድንኳናቸው ውጭ ምጣንፍ አዘርግተው በመዝናናት ተቀመጡ ። ባይሠሩም ድካም ተሰምቷቸው ነበር ። ጃኖ ጋቢ ያደገደገ አንድ ሰው ከአንዲት ልጅ ጋር ድንገት ከፊት ለፊታቸው መቆሙን ያስተዋሉት በዚህ ሁናቴ ላሉ ነበር ። ገብርዬና ታንጉት ፣ ትንሽ ግራ ገብቷቸው እርስ በርሳቸው ተያዩ ። ዕር ጻታ ጠያቂ ደሃ ቢጤ ነው እንዳይባል አለባበሱና ግርማ ሞገሱ ያስተባብላል ። እጅ አነሣሡም የትሕትናና የአክብሮት እንጂ እንደ ለማኝ የመለማመጥና የመሽቆጥቆጥ ዐይነት አይደለም ። ቀኑን ሙሉ ሲንጋጋ እንደ ዋለው ጕልማሳ ሁሉ ለማየት ብቻ የመጡም አይመስሉም ። ጉዳይ እንዳላቸው አቀራረባቸው ያስታውቃል ። ለአዛውንቱ ሰላምታ አጸፋውን በመመለስ ገብርዬና ታንጉት ከአቀማመጣቸው ቀና አሉ ።

ሰውየው ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራረገና ፣ ‘‘ከድፍረት አትቁጠሩ ብኝና ! ላስቸግራችሁ ። ልለምናችሁ ጌታየ ፣ እመቤቱ !’’ አለ በረጋ ጨዋ እንደበት ከወገቡ እየታጠፈ ። ልጅቷ የተጨነቀች ይመስል ትን ንሽ መዳፎቿን እያፋተገች ዐይንዋን በሰውየው ፣ በታንጉትና በገብርዬ መካከል ታንከራትታለች ፣ አብዛኛው ጊዜ የሚያርፈው ግን በታንጉት ላይ ነበር ፣ ጉዳዩን እስኪናገር ጠበቁት ።

‘‘ እሽከር የያዛችሁ አልመሰለኝም ። ፈታዳችሁ ቢሆን ተኔ ቤት ዕረፉ ። እልፍኝ አዳራሽም ባይሆን ለመጠለያነት አይገድም ።’’

‘ሰውየዉ በራሱ ሙሉ እምነት የሚሰማው ፣ የሰውነት ዋጋውን ያወቀ መሆን አለበት ’ ሲል ገብርዬ አሰበ ።

‘‘ ዛሬያ እኛ ታንተ ቤት ባረፍን ፣ አንተን እናስቸግራለን እንጂ መች እንቸገራለን ? ’’ አለው ።

‘‘ ለኔ ደስታና ክብር ነው ጌታዬ ’’ አለ ገበሬዉ ድግድጉን እያስ ተካከለ ።

‘‘ አይ ! ሰውን ማስቸገር ምንም አያስፈልግ ። ተዘሁ መሰንበቱን ነው የምንመርጠው ። ስላሳብህ እግዜር ይስጥህ ።’’

‘‘ አይሆንም ። እንደማመጣችው ላይኔ አበባ ቃል ገብቼላታለሁ ።’’ አንጋገሩ የልመና ሳይሆን የማረጋገጫ ዐይነት ነበር ።

የተዘባነነው መጣ !‘‘ ምንናት ያይኔ አበባ ?’’ ሲል ገብርዬ ጠየቀ ፣ በመገረም ንግግሩን ትንሽ ስለት ሰጥቶ ።

‘‘ ይች የኔ ልጅ ናታ !’’ ቁልቁል እየተመለከተ ራሷን በእጁ ያሻ ሻት ጀመር ።

ልጅቷም በማባበልና በመለመን አኳኋን በሁለቱ እንግዶች ላይ የሚያምሩ ዐይናቿን አቁለጨለጨች ። ሁለቱም የመገረም ማት እንደ መጣባቸው ተገንዝቦ ፣ ‘‘ምናልባት ታሪኳን ብንሰራችሁ ነው የሚሻለው’’ አለና ሳይጋበዝ ከአጠገባቸው ተቀመጠ ። ልጁንም በክንዱ ሳብ አድ ርጎ ከጉኑ አስቀመጣት ። ከዚያም በእርጋታ አሜወታቸው ።

ያይኔ አበባ እንዲት ልጁ ናት ። ገና ከአራስ ቤት ሳትወጣ እናትዋ ከሞተች እነሆ ዘጠኝ ዓመት ሊሆናት ነው ። ሌላ ሚስት አላገባም ። የቤት ፍቅር ምንጩ ስለ ደረቀበት ፣ ልጁን የእንጀራ እናት እጅ ግላየት ስለማይፈልግ፣ ሌላ ሚስት የማግባት ሐሳብ ጨርሶ የለውም ። እግዜር ይመስገን ፣ አገልጋይም ሀብትም አለው ። ግን ዕድሜ የሚለምነው ለልጁ ሲል ብቻ ነው ። የርሷን እበባ ፣ ወግ ማዕረግ ለማየት እንዲበቃ ብቻ ! ለሌላው ግድ አልነበረውም ። ዛሬያ ጪቱን ቤተ ክርስቲያን ይዟት መጥቶ ነበር ። ከቤተ ክርስቲያን ሲወጡ በእመቤት ታንጉት ላይ ዐይኗ እንዳረፈ መላ ሰውነቷ ይለዋወጣል ። በጣም ትደሰትና ፣ ‘‘ ያች ፊትዮ ማናት ?’’ ብላ ትጠይቀዋለች ። ከነገራት በኋላ ፣ ‘‘እናቴን መሰለችኝ ። ወይ እናቴ ብትሆንልኝ ?’’ ትልና ትካዜ ይገባታል ። ይቅላት እንደሆነ በማለት ከሰዎቹ ጋር ወደ ድንኳኑ በመምጣት በድጋሚ እንድታይ እድ ርጎ ወደ ቤት ይመለሳሉ ። ግን ትካዜው ብሶባት እየቆዘመችና እያለቀ ሰች ምላ ሳትበላ ዋለች ። እንደ ምንም አባብሉ ምክንያቱን ቢጠይቃት ፣ ከቤትዬዋ ዘንዳ ሒዳ ካላደረች ወይም ቤትዬዋ ከቤታቸው ካልመጣች ሙቼ እገኛለሁ ብላ ትንሰቀሰቅ ገባች ። ነገሩ ኦንዓዳ ቢሆንበትም መቸም እንድ ልጁ ናትና እንደሚያመጣቸው ቃል ገብቶላት ፣ እህል ቀምሳ እንዞ ሊጠይቃቸው መጣ ። ታሪኩን ሲጨርስ ለጥቂት ጊዜ ያህል ምስ ቱም ዝም አሉ ። ዐይኔ እበባ መልኩን የምትጠብቅ ይመስል ዐይኗን በታንጉት ላይ ትክል አድርጋ ቆየች ።

‘‘ነይ እስቲ !’’ አለችና ታንጉት በማቅማማ እኳኋን እጅዋን ዘረጋች ። ‘‘ ለመሆኑ እናቷ እኔን ትመስል ነበር ? ’’ ስትል ጠየቀች ። ያይኔ እበባ በክንፈርዋ ላይ የማፈር ፈገግታ እየተጫወተ ተነሥታ ተጪጋች ።

“እረ እስተዚህም እትመስልም ። ግና እርሷም መልክ መልካም ነበረች ። ” ሰውዬው የሚስቱን ፊት በሩት የሚያይ ይመስል ፣ ዐይናቹን ወደ ግዶው የወይኒ ተራራ እነጣጠረ ።

“እስቀድመህ ለልጅ ታል መስጠትህ ደግ አልነበረም። እይመስል ህም ፣ ” አለ ገብርዬ ። ጥያቄም ምክርም ነበር ።

“ምን ችግር አለው ፣ ተወደደችን ተኔው ጋር ተዚህ ትሰንብታለች ፣ ሁሊታችሁ ተተስማማችሁ ደሞ በኋላ ይዘናት እንሔዳለን ” አለች ታንጉት ለጠቅ አድርጋ ።

ሰውዬው የታንጉትን የመጨረሻ መልስ ዘሱ ፣ “እየ መቸም እመ ቤቱ የዚሁ የእኛው አገር ናቸው ስለሚባል እምቢ አትሉኝም ብዬ ነው ። ደሞም አባ ታጠቅ ካሣ ፣ ገበሬ ባላገር ይወዳል ። ተነሱ ጋር ይበላል ፣ ይጠጣል ፣ ተቢታቸውም ይውላል ሲባል ስለምንሰማ ነው ። ዛዲያ ምን አለበት ፣ እኔም እንደ ዐቅሜ ቤት አለኝ ብዬ ነው የደፈርኩት ” ሲል ተናገረ ።

“እረ ቀላል ነው !” አለ ገብርዬ ፣ እጁን በማወዛወዝ ። “ታንጉት እንዳለችው ልጅቱ ተኛ ጋር ትሰንብት ።”

“አይ እሱማ እንዴት ተደርጉ ” ከልጁ መለየት ሞት መስሎት መንፈሱን እንዳሸማቀቀው ከፊቱ ላይ ይታወቅ ነበር ።

“ዛዲያ እንዴት ይሁን ?” ተብሎ ተጠየቀ ።

ሰውየው ግን ፣ ታሪኩ ልባቸውን እንደ ነካው በመረዳት የእሽታ ቃል ካፋቸው ሳይወጣ ፣ “እንዳልኩት አዳራሽም ባይሆን ፣ ለብቻችሁ የምት ሆን ገለልተኛ ማረፊያ አለችኝ ” የሚል መልስ ሰጣቸው ።

የአባትዬውን ሞንቀት ፣ በጉጉትና በተስፋ የሚቁለጨለጨውን የልጅቷን ዐይን ሲመለከቱ እምቢ ማለት አልቻሉም ። ድንኳናቸውን ልጆች እንዲጠብቁ አድርገው አብረውት ሔዱ ።

በመሔጻቸው ቅር አልተሰኙም ። ማረፊያው ጉጀ ከደንኳናቸው የተሻለ ምቾት ነበረው ። ከበለጡ ሌላ አንድ አገልጋይ ተመደበችላቸው ። በምገብም በመጠጥም የሚጉድል ነገር አልነበረም ። የታንጉትና ያዩኔ አበባ ፍቅርም የእናትና ልጅ ዐይነት ሆነ ። ታንጉት ጧት ተነሥታ ቤተ ክርስቲያን ስትሔድ ፣ በጓሳ አንጻንድ ነገር ስታዘጋጅ ፣ ወይም ዋዋ ስት ፈትል ሁሉ ያዩኔ አበባ ከአጠገብዋ አትለይም ። የባጥ የቆጡን የልጅ ተረት ታጫውታታለች ። ወይም ደግሞ ፣ “እትዬ ታንጉት የላሚ በራን ተረት ንገሪኝ ” ብላ ለስንተኛ ጊዜ እንደ አዲስ በጉጉት ታዳምጣለች ። የምትለያት አምሽታ ግታ ለመኝታ ወደ አባትዋ ስትሔድ ፣ ሌላ መን ደር ስትላክበአንደ ደንገተኛ ስመታ ልታስደስታት ስታስብ ብቻ ነው ።

ተደብቃ ወደ ሜካ ትሔድና የሚያምር የመሰላትን አበባ ፣ የሚማፍጥ የመሰላትን ፍራፍሬ ይዛላት ትመጣና ፣ “እትዬ ታንጉት ይች አበባ እን ቺን ስለምትመስል አመታሁልሽ ” ትላታለች ። ከስመታው ሌላ ያዩኔ አበባ ኮልታፋ አነጋገር እንደ ግሩም ዜማ ይጥማታል ። የእናትነትን ጣዕም ፣ የእናትነትን ተስፋ ይበልጥ ያላድርባታል ።

በዚህ የሚያዝናና ደስ የሚያሰኝ ቆይታቸው መካከል ፣ ገብርዬ ለአባ ታጠቅ ያለግሳወቁ ጉዳይ በመጀመሪያው ሳምንት አላሳሰበውም ነበር ። እንዲያውም ጊዜው ሳይታወቀው ነው የበረረበት ። በሁለተ ኛው ሳምንት ላይ ወልፎ ወልፎ ከነከነው ። በሦስተኛው ሳምንት ኪዳነ ምሕረት የምትውልበት ሰሞን ስለነበር ፣ ምናልባት ታንጉት ግስቀደስ ብትፈልግ ከዚያ በኋላ እንነሣለን ብሎ በመገመት ለጊዜው ችላ አለው ። በኪዳነ ምሕረት ግግሥት ፣ “እንግዲህ እምርትሽም ሳይቢቃው አይቀ ርም ፣ ታስፈለገም ለስንት ያህል እንይዛለን ፣ እንነሣ እንጂ ” ቢላት የሰጠችው መልስ ፣ “ የምትነግሙው የዛሬ ወር ነው ። ለዚህ ተቢቃው ተዚህ ድረስ መጥቼ ፣ ስለት ሳላስገባላት ፣ ዝክር ቢጪ ሳላደርግ ልሔድ ነው ? እህ !” የሚል ነበር ።

“ ... ዛዲያ የዚህ የዚህ መጀመሪያ ደብረ ታቦር ደርሰን ብን መጣ አይሻልም ነበር ? ምን አቻኮለን ! አባ ታጠቅስ ምን ይላል ?” ገብርዬ ጥቂት እንደ መበሳጨት አለ ።

“ ምን እንዳይል ነው አባ ታጠቅ ? ተሚሽትህ ጋር ለምን ጠበል ሔድክ ? ለጠበል ይገርህ መምጣቷን ተምሥራቹ ጋር ስንግረው ደስታው ንም አይችለው ። ስለ ቀደምከው እንዳያቱና እንጂ !” ስትል በቀልድ መልክ ሕሊናዋ ከውስጥ ቆንጠጥ እያረጋት ።

“ መጀመሪያ ፣ ደብረ ታቦር ብንሔድም ትርፉ መንገድ መመታት ነበር ። ቀደም ብለን መምጣታችንስ ምን ጉዳን ? ላንተም ዕረፍት ሆነ ልህ ። ጠበሉ ተስማማህ ። የረሳኸውንም እርሻ ይዤው እየለመድክው ሔደክ ።”

ታንጉት ፣ እስክ ኪዳነ ምሕረት ንግሥ ለመቆየት መፈለግዋ ክል ብዋ ቢሆንም ፣ ለይታ ልታውቀው ያልቻለችው ፣ ከወይኒ እንዳትወጣ እንደ እናት ጉያ ምቾትና ሙቀት የሚሰብ እንዳች ውስብስብ ስሜት ደግሞ እያደረባት ሔዶ ነበር ። እንደ እናት ከምታያት ከወይኔ አበባ ጋር መሆን ፣ በግሳፀንዋ ውስጥ ላለው የራሰዋ ልጅ ደኅንነት እንደ ከታብ የሚበጅ ፣ ወይም ለእናትነት ለመብቃቷ የተምሳሌት ማረጋገጫ መስሎ ይሰማታል ። ሌላው ደግሞ ፣ የሕሊናዋን ወቀሳ ለመከላከል የተፈጠረ ስሜትም ይሁን ፣ ስለ ገብርዬ የልጁ አባትነት የሚመላለስባት አንል ተስፋ ነው ። ከአምባ ጊዮርጊስ ተመልሳ ከገብርዬ ጋር ግንኙነት በምት ፈጽምበት ጊዜ ሰንኳ ፣ “ ግን ያውታል ! እንዲጋጣሚ የርሱ ይሆን ይሆ

ናል" በትል ራሷን እባብላ ነበር ። አውንም ፣ ከተለመደው የቤተ መ
ግሥትና የወር ሠፈር ግርግር ተለይተው ሁለቱ ብቻቸውን ሲሉ ንርስ ከ
ሳቸው ብቻ በመተሳሰብ ፣ በወይኒ መቆየታቸው በእንዳች ተአምር ለጊ
የንብርቱ ያጸርገዋል የሚለው ተስፋ በውስጠ ሕሊና ይሰማታል ። ያን
ንያት እታገኘለትም ። ብቻ እንዲው ይሰማታል ። ስለዚህም የተቻለው
ጊዜ ያህል ወይኒ መቆየት ትፈልጋለች ። እንደማይሆን ታውቃለ
እንጂ ፣ እንደርሷው ሁሉ የልጅዋም እትብት ወይኒ ቢቀበርላት ትመ
ነበር ፣ የእናቷ ዘመዶች ሁሉ እትብት በተቀበረበት ።

" እና ምናለበት ትንሽ ብንቆይ ?" አለችው የራሷን ቅሬታ ተ
ልክታ ። " ታለአሁን እንኳ እስተዚህ እስቸግሬህ እሳውቅ ?" እ
ነቷን ነበር ። ታንጦት ባሏን የምታስቸግር ሚስት አልነበረችም ። እር
ሱው እራሱ እስቦ ካልሆነ በቀር ፣ ተም ቀት መጣ ፣ ፋሲካ ደረሰ ፣ ቅዱ
ዮሐንስ ተቃረበ ፣ የባሕር ማዶ ሐር ቀሚስ ገዛልኝ ፣ ጌቶ እምጣልኝ ፣
የሠርቅ ጌጥ አሥራልኝ ብላ መጀታው አታውትም ። እንደ አንዳንዷ
ዘመትር ዘሎ የሚሔድ ሚስት ፣ ቀንታ የምትጨቅጭቅ ፣ አስቀኒ
የምታቀርብ ፊት አይደለችም ። አባ ታጠቅ ሲድሩዋት ፣ " ተቀበ
ለኔ እንደ ሆነችው ፣ ሚሽትም እንጉም ውኃሰት እንጂ ፣ ወንድሜን ብ
ስቸገረው ፣ ብታስከሬው ወዮልሽ !" ሲሉ የመከሩዋትን እንዳላንደፈ
ንብርቱ ያውቀዋል ።

" እሺ እንዳልሽ እንቆያለን !" አላት በማቆላመጥ ስርጉዳቷ ላ
ቆንጠጥ እያደረገ ። መልኳ የርግብና ውበት እየደረበ ሔዶ ነበር ።

በዚህ አኳኋን ፣ እንድ ሳምንት ፣ ሁለት ሳምንት ፣ ብዙ ሳምንታት
ሆሉ ። ንብርቱ ፣ ወደ ደብረ ታቦር ሰው ለመላክም ቢሆን ነገ ማልጀት
ሲል ፣ የአባ ታጠቅ የትጣት መልክተኛ ቀድሞ ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ደረሰ ።

—4—

በጎንር ግቢ አራት ሰዘካው የወይኒ ኪዳነ ምሕረት አዋሳኝ የሆነው
የተከለ ያይማኖት ታቦት የሚነግሥበት ዓመት በዓል ስለሆነ ፣ በሁሉም
ሰበክሎች የሥራ እንቅስቃሴ አይታይም ። አብዛኛው ሰው ወደ ተክለ
ያይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሔዶ በዚያው በየማኅበሩና በየዝክሩ ታድሞ
ስለዋለ ፣ የወይኒ ኪዳነ ምሕረት መንደርኞ በአብዛኛው ጭር ብሎዋል ።
ንብርቱና ታንጦትም በአካባቢው የታወቁ ምስት አራት ሰዎች መጥተው
ጠበል እንዲቀምሱላቸው ጠይቀዋቸው ነበር ። አክብረው የሚወሩ
ቸውን ሰዎች ለማስደሰት ስትል ታንጦት መሔዱን ባትጠላውም ፣ እን
ዲያውም ብትወደውም ፣ ንብርቱ ግን ስንኪን በዓመት ንግሥ በየዝ
ቡቱ እንደ ትንግርት መታየቱ ስለሚቀረው ፣ ብቻዋን መሔዱም ጥሩ
ስላልመሰላት አብረው ከቤት ውለዋል ። ታንጦትና ያይኔ አበባ ፣ ከሚሄ
ዘመትሩት ታዛ ሥር ተቀምጠው ቡን ከማሽላ ቆሎ የበሶና ቁርበ ጋር

ቀርበ ተዘናንተው ይጨዋወታሉ ። ያይኔ አበባ አውን ንብርቱንም እየ
ቀረበችና እያተሰማመጀች ስለሔደች ፣ ተረት እንዲነግሯት መወሰች ጀም
ራሷች ። ንብርቱ በሕሳንጎቱ የሰማውን ተረት ከዚያ በተረው መልሶ
ያጫወተው ልጅ ስለልነበረ ፣ ሐሳቡም በአብዛኛው ፣ በደሩ ከሰደሩ በሚ
ፋጭበት ፣ ሕይወት ከሕይወት በሚጋጭበት ፣ ጀግንነትና ሞት በሰፈ
ነበት የወር ሚሊ ትዝታ የተሞላ ስለሆነ ፣ ለልጅ የሚሆን ገራ ገርና እስ
ደናቂ ተረት አልመጣለት እያለ ይቸገራል ። " እኔ ግሩ ተረት አላው
ቅም ያይኔ አበባ " ይላታል ። " ግደልም ያንተ ተራ ነው " ብላ ትመይ
ቀየበች ። ራማተር ፣ አንዱን ከሌላው ቀጣጥሎ ያጫውታታል ። በዚ
ህም ወቅት ፣ " አውን ግ ይሙት እንደዚህ ያለ ተረት አለ ? " በትል
ታንጦት እያፈዘቸበት ስለ አንድ ሰንሩ ጅብ የፈጠረውን ተረት ለወይኔ
አበባ በግውጋት ላይ ነበር ።

ይሔይ በቅበቶ ብለ ቀዝቃዛ አየር ይነፍሳል ። ከቤት ገር የዋሉና
የናታቸውን ጡት ለመጉረስ የተቻኮሉ እምቦሳቸች ጥሪ ያሰማሉ ። ተሳ
ራሪ መልስ ከዚህም ከዚያም ይሰማል ። በዚህ የተረጋጋና የተፈጥሮ ከን
ዋኔ መካከል ከሩቅ የጓንቱን ጥግ ይዞ እንድ ነጭ ነገር የሚበር ወይም የሚ
ሸከረከር ነቁጥ መሰሉ ወደ እነርሱ አግጣጫ ሲመጣ ተመለከቱ ። እየ
ቀረበ ሲሔድ የሚንቀሳቀሰው አካሉ ለየ ። የሚርገጥ ሰው ነበር ። ከመንደ
ራቸው ጓንት ሥር ሲደርስ ከሚሳው ውሀተ ንብቶ ጠፋ ። ንብርቱ ጨዋ
ታውን ባያውርም ፣ የአጓኝ ጠረን በሩት እንደሚሰማው አውሬ ፣ የዘ
ወትር ዘመቻ ባለደረበት የጉንታቱ ልምድ ጀርውን እቅንቶ ወይኑን ከመ
ዲያ ወዲህ ወርወር እያደረገ ይጠባበቅ ነበር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ
ባለቤቱ በሩጫ እያለኾለኽ ከተፍ አለ ። ውሎም ከሙ አለ ። በድንና አለ
መሆኑ ግልጽ ነበር ። ጫን ጫን ይተነፍሳል ።

ያይኔ አበባ ፣ " አባብቡ " ስትል ተመርውራ ከመገቡ ላይ ተጠ
መጠች ። በዝክር ወይም በማኅበር ላይ እምቁባር ተነሥቶ ከሰው ጋር
የተጋጨ ወይም እደጋ የደረሰበት መስላቸው ።

" ጌታዬ ! ጌታዬ ! ቶሎ ቢነሙ ይሻላል !" አለ ገበረመ ካለ ወት
ርው ከሚቆረረጥ ትንፋሹ ጋር አትላቱ እየተወራጨ ።

ንብርቱ ፣ ግራ ንብቶት ዝም ብሎ አስተዋለው ።

" የአስተናጋጅ ይውሳ ስም አያነሙኝ ። በእምላክ ፊትም አያነ
ጠይቁኝ ነው የምሉት ! ቶሎ ይሒዱልኝ ተዚህ !" የገበረመ እነጋገር
የቁጣ ትዕዛዝ የመሰለ ነበር ።

" ምን ?" ንብርቱም ላይታወቀው በቁጣ ወይነት ሥሣ ብሎ
ጠየቀ ።

'ለምንን ነው እገጂ ለምንነው አልመጣንም ፣' የሚል ትዝብት እየ
ተሰማው ።

" ይነሙና ይሒዱልኝ ነው የምሉት !"

“ ምን ተፈጠረ ?” ገብርዬ የሚወደውና የሚናገረው ወዳጁ ሰውዬው እብዲል፡ በሚል እምለክት ገበረውን ከላይ እስከ ታች ሙው ።

“ ተፈጥሮዋል ! እዎ ሞር ዘሞተብዎታል !” አለ ገበረው በሚ ትም በአእትም ።

“ የምን ሞር ?” የገብርዬ እንጋገር ከተያቂ ይልቅ የመገረም ነበር ።

“ የንጉሥ ሞር ! እንደሚባለው ወደዚህ የመጣችው በቴዎድሮ ላይ ጀፍታችው ነው አሉ ። በመጀፈትዎ ባልሰማንም እንግደነታ ሁን አክብራለው ። እኔው ለምናችው ፣ እኔን እምናችው ባረፋችውበት ቤቴ ውስጥ አትያዙም ።”

ገብርዬ አልመለሰለትም ። በሥውር እጅ ድንገት እንደ ተኩሲ ያህል ክት ብሎ ጣቀ ። ያጣቀው መጀፈቱ ነበር ። ራሱ ላይታወቀው ጀፍ ይሆን? የቁም ቅዠት ነው ? ወይስ ሕልም ? ይህ የዋህ ገበረ የዝክር መ ከራሱ ላይ ወጥቶ እያስቀባዥረው ይሆን? ሁናቴው ግን አይመስልም ። መልሱን የሚያገኝበት ይመስል ወይኑን ከሰውየው ወደ ወይኔ አበባ ፣ ከወይኔ አበባ ወደ ታንጉት ፣ ከታንጉት መልሶ ወደ ሰውየው እንከራተተና ፣ “እርግጠኛ ነህ ?” ሲል ጠየቀ ። “ ያው !” አለ ሰውየው እጁን በግወራጨት እያመለከተ ፣ “ ጀፍታ አሳዳሪ ነህ በግለት ከፈታቸው ያነጉትን መንደር ሁሉ እንደ ቂያ እሳት እየለበለቡ በመገሥገሥ ላይናቸው

ገብርዬ ፣ ከተቀመጠበት ሳይነሣ እንገቱን ሰገግ አድርጎ በሩት ተመ ለከተ። በርግጥም ወደ ጭልጋ በሚወስደው መንገድ አግጣጫ ምስት እራት ላይ ጪስ ወደ ሰማይ ሲወጣ ይታያል ። ስካርም ፣ ቅዠትም ፣ ሕልምም አልነበረም ። ገብርዬ ከመገረሙ የተነሣ ፣ “ ለመሆኑ እዝግቹ ማነው አሉ ?” ሲል በትዝብት እኳኋን ጠየቀ ።

“ የቴዎድሮስ የአጉታቸው የደጃች ከንፉ ልጅ ፣ ልጅ ጋረድ የሚ ባለው ነው አሉ !”

“ አሃ ! ነው ! ” አለ ገብርዬ በምፀት ፣ ድምፁን ከፍ አድርጎ ። ተመ ግሪ ግብራሪያ አላስፈለገውም ። የጋረድ ስም መጠቀሱ ብቻ ነፍሩን ከሥተለት ። ቴዎድሮስን በሚራ አወናብደው በሐሰት አሳምነውታል ። ግ እንዴት በቀላሉ ሊታለልላቸው ቻለ ? ቢጠረጥረውስ ሳያረጋግጥ እን ዴት ሠራዊት አዘመተበት ? ደግሞስ ወይኒ መምጣቱን በምን ዐወቁ ! እሱ ራሱ የሚሔድበትን የነገረው ሰው የለም ። ምናልባት ታንጉት የነገረችው ቢኖር ወይዘሮ ደብሬ ናቸው ። እሳቸው ነገሩዋቸው ?ወይስ በሌላ መንገድ ደረሱበት ? እነ ጋረድ ለሚራቸው ሲሉ እስከ ጓጻ ያሉ ንፋሱ ግለት ነው ? አበስኩ ገበርኩ ! በሕሊናው አግተበ ። ጠቅላላው ከገውን እንዴት እንደ ተቀነባበረ ለመገመት ሲያሰላስል ፣ ታንጉትን

ሰንኳ ሊያናገር ዝም ብሎ ረዥም ተቀመጠ ። እሷም ነገሩ ጸብ ይኖ ባት እንደሆ እንደ ተዘጋ ያህል ግራ ግራውን እየተጣ እየተመለ ከተች ከተቀመጠችበት አልተንቀሳቀሰችም ።

“ጌታው ቁጭ ብለው ነገር ለማስላት ጊዜ የለዎትም ። የዝመተብዎ መራዊት እያተታረበ ነው ፣ በኋላ በኋ እንላያማርሩ !”

የሰውዬው ኮስተር ያለ እንጋገር ፣ ገብርዬን ከሐሳብ ሰመመኑ አነ ቃው ። የመጀመሪያ ቅጽበታዊ ስሜቱ ወደ ድንኳኑ ሰመግሥገሥ ታጣው ። ተድሞውንም ቢሆን ወይ ከድንኳኑ መቆየት ወይ ድንኳኑን መንቀል እንደ ነበረበት እውን ተሰማው ። በገበረው ግረፊያ ለመቆየት ከሐሳ በኋላ ድንኳኑን ለመንቀል አስቦ ነበር ። ግን ገበረውና ሌሎችም የመን ደሩ ሰዎች ፣ “የአባ ታወቅ ሞር አዝማች ድንኳን ለመፈራቸን ከብር ምክ ነውና ይቆይልን ፣ ልጆች በየተራ ይመብቁታል” ብለው ስለ ለመኑት ተመው ። እሁንም ከአንድ ገበረ ጉጆ ተደብቆ የተገኘ ከሚመስልበት በራሱ ደንኳን ፣ የጣለውን ጎጡ መውደቂ የተሻለ መሰለውና ፣ በድንገት ተወራጭቶ በመነሣት አሻገር ተመለከተ ። ድንኳኑ የተተከለበት ገላጣ ስፍራ በግልጽ ይታያል ። ገና ወይኑን እንደ ተከለ በአሳባቢው ጪስ ተነሣ ።

“ አታጠሉት ድንኳኔን !” አለ ገብርዬ ከራሱ ጋር የሚነጋገር በሚ መስል አኳኋን ። ዕንባ ተናነቀው ። ሬቴን በመጻፉ ጀፍና አንገቱን ደፉ ። ታንጉት ደፉ አሰችና በትክሻው ዕቅፍ አደረገቸው ። ሰውነቱ በንዴት እንደ መንቀጥቀጥ ሲል ይሰማት ነበር ። ይህ ሁሉ የመጣው በርሷ ምክ ንያት መሆኑን በግወቅ ፣ የምታስበው ፣ የምትናገረው ፣ የምትይዘው ነገር ጠፍቷታል ። ለግጽናናትና ለግደፋፈር ስንኳ እንደበቷ ተዘጋባት ። ገብርዬ ግን የቋጣ ስሜቱ ሁሉ የተሰበቀው በጋረድና በአክሊሉ ተንኮል ላይ ስለ ነበር ፣ በታንጉት ምክንያት የመሆኑ ጉዳይ ለጊዜው በሐሳቡ አልመ ጣም ። ባልና ሚስቱ በዚህ ዐይነት እንደ ቆሙ ፣ ሰውየው ወደ ጓሮ ሔደና ከጥቂት ጊዜ በኋላ በቅሎ እየሳበ መጣ ።

“ ለጊዜው በጋጥ ያለችው የኮርቻ በቅሎ ይህች ብቻ ናት ። ተታች ከመስኩ እንድ የሚጎት ከብት ነበረኝ ። ግና እንደምታዩት ረልጌ እስ ታመጣው ድረስ የሚያቆዩን አልመሰለኝም ። በዚችው እንደ ምንም ተቸገሩና ባመቻችሁ ጊዜ ትልኩልኛለችሁ ” አለ ገበረው በመቸር ረንታ ፣ ያስቸገራቸው ይመስል ይቅርታ በመጠየቅ መልክ ።

የልብስ ከረጢታቸውን ሳይዙ ፣ ገብርዬ ከበቅሎው ሲወጣና ታን ጉትን ከኋላው ሲያፈናጥጥ በንዴት ከመኮማተሩ የተነሣ እንደ ደመ ነፍስ ነበር ። ሌላው ቀርቶ በቅሎዋን ከደብረ ታቦር በሰው ከመላክ እነ ጋረድ አልዘረፉዋቸው እንደሆነ ሰውዬው በምትኩ የእርሱን ከብቶች መውሰድ ፣ ወይም ደግሞ በትንሽ ኮረጆ ከያዘው ገንዘብ ዋጋዋን በብር መክፈል እንደሚቻል አልታሰበውም ። በቅሎዋን በኃይል መጭ አላ

ትና ስትሸመጥጥ ሁለት ሦስት ጊዜ ወደ ገበሬው ቤት ተገላመጠ ። ታገ
ጮት ፣ በሁለት እጅዋ ወገቡን እንደ ያዘች ወደ ኋላ ዙራ የወይኔ አበባ
በወይንዋ ለመሰነባበት ሞከረች ። ግልቀስ ስትጀምር አባቷ ዐቅፎ ቤት
ይዟት ገብቶ ስለነበር ከቆመችበት ቦታ አጣቻት ።

እነ ገብርዬ ወደ ምዕራብ ከታጠፉ በኋላ ፣ የጋረድ ሠራዊት እልፍ
ረሰበትም ብለው በገመቱት ቁጥጳጦ በበዛበት ፈፋ ለፈፋ ከተጓዙ በኋላ ፣
እንደገና ፈታቸውን ወደ ምሥራቅ መልሰው ከጋረድ ሠራዊት ጀርባ
ወደ ጭልጋ ከ ሂወስደው መንገድ ገቡ ። ሥፍራው ለጊዜው የማያመጋ
መሆኑን ሲያረጋግጡ ፣ ገብርዬ በቅሎዋን ወደ ኋላ አዞረና በሰላም የሰነ
በተበትን መንደር ለጥቂት ጊዜ በትካዜ ቃኘው ። በየሥፍራው የሚል
ኮሰው ቃጠሎ አሁን እየተበራከተ የወይኒ ኪዳነ ምሕረት ሰበካን በማ
ዳረስ ላይ ነው ። ቀደም ብሎ የተለኮሰው ተታጥሎ እያበቃ ጥቂት ጥቂት
የሚተን ጢስ እየቀረው ሲሔድ አዲሱ የሚነሣው ትኩስ ነበልባል ፣ እያ
ቀዘቀች ከሔደችው ጀንበር ጋር ይንጸባረቃል ።

“ እኔስ ሸፈተ ልባል ! አገሬው ምን በደለ ? ” አለ ገብርዬ ከራሱ
ጋር ዐይኑን ወደ ገበሬው ቤት አማጣጫ ሲያማትር ። በመጀመሪያ እንደ
ባዘቶ ሳሳ ያለ ጢስ በቀጭን ሲነሣ፡ቀጥሎ እየሰፋና እየጠቆረ ሔዶ ከው
ስጥ እሳት ቡልቅ ቡልቅ ሲል አየ ። አንጀቱ አብሮ የተቃጠለ መሰለው ።
በቅርብ ሆኖ ከዚያ ቃጠሎ አጠገብ የተፈጸመውን ቢመለከት ኖሮ
ምን እንደሚሰማው እንኳ !

ጋረድ ፣ ከሠራዊቱ ጋር ፣ በየሠፈሩ እየተርመሰመስ ሲዘርፍና
ሲያቃጥል ቆይቶ የገብርዬ ድንኳን ካለበት ሲደርስ ፣ ውስጡንና ዙሪ
ያውን አስፈተሸና ሳያመልጥ የቀረውን አንድ አንድ ጠባቂ አስጥሎ
በጅራፍና በትርኳሽ ተያያዘው ። ጠባቂው ግን ፣ ታማኝነቱም ይሁን ደን
ጋጤው ፣ መዓቱ እየወረደበት መልስ ከመስጠት ዘገየበት ። በዚህ ጊዜ
ጋረድ እግሩን አንፈራጥጦ ቁሞ አፉ አረፋ ቢጤ እየደፈቀ ጉራዴውን
ላጥ አደረገ ። “ በሕይወት መኖር አትፈልግም !” በማለት ሲያገላ
ርቅበት ጠባቂው ድንገት የባነነ መሰለ ።

“ እ. እእ ! ” አለ ሰመመንና ጣዕር በሚመስል ድምፅ ።

“ገብሬ የት አባቱ ሔደ ? ሕይወትህ እንዲተርፍ ከፈለግህ ብትና
ገር ይሻልሃል !” ለአንገት ሽሚያ በዙሪያው ያሰፈሰፈውን ጉራዴ ሲመ
ለከት ፣ “እዚያ እዚያ ግዶ” አለ በደመ ነፍስ ፣ አንድ እጁን ወደ ገበሬው
ቤት እያመለከተ ። “ ታን-ታንድ ሰው ቤት ነው ያረፉት ” የዘረጋውን
እጅ ሳያጥፈው የጋረድ ጉራዴ አንገቱን ቀለበውና መትረፉንም ሆነ
የፈራውን ሞት መቀበሉን ሳያውቀው ተገላገለ ።

ገበሬው ፣ ለመፍለጪያ ከሚያገለግለው የግንድ ጉማጅ ላይ ተቀ
ምጦ ያይኔ አበባን እያባበለ ጠበቃቸው ። ከድንኳናቸው ሲያጣቸው የት

እንደ ሔዱ ጠይቀው እንደሚረዱ ገምቷል ። ከመድረሳቸው በፊት ሸሽቶ
ማምለጥ ይችል ነበር ፣ ምን እንደ ያዘው ራሱም በትክክል አልተረዳውም ።
ባንድ ፊት ከቤቱ ደግሞ ማነው የሚያባርረኝ ? የሚል እልህ ነው ። በሌላ
በኩል እኔ መሸፈቱን ዐላወቅሁ ። የእግዜር እንግዳ በአሳረፍኩ ምን አጠ
ፋሁ ? በሚል ሐሳብ ምንም ጉዳት እንደማይደርስበት በመገመት ነው ።
ሌላው ቀርቶ የሚፈለገውን ሰው ያላስተናገዱ ቤቶች ሁሉ መቃጠላ
ቸውን ግን አላስተሃቀረውም ነበር ።

ብዙም ሳይቆዩ ደረሱ ። ጋረድ ከበቅሎው ዱብ ብሎ ወረደና ወደ
ፊት ቀደመ ። እንዲቃጠለው ቤትና ድንኳን እሳት ለብሶ እሳት ጉርሶ
ነበር ። የደረቀው የምራት አረፋ በከንፈሩ መጋጠሚያ ነጭ መሥመር
አበጅቷል ። ዐይኑ ጉርሽጥ መስሏል ። ተከታዮችም የእርሱን ስሜት የሚ
ያስተጋቡ ይመስላል ። ከፊሉ ጉራዴውን እየነቀነቀ ይንቆራጠጣል ።
ከፊሉ እንዲሰግለት አድርጎ ጥርሱን ያፋጫል ። ሌላው ፊቱን አኮሳ
ትሮ ይገላምጣል ። የተለየ እርጋታ የሚታይበት ደብተራ አክሊሉ ብቻ
ነበር ።

ከዚህ በፊት መንደሮቹ በእሳት ሲለኮሱ ፣ የገብርዬ ድንኳን ሲቃ
ጠልና ጠባቂው ሲገደል እንዳደረገው ሁሉ ፣ ከበቅሎው ሳይወርድ እየ
ኮለኮለ ወደ ዳር በኩል አቁሞ ጠቅላላውን ትርዒት ያስተውል ጀመር ።
የሰጠው ፍርድ ሲፈጸም የሚመለከት ዳኛ ዐይነት ነበር ። እርሱ ፣ የቅ
ጣትን ፣ የቁጣን ፣ የበቀልንና የጥፋትን ኃይል የሚፈጥር ብልሃት ነው ።
ይህ የፈጠረው ኃይል እንዴት እንደሚሠራ በሚገባ ማወቅ አለበት ።
ሊቁጣጠረው ፣ ሊመራው የሚችለው ሲያውቀው ብቻ ነው ። እንዳንድ
ጊዜ ጋረድ እንደ ዕብድ መወራጨቱ እያስገረመው ከንፈሩ በፈገ ፈገ
ግታ ወደ አንድ ጉን ጠመም ይላል ።

“ የዚህ ቤት ባለቤት አንተ ነህ ?” አለ ጋረድ ። ጥያቄ ሳይሆን
የደነፋ ቁጣ ነበር ።

“ እዎና ጌቶች!” ሲል መለሰ ። ከተቀመጠበት ተነሥቶ ሳይንቃነቅ ።

“ ኧረ የማን አባቱ ጀለንፎ ባለጌ ነው ! ደሞ እጅ እይነሣም” በማ
ለት ጋረድ ጉራዴውን እየነቀነቀ ጮኸበት ።

ገበሬው ፣ ከክንዱ ላይ ተንጠልጥላ የነበረችውን ያይኔ አበባን ገፋ
አድርጎ ለጥ ብሎ ሰገደ ።

“ ገብሬ የት ነው ያለው ?”

“ ገብሬ? ገብሬ ? ” የተጠየቀው ማንን እንደሆነ ቢያውቅም
ያላወቀ መሰለ ። የስድቡን አጠራር አልወደደወ ም ነበር ።

“ ገብርዬ ነዋ! ገብሬ ገብርዬ ያው ነው ።”

“ የታባቴን ዐውቂ ጌታው ” ጋረድ ሊጮኩ የሰውየው እንደ
ርጋታ አልተቀየረም ነበር ።

“ እንዴት ፣ ከቤትህ አልሰነበተም ፣ ”

“እሱማ መቸስ ቤት ለማዜር እንግዳ ነው ፤ ”

“ ድንቄም እንግዳ!” ሲል ጋረድ በፈዝ እንባረቀና እሽከሮቹን ይ
ይኑና እንገቱን ሰበቅ በማድረግ ሲያመለክታቸው ፣ ለመፈተሽ እየተጅ
ወደ ሁለቱ ቤቶች ገቡ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በማስተባበል ራሳቸው
እየነቀነቁ ተመለሱ ።

“እኮ የት አባቱ ሔደ ነው የምልህ!” ጋረድ የእፉ አረፋ በከንፈሩ
መጋጠሚያ መፍለቅ ጀመረ ።

ሰውየው መልስ አልሰጠም ።

“ ምን ይዘጋዋል ? አትናገርም ! ” ጋረድ እንደገና ጮኸበት ።

“ በእውነቱ እኔ አላውቅም ጌታዬ ። ”

ከገብርዬ መጥፋት ፣ የሰውዬው እልህና ታብዮ ጋረድን ይበልጥ
በንዴት እንጨረጨረው ። መላ ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ገባ ፣ ጥርሱን
አፋጨ ፣ ገብርዬ ካመለጠ ነገር ተበላሽ ማለት ነው ።

እየተንደረደረ ሔዶ ሰውዬውን በታሪያ ጥፊ ሲያጮኸው ነፍሱን
አያውቅም ነበር ። ሰውዬውም “ ይህን ይወዳል መሬ ! ” ብሎ በዚ
በገበሬ መዳፉ ስማይና ምድሩን ሲያደባልቅበት እንደዚሁ አልታወቀ
ውም ። ወዲያው በቅጽበት ደግሞ አንድ የጋረድ ባለሟል ፎክሮ ጉራዉ
ውን ሲሰነዝርና የሰውየው ሞንትላት ከመሬት ወድቆ ሲንከባለል አንደ
ሆነ ። ያይኔ አበባ ከድንጋጤዋ የተነሣ የሆነውን በትክክል ባትገነ
ብም እራታዋን ለቀቀችው ።

“ ልጅትዋን ብትይዚት አይከፋም ። ስታድግ መልካም አገልጋይ
ይወጣታል ። ወይም ደኅና ዋጋ ታወጣለች ” ሲል አሁንም ድርጊቱን
እንደ ታዛቢ በርጋታ የሚመለከተው አክሊሉ ምክር ሰጠ ። እሬ እያለችና
ትናንሽ እጆችዋንና እግሮችዋን እያፈራገጠች ስታለቅስ ፣ ወዲያው ቀለቡና
ከአንዱ አጋሰስ ላይ አስረው ሜኑዋት ። ከዚያም ሁለቱን ቤት በእሳት
ለኩሰው አሰሳቸውን ለመቀጠል ወደ ሌላ መንደር አመሩ ።

— 5 —

ከወጣትነት እንሥቶ ብዙ መንገድና ዘመቻ የሔደው ፣ ብዙ ውጊ
ላይ የዋለው ገብርዬ ፣ ከተዋጊ ኮብላይ ፣ ከፈራጅ ተፈራጅ የሆነበት የአ
ሁንኛው ጉዞው ራሱን ፈትኖና ተፈታትኖ ራሱን የታዘበበት ፣ የዓለምንና
የሕይወትን ተለዋዋጭነት የተገነዘበበት ነበር ። የውሃ ዋናና አደን ግዘው

ተሩን ያልተወ ቢሆንም ፣ በረጅም ጉዞ ረገድ የከብት ጀርባ የለመደ መሆኑን
ያወቀው በዚህ ጊዜ ነው ። በተለይ ቋራ ላይ ከካሣ ጋር ከተገናኘበት ጊዜ
እንሥቶ ለመንገድ ሲጋር በቅሎ ፣ ለግልቢያ ሸምጣጭ ፈረስ ተለይቶት
የማያውቅ ስለነበር ፣ አሁን ለሁለት የተፈናጠጣት በቅሎ ከሥር መብረ
ከረከ ስትጀምርና ወርዶ በእግሩ ማኩበኩብ ግድ ሲሆንበት ፣ አካላቱ
እንደ ዱርው እንደማያስመካው ተረዳ ። አንድ ቀን በእግሩ እንደ ተጓዘ
ውንቅው ይተሳሰር ፣ ጉልበቱ ይብረከረክ ፣ አንጓው እንደ ደረት ዕንጨት
የሚሰበር መስሎ ይሰማው ጀመር ። በዚህ ላይ ሰውነታቸውን ትንሽ
የሚያበረቱበት ስንት አልነበራቸውም ። በመንገዳቸው ላይ ወደ መንደር
ገባ ብለው እህል ውሃ እንዳይጠይቁ ከቴዎድሮስ ፊት ቀርበው ከማሰረ
ዳታቸው በፊት ፣ ወሬውን የሰማ “ እረመኔ ” ተቀዳድሞ መሸሚያ
መሸለሚያ እንዳያደርጋቸው ፣ ወይም የጋረድ ሰራ እንዳያገኛቸው ሠጋ ።
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሥጋና ጠጅ የለመደውን ሆዳቸውን በዱር ፍራፍሬና
ሥራሥር እያስታገሡ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። አብዛኛውን ጊዜ የሚጓዙት
መንገድ እያሳበሩ ነበር ፣ መንገደኛ እንዳያጋጥማቸው ነው ። ግን ይህ
ደግሞ ፣ ጨርቃቸው ከላያቸው ላይ እስኪቦጫጨቅ ፣ እግርና እጃቸው
የተተለተለ እስኪመስል ድረስ የቆንጥርና የሾህ ሲሳይ አደረጋቸው ።

የአካል ድካሙ ፣ የመንፈስ ቁስሉ የተሰማት ታንጉት ፣ እርስዋ ወርዳ
ለእሮር ጊዜም ቢሆን በበቅሎ እንዲጓዝ በመወትወት ፣ “ እንግላታሁህ
የኔ ጌታ ! ” ትለዋለች ።

‘ደኅና ነኝ!’ ይላል በልህ ጥርሱን ነክሶ ። ‘ይልቅስ ድካሙ እን
ቺን ነው የሚጐዳው ’ ይላል ፣ እርግዝናዋን ሲያመለክት ነው ።

“ አንተ ታልወጣህ ፣ እኔ ሁለተኛ አልወጣትም ። ሌጣዋን ትሔ
ዳለች እንጂ ! ” ታንጉት በእግርዋ እያዘገመች ገብርዬ በበቅሎዋ ጥቂት
ይጓዛል ። ግን የስሜቱ ክብደት ፣ ከእግር ጉዞ ድካሙ ይብስበታል ።

‘ ይብረ ታቦር ተደረስን በኋላ ብታባርረኝ እባ ታጡትም እይፈር
ድብህ ! ’ ትለዋለች ሌላ ጊዜ ።

‘ እንቺ ምናረግሽ ! ነገሩ ሌላ ’ ይላታል ።

‘ የማይሆን ነገር ባያሞረኝ ኖሮ ፣ ስለት ላስገባ ፣ ጠበል ልዘክር ባልል
ኖሮ መቸ ይኸ ሁላ ’ በራሰዋ ላይ በመፍረድ በትካዜ ባሕር ውስጥ ትሰ
ጥማለች ።

‘ ያለፈዉ ዐለፈ ። ብቻ በደኅና እንድረስ ’ ሲል ያጽናናታል ።

በሦስተኛዉ ቀን ፣ ቆላውን ወጥተው ከደጋው አገር እንደ ደረሱ ፣
“እውርደኝ ! እውርደኝ ! ” እለች ታንጉት በጣዕር ድምፅ ። ገብርዬ
ተፊት ሲንገዘገዝ እንደ ነበር ዘወር ሲል ፣ ለመውደቅ ወደ ጉን ዘምማለች ።
ክንብል ኮማለታ በፊት ተንደርድሮ ደገፋት ።

“ ምን ሆንሽ ፣ ምን ነካሽ ፣ ” ከድንጋጤው የተነሣ የገብርዬም ድምፅ የማታለት ታና ያዘ ።

“ ደም — ደም መታኝ መሰለኝ ፣ እስቲ ወደ ጥላ ቢጤ ውሰደኝ ፣” አለች ፣ እያቃለተችና እንደ ማማተ እየቃጣት ።

ከቁጥጁ ሥር ነጠላ ጋርዶላት ዐርፋ ከቆየችና እርሱም ወደ ምንጭ ወረድ ብሎ የተበላሸውን ጨርቅ ለቃልቆ ከተመለሰ በኋላ ነበር ሐሳቡ በመጠኑ የተስበሰበለት ። እንደ ዋሣ ወርወር ያደረገውን ዐይኑን ትክል አድርጎት ቀረ ። መልዶ ግራና ቀኝ ተመለከተ ። ተንሥቶ ዙሪያውን ቃኘ ። ማመን ቢያቅተውም መንገድ ዳር ትተዋት የነበረችው በቅሎ በእካባቢው ጨርሶ የለችም ። ተዘዋውሮ ከፈለገ በኋላ ዕድላቸው ገርሞት ቁጭ ብሎ አሰበ ። እንዳንድ ልማደኛ ከብቶች እንደሚያደርጉት የቆላውን አየር እያሸተተች ወደ አዝርዋ ተመልሳ ከሆነ አይደርስባትም። ታንጉትሙርጀው የመጣባት ከረፋዱ ላይ ሲሆን ፣ አሁን ፀሐይ ወደ ምዕራብ በኩል እዘ ብላ ነበር ። ታንጉት ፣ ትንሽ ጠና እስከትል ለምኖ ከእንድ ቤት ለማስጠ ጋት አስበና እካባቢው እንድ ጊዜ “ ክንፉ ቀመስ ” ስለነበር ፣ ምናል ባት ልጃቸውን ጋረድን ከሚደግፉ ሰዎች ቤት እንዳይወድቅ ሠጋ ። የሚ ያጣሩበት መንገድ አልነበረም ። የበቅሎዋን መጥፋት ለታንጉት ከነ ገፉት በኋላ ፣ “ እስቲ ምናልባት ካሀናቱ ለመታመን ቢሻሉ ተዚያ ግለ ቤተ ክርስቲያን ደጀ ሰላም እንጠጋ ” አላት በሩቁ ከጉብታ ላይ የተተ ከለችውን ቤተ ክርስቲያን እየተመለከተ ።

ታንጉት በክንድዋ ትከሻውን ተደግፋ ፣ እያረፉ እየተነሡ ሲያዘ ግሙ ፣ የሲራፉ ነጋዴ ከኋላቸው ደረሰ ። የሞኑት ከብቱ እያለከለከ ፣ ሣኑ እንደ ዋሣ እያያቸው ዐለፈ ። በግራጫ በቅሎ ላይ ተቀምጦ ከኋላ ያከ ተል የነበረው ቁጩር ነጋዴ ከእጠገባቸው ሲደርስ ቆም ብሎ አስተዋላ ቸው ። “ እንደምን ዋላችሁ ፣ ደኅናም አይደላችሁ ፣ ምን አገናችሁ ፣” ሲል ጠየቀ ።

“ አሞብኝ ድንገት ” ገብርዬ ዐቅመ ቢስ መሆኑ አስተሳሰቡንም እንጋገሩንም ባላገር መሰል አደረገበት ።

“ ዛዲያ ወደ መንደር መውሰዱ አይሻልም ነበር ፣”

ነጋዴው ዐልፏቸው እንደ መሔድ ሲል ገብርዬ የመጣው ይምጣ ብሎ ወሰነ ። “ ጌታው !” አጠራሩ ከምላሱ ላይ አዲስ ሆነበት ። “ እንድ ነገር ልለምንዎት ፣”

“ የምችለው ነገር ተሆነ ። ምንድነው ፣”

“ መጀመሪያ ደብረ ታቦር እስትደርስ ምሥጢሬን ላያወጡብኝ ይማ ሉልኝ ”

“እኔ ስለ ምሥጢርህ ምን አስችገረኝ ወንድሜ ” ጉዞውን ለመቀ ጠል ፣ በቅሎውን በርካቡ ነካ አደረገ ።

“ በእግዚር ይገርምታለሁ ” ሲል ገብርዬ እንደ ገና አስቆመው ። “ እንደዛሬ ሰው ለምኜ አላውቅም ። የሷ ነፍስ ነገር ሆኖብኝ ነው ” አለ ታንጉትን በዐይኑ እየተመለከተ ።

“ ችግርህን ንገረኛ ፣”

“ ይማሉልኝ ” አለ ገብርዬ ፣ ታንጉትን ከመንገዱ ጻር አሳርፎ የመሐላውን ዐይነት ቅጠል በጥሶ እያሳየ ።

ነጋዴው ፣ ነገሩን እንደ ቀልድ እንዳይመለከተው ገብርዬ በሞንቅ ላይ መሆኑ ያስታውቅ ነበር ። እንቆቅልሽነቱ ሞምር ሳበው ። ከበቅሎው ወረደና ፣ የነጨውን ሣር ፣ “ ይሽውልህ !” ሲል ደጋግሞ በጠሰለት ። ገብርዬ ግንባቱን ሲነግረው ፣ ነጋዴው ሊጥለው የነበረውን ሣር እንደ ያዘ ፈዘዘ ቀረ ። “ ድፍን ወይኒ የተቃጠለው እንተ ሽፍተህ ነው አል ተባለም ፣”

“ መባልማ ተብሏል ። ታሪኩ ረጅም ነው ። ወደፊት አጫውትዎት ይሆናል ። የምለምንዎት ግን ፣ ይችን በሽተኛ ሲሆን ደብረ ታቦር ፣ ታለበለዚያ ከሚታመን ሠፈር እስከደርስ ፣ የጋረድ ሰዎችም ቢያነጉን የርስዎ ሰዎች እያስመሰሉ ለማድረስ እንዲረዱን ነው ” አለ ገብርዬ ።

በእርግጥ በቁምድርስ ላይ የሸፈተ ሰው ካላበደ በስተቀር ተመልሶ መግባት እንደማይፈልግ ነጋዴው በመገመት ፣ “ መናዝረያችን ስንኳ ይቆግ ድረስ ነው ። ለሁሉም መጀመርያ ተዚያ እንድረስ ” አለ ።

ነጋዴው ፣ የኮርቻ በቅሎውን ለታንጉት ሰጥቶ ፣ ገብርየና ራሱ ሞንት በተጋባላቸው ሁለት እጋሰሶች ላይ በድብዳብ ተቀምጠው በሰላም ደቆግ ሊደርሱ ነጋዴው እዲስ ሐሳብ አመጣ ። በገብርዬ ላይ የተፈጸመውን ተን ኩል ከግመኑ ሌላ ፣ በመንገድ ላይ ስለ ቁምድርስ ያወጋለት ሁሉ አስደንቆት ነበር ። “ ፈቃደኛ ሆናችሁ ታቀረባችሁኝ ፣ አብሬያችሁ ደብረ ታቦር ልውጣና የዚያን ታምረኛ ሰው ፈት ልየው ። በየደረስኩበት ለወሬም ይመቸኛል ” ሲል ጠየቀ ።

“ ምን ችግሮኝ ! ” አለው ገብርዬ ።

ከአንድ ቀን ዕረፍት በኋላ ፣ ሦስት በቅሎ ተሞኖ ሦስቱም ወደ ደብረ ታቦር ጉዞ ቀጠሉ ።

* * *

የደብረ ታቦር ከተማ ፣ ከፊት ለፊታቸው ብቅ ሲል ቀኑ ገፍቶ ጀም በር በምዕራብ በኩል ሩብ ያህል ተደፍኖለች ። በሩቅ ከፊት ለፊታቸው የኑና ተራራ ሞጋግ ለብሶ የሰማይ ጣሪያ ጥሶ የገባ ይመስላል ። ከግራ

ቸው እንደዚሁ በሩቱ የደጋ መልካ ተራራ ሰማይን እንደ ተሸከመ ግዳ በርዝማኔ ተገትሯል ። ከተኛ በኩል ፣ እንደ መልካም የጤፍ ክምር መስሎ ከወጣው ተራራ ላይ ከተተከለው የየሱስ ደብር መሳለሚያ ላይ ሲደርሱ ፣ የቴዎድሮስ ሠፈርና የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ወደታች ተንጣሎ ታያቸው ። ገብርዬ ከንዱን ከበቅሎዋ ጀርባ ላይ ደገፍ አድርጎ ቆመና በጣም ተከዘ ። ከአካል ድካሙ ይልቅ የመንፈስ ሠቀቀኑ ከብዶ ተሰማው ። እንደዚህ ያለ ጉዞ እንኳን በውኑ በሕልሙም አልታየው ነበር ። አውንም ቢሆን እውን መሆኑን ማመን ያስቸገረዋል ። ወይኔ ገብርዬ ! እንደ ተራ ወንበዴ ዱር ለዱር ልሽሎከሎክ ብሎ ራሱን ነቀነቀ ።

ገብርዬ ፣ ከአባ ታጠቅ ጋር ለመገናኘት በጣም ቸኩሎ ነበር ። ግን እያጋው ደግሞ ግልጽ ሆኖ ታየው ። 'የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል' እንዲሉ ፣ ወፀደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ውሻ እንደሚቀጠቀጠው ሁሉ እር ሱም የባልንጀራ አለታውን አባ ታጠቅን የከዳ ይሁዳ ነው ተብሎ ተወ ርቶበታልና ፣ ሰው ሁሉ ፍትሩንና አክብሮቱን ሊገልጥለት በተሽቀዳደ መበት ሠፈር ፣ ከሰላምታ በፊት ሰይፍ መዝዘ ፣ እውነቱን ከመጠየቅ በፊት አድብቶ አንገቱን በመቀንጠስ ወደ ቤተ መንግሥት የሚሮጥ የትናንት ዕውቂያ ወይም ጓደኛ ቢያጋጥም እያስገርምም ። በስምና በመ ልክ ብቻ የሚያውቀውም ቢሆን ፣ በመጀመሪያ እንገት ቀንጥሶ በኋላ መመራመሩን ይመርጣል ። ችግሩ የተቀነጠሰ ሞንትላት እይቀጠልም ። ሌላው ቢቀር ፣ እውነቱ ሳይታወቅ መሞቱ ፣ ድርብ ሞት ድርብ ውርደት መስሎ ተሰማው ።

መሸትሸት እስኪል ከአንድ ችፍርግ ቁጥጭጠ ሥር ተከልለው ዐረፉ። ገብርዬ ፣ በዚያ ድካሙና የሐሳብ ለመሙኑ ፣ ከኮርቻው ላይ ደገፍ እንዳለ ወዲያውኑ እንቅልፍ ይዞት ሔደ ። ታንጉት ጡንቻው በመጠኑ እንዳለሳ ለስ ቀስ አድርጋ ጀንጃውንና ቁርጭምጭሚቱን ስታሻሽለት እንደ ቆየች በመጥፎ ትዝት ባንኖ ሲነቃ ጀንበር በምዕራብ አድማስ ጠልቃ ነበር ። ከላይ ጨረርዋን ገና የሚቀበለው ሰማይ ግን ፍም መስሎ ነበር ። የደም ምልክት ነው ይባላል ። የማን ደም ? የኔ ደም ? የጋረድና የአክሊሉ ደም ? ወይስ ሌላ ጥፋት ሊመጣ ነው ? ያም ሆነ ይህ የሚፈጸም ነገር ቢኖር በሐሳብ ቀስ በቀስ ከሚጨርሰኝ እንዲያውኑ ዛሬ ይለይልኝ ሲል ቁረጠ ።

ከዋና ከተማው እስኪገቡ ሙሉ ጨለማ እንደሚሆንና ሰውም ወደ የቤቱ እንደሚከተት ገመተ ። ግብገባ ከሌለ የቤተ መንግሥቱ ድንኳን አካባቢም ጭር እንደሚል ገመተ ። ራት ተበልቶ እባ ታጠቅ ካማ ከሊቀ መኳስ ዮሐንስና ከሌሎችም የቅርብ አማካሪዎቻቸው ጋር በእልፍኝ ወይም በቤተ መጻሕፍታቸው ፣ ስለ ዓላማቸውና ስለ ዕቅዳቸው የሚወ ያዩበት ጊዜ ነው ። ምናልባት እንዳንዶቹ ተሽቀዳድመው ሰይፍ ለመም ዘዝ የሚራወጡ ቢሆንም ፣ እንዲ ከፈታቸው ከቀረበ እውነቱን ለመንገር ዕድል እያጣም ። መቸም ፍትሕ ለመስጠት የሁለት ወገኖችን ጉዳይ ማዳ

መጥ ያስፈልጋል ። ቴዎድሮስ ደግሞ በፍትሕ ያምናል ። ለመናገር እንዴት ዕድል ይነፍገዋል ። ችግሩ ፣ ድንገት የሚፈነዳው ቁጣው ነው ። ቢሆንም ፣ ተዋበች በእጠገቡ ካለች ደግሞ እሳት ቁጣውን ውሃ ሆና በትጽበት ታቀ ዘችዋለች ።

ገብርዬ ፣ ታንጉትን አገላብጦ ጉንጩዋን ሳማትና ደግፎ ከበቅሎዋ ላይ አወጣት ። '' እናንተ እንግዲህ የሚያስጠጋ ዘመድ ፈልጉና . . . '' ሲል '' እስክመለስ '' የሚለውን ቃል የተጠራጠረ ይመስል ሳይጨርስ ተወው ።

'' እረ ምን ዘመድ ይጠፋል ? የነጋድራስ ይማም ቤት ፣ ቤቱ ማለት ነው ! '' አለ ነጋዴው ።

'' ስለኔ ሰው የጠየቀሽ እንደሆነ ግን የት እንደ ደረሰ አላውቅም ፣ ብቻየን ነው የመጣሁት በያቸው ፣ ነገሩ እስቲለይ ! '' ሲል ተሰናበታ ትና መጭ ብሎ በቅሎዋን መንገድ አሳያት ። ከዚያም ጸሎት እንደሚ ያደርስ ከንዶቹን ከደረቱ ላይ አመሳቅሎ ሳይንቀሳቀስ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆመ ። ዐይኖቹ ዕንባ ቋጥረው ነበር ። ምናልባት ነገ ጧት ከታንጉት ጋር በሰላም አይገናኙ ይሆናል ። ወይም ደግሞ ለመጨረሻ ጊዜ መሰነባ በታቸው ይሆናል ። ከንፈሩን ነክሶ ወደፊት ተራመደ ። መሞቱ ካልቀረ በሞልጋ ዱር የጅብ ራት ከሚሆን ከቴዎድሮስ ፊት መውደቁ ይሻለዋል ።

እንደኛውን የዘብ ክልል ያለችግር ሰተት ብሎ ዐለፈ ። የጠየቀው አልነበረም ፣ ዘቡ እንቀላፍቷል ፣ ወይም ሌላ መኰንን መስሎታል ። ከሁለተኛው የዘብ ክልል ሲደርስ ፣ '' ቁም ! ማነህ እንተ ! ሃ ! ሃ ! '' የሚል ድምፅ ጸጥታ በሰፈነበት ጨለማ ውስጥ አስተጋባ ።

ገብርዬ ስቅጥጥ አለው ። የመጀመሪያ ስሜቱ በጉራዴው ስለት ጸጥ ማሰኘት ነበር ። ነገር ግን ፣ የታዘዘውን ብቻ የሚፈጽም ሰው ሕይወት ማጥፋት ከባድ በደል መስሎ ተሰማው ። ባይሆን ሌላ መንገድ ካጣ መቸስ ምን ይደረጋል ። ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራረገና ቢያዋጣ ያዋጣ ሲል እንደ ራስ እንግዳ ፣ ድምውን ጉርንን አደረገና ፣ '' ጉበዝ እንደዚህ ነቃ ብሎ መጠበቅ ነው '' እያለ መንገዱን ቀጠለ ።

'' ተመልሰው መጡ እንዴ ጌታዬ ? '' የሚል ድምፅ ከወደ ጀር ባው መጣ ።

መልስ ሳይሰጥ እርምጃውን እፋጠነ ። ጥቂት እልፍ እንዳለ መሮጥ እየታጣው ፣ ራሱን በመታዘብ እየገታ ፣ እንደ ሠጋር በቅሎ በማኮብኮብ ገሠገሠ ።

ገብርዬ የለው ደም እንደ ውሃ በጨቀየበት ፣ ራሣ ተነባብሮ መረ ማመጃ ባሳጣበት የጦር ሜዳ ላይ ውሏል ። ግን እንደ እሁኑ መንፈሱ ታውኮ አያውቅም ። ልቡ ደረቱን ሰብሮ የሚወጣ እስኪመስል ድረስ መታ ።

በዚያ ቅጽበት ምኽት ሰውነቱ በሁሉ ወረዛበት ። ከቁጥጥሮ ራት መቆ
ረጡ ነው ? ወይስ የሞት ናፍቆት ነው እንዲህ የሚያረገን ? ብሎ ራሱን
በመጠየቅ ራሱን በሀሳም ታገለው ። እዲስ ሆኖ ፈተና ወቅት ተረገጥ
እንዲት እንደሚለውጥ እነሱ እውን ብለመማገሉ ተገረመ ። ከዚህ በፍ
ግን ወደኃላ መመለስ የለም ። እየተንደረደረ ከቁጥጥሮ ቁጥ ደንገ
ደረሰና ሁሉን ወደላይ ገፍቶ እድርን ተመለከተ ። ሚኖ በቅመረት በረጋ
እሳራት ናንትው ብሎ ይጠያል ። ግን ፥ ፅቃም ፥ ሰውም ድምም ነበር ።
ድግሉ የተቆጣጠሩት ጓሀ መሀይል ። የፈለጉ ዎት እየነበሩውን የሚቀጥል
እየመሰለው ሁሪያውን ሊመለከት ። ከእንድ ጥግ በኩል ከጥቂት ንጋ መነ
ከል የሰው ቅርጽ የነፀ መሰለው ። ከእንጂ መቆረጠ ላይ ፕማውን እነ
ሣና ይዛ ወደኢቦ ሬደፈራሉ ፕፈተ እንደ መሰለ ሁሉ ። እውንም ያጋጠመው
ትርጉት ቅዠት መሰለው ። እንድ ዋንጫ ተንከባለ ወድቆ ከመሰለ
የፈለሰው መሰባ ወፈሩን እርቦታል ። ከጨለማ እንድ ቅም ጫና አለ ።
ሁሉም ነገር እየተሰለ የሚሔድ ይመስል ። ቀን እጀን ወደ ዋንጫው አማጫ
እንደ ዘረጋ የተገነደመው የራሱ ፕቢቅ እጦት ነበር ። ማመን አቅቶን
ከርከከ ብሎ ሲሉን ከፊቱ ላይ ከመደቀን አረጋገጠ ። የከባር እንቅልፍ
ጭልጥ እድርን ወሰዶታል ። ነርከከ ከለው እሱ ከርፈያና ፉጨት የሰው
ላቀለበት እስትንፋስ እንደ ወናፍ ሳብ — ሁልቅ ። ሳብ — ከጉልቅ ይላል ።
የራሱ መንፈስ ከነቀቀን ተወጣር ብለ ። ፕቢቅው ነገር ኃለመን ሸሽ ብሎ
ከመነከሩ ነገርቹ ይህ ነው ይማይባል ንዲት ብልጭ አለበት ። ከዋሬ
እቃተለው እለኝውና የቃላቱትን እጀን እንደ ምንም መሰለው ።

" ዘንደቂ ! ዘንደቂ ! እንት ዘንደቂ ! " ነገርቹ የወቃሂሩን ትከሻ
ዘጋፊል እንተጫነጫው ።

" እ ! እ ! ማነው እሱ ለውን እላስቀኛ የሚል ! " እለ ወቃሂሩ
ለተቂት ጊዜ ያህል ዝም ብሎ እንደ ዘድን ከተገዘፈለፈ ዘነብ ወይን
ገለባ ከድን እያደረገ ።

"እንፈር ! ቀንም ! ቀንም ነው ያም አለ ! " እያለ ነገርቹ እንደገ
ዘጋፊል ነቀንቀው ።

" እት ቀስ ! "

"ቀንም ነው ያም አለ ! " ለማለት ነገርቹ ከዛፍ ፍሬ እንደሚራገፍ
ወይነት ሁለት ትከሻውን ፈተርቆ እርገጠገው ።

ፕቢቅው እያነቃ ሔደ ። " ምንድነው ተድፈየው ! ድንጓን ለብቻ
እንጂ ለሙቻ ተነግ አልተባለኩ ! ድንጓን እየጠፈቅው ነው ። ዘድፈ
ግን አዲቃ እንደሆነ የለኝም ። "

" አዲቃህ ነኝ ! "

" ማን ! " ወቃሂሩ ለመገረም አቅለን ወደነን ብልጥ አዩለ ።

" እሷ ነገርቹ ። "

" ነገርቹ ? ነገርቹማ ... "

" እቃ ነገርቹ ኃኝ " ለማለት ነገርቹ ወቃሂሩ ለሚገባ እንዲቃው
ፕማውን ከራት ለራሳ ድቅን እደረገው ። " እሆኝ ! ነገርቹ ኃኝ ። "

ወቃሂሩ ለመለራመርና ለመገረም አለነቃቸው ። " ግቅምንም
ተቀይሚለሁ ! እንት እለመሸሰኝ ! ታጠቅም ለንት ወረሰረኝ ! ጭኑ
ለት ታለ ጉመን ነው ትሆንኩት ። ለዚይ ! ለዚህ ወጅ ነው መትንሳሳ ! "
ነጅን ወደ ቅም ሜናው ዘረገ ።

ነገርቹ ከንፈን ጨለተ እደረገው ። " ድቸ መትንሳት እደለም ።
እንተም ቀምትቀለተረው እይገባኝም ። "

" ዘይ ለምን አልወለድከኝም ! "

" ፅት ! "

" ለት — —እህ — ል ለትቸ ... "

" እልቸረትኩም ! " ነገርቹ ብይታውቀው ምቸ ።

" እህ ! ቸፍተህማ ሠራዊት ሙቶለህ ! "

" ልለት ነው ! " ነገርቹ እጀን አወራጨ ።

ወቃሂሩም እኔ ምናውቃለው ለሚል ለሚት ትከሻውን ነቀነቀ ።

" እቃምንኝም ! "

" ለምንሠማ ነገር እሳሬህ ለዘም ቀኖርኩት ። "

" እውንም ኑመነኝ ። "

" የኔ ማመን እለማመን ምን ቀጋ አለው ! እለ ታጠቅን እሙን
እንጂ !! "

" ለለ እድሏለ ! ከረቃ ለከረቃ ለክሉትን የመጣሁት ። ለመሆኑ የት ሔዶ
ነው ። ድንኳኑ እንደጀህ ወና የሆነው ። ዘመቻ ነው እንላለሀ ለንድቅ ድን
እንን ላይነቅል ለደነግም ። "

የተቀሀቹ ሕመም እየጠናባቸው ለለ ሔዶ ለማነሽውም ነገር ከድን
እን ። ቤቱ ይሸኻል ተብሎ ። የተጀመረው ቤት እስኪያልቅ ለጊዜው ወደ
ሰብ ትመህ እናራቸ መዛወራቸውን ለንደቂ ነገረው ።

የተደነመበትን ግራ ። የተሰሙንም ሁናቴ ከተረከለት በኋላ እዛው
ሔደው ለንደቂ ተጠግቶ ለመሰለል እንዲረግጠው ። ነገርቹ ግን መሆኑ
ሂቃውቅ ከእናራቹ ለመሄት እንደ ድንኳኑ ቀላል አይሆንም ። ግዚው
ኮረሙን የታወረ ሆኖ መግቢያው ለር እንኮ ብቻ ነው ። ከለፉ ቤቱ

በርከት ብለው ቦተኩለኩሉት ዘበኞች እንድደው የሚሞቱት እላትም በአጠገባቸው የሚያልፈውን ሰው ማንነት በቀላሉ ለመለየት ያስችላ ቸዋል ። በዚህ ላይ ቱምድርስ ከለምች ጋር በቆይታ ላይ ስለሆኑ ፣ ያልተ ፈለገ ወይም አስቅድሞ ያልተፈቀደለት ሰው እንዳይገባ ተብሎ ታዟል ።

አሊቃና ሜፍራ አዳራሹን በሩቅ እየተመለከቱ ዘዴ ተመካከሩ ።

" ንብርዬ መጥቷል ብለው ለምን ንብተው አይነግሩልህም ?" ሲል ሻሊቃው ሐሳብ አቀረበ ፣ ቱምድርስ ወዲያው እንደሚያስጠሩት በማመን ።

ንብርዬ ራሱን ነቀነቀ ። መልእክቱ በእርግጥ ከደረሰ ለክፉም ሆነ ለደግ ወዲያው መጠራቱ አይቀርም ። ግን 'እባብ ያየ በልጥ ይበረግጋል' እንዲሉ ፣ በእነጋረድ ሜራ ማንን ለምና ማንን እንደሚጠረጥር እርግጠኛ ሊሆን አልቻለም ። ቱምድርስን ማሳመን ከቻሉ ፣ ከአልፍኝ አስከአካቢ እንሥቶ እስከ ዘበኞች ድረስ የራሳቸውን ለው እዚጎድተው እንደሆነስ ? ከቱምድርስ ፈት በሕይወት መቅረቡ ፣ ሜራቸውን የሚያጋልጥባቸው ስለ ሚሆን አስቀድመው ከማጥፋት አይመለሱም ። ጉዳያቸውን ሸፍፍነው የሚያስቀሩበት ሌላ ምንም መንገድ የላቸውም ። ከነደሉት በኋላ ምክ ንያት መስጠት ቀላል ነው ። በቱምድርስ ላይ አደጋ ለመጣል አድብቶ ሊገባ እንጉንው ማለት ይችላሉ ። ቱምድርስም ፍርዱን ለማችውት ብሎ ያመለማናቸዋል ፣ ይሸልማቸዋል ።

" ይህማ እንደሳት ራት በርረን ወጥመዳቸው ውስጥ ነባንላቸው ማለት ነው ። የለም የሚሾሞን እንደ ምንም ሾልኮ ማለፍ ነው ። ይልቅስ እንድ ሐሳብ መጣልኝ ። እንተ ካልገባሁ ብለህ ወይም ለካራም መስለህ ፣ ለነጉሩማ እውንም እንደ ለከርክ — ነህ — ከበሩ ላይ ጭቅጭቅና ጫጫ ፍጠር ። ዛዲያ ሁሉም ባንተ ላይ ሲረባረቡና ሊያተኩሩ እጓ በለጥሩ ዘልዶ ልግባ ። እጠር ያለ ስለሆነ የሚያቅተኝ አይመስለኝም ። "

በንድቁ በሞትታ ስሜቱ ለለምባንር የገፃ ይመስል ፣ ንብርዬ ንግግ ሩን ሳይጨረስ " ምን ቸነረኝ ! " አለና እንደ መራመድ ታጣ ።

" ቆይ ! " ሲል ንብርዬ በክንዱ ሳብ አደረገው ። " ወሙተህ ግባ በት ። "

" ምኑን ? "

" እዲን ሊያደርስብህ ይችላሉ ። "

" እንተን ይትናህ እንጂ ለጀ ሊታስብ ። ሰሩ ሜዳ ውዱ ምላሙት አደረከኝ እንዴ ? "

" ያ ሌላ ይሽ ሌላ ። "

" እሳት ካየው ምን ለየው ? "

ንብርዬ ምክንያቱን ያላወቀው ቅሬታና ጎዘን ድንገት እየተሰማው የሞቀራውን ትከሻ በእጁ ጠብ ጠብ አደረገው ። " በላ እንግዲያው ውለታ ከፉይ ያርጉኝ ። "

" ባትረሳው ! " አለ ወታደሩ በቀልድ አኳኋን ። " በሰሜን በኩል ያለው አጥር ይሻላል ። እሾሁ ቀለል ያለ ነው ። "

ንብርዬ ወደ ተባለው አግጣጫ እስኪቃረብ ድረስ ወታደሩ ጥቂት ጠበቀው ።

—6—

የበሩ ሜጫታና አምባንር ሲቆፋም ፣ ንብርዬ አጥሩን ዘሎ ግራና ቀኝ ተገላመጠና ተመርመር ከአዳራሹ በራፍ ደረሰ ። የልቡ ትርታ ግቢውን የሚቀነቅስ መስለው ። ዝርበብ ብሎ የተዘጋውን በር ቀስ እድርን ከፈ ተውና እንገቱን ብቻ ለገባ አድርን አስገባ ። እቶ መላኩ ግራና ቀኝ ሁላት ኛ ተቀነሎለት ከአትርናሱ ላይ ተደፍቶ ይጽፋል ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ከአጠገቡ ቁሞ መላኩ የሚጽፈውን ይመለከታል ። ቆንስል ፕላውዴን ከአናፉሹ ጥግ በድንክ መንበር ላይ ተቀምጧል ። ቱምድርስ እንድ ጊዜ መደ ፕላውዴን እየሔዱ ሌላ ጊዜ መደ መላኩ እየቀረቡ ፣ ከመጂያ መጂሀ እየቀንጭራደዱ ፣ ጣታቸውን እየቀሰሩ በእእምሮዋቸው የሚንላላውን ሐሳብ የሚያወጡ ይመስል ፣ እንገታቸውን ሰበር መለስ እያደረጉ የሚጻ ፈውን ይናንራሉ ። ንብርዬ እንደ ነፋሱና እንደ ፈታቸው አትጣጫ የሚና ፍሩት በከፉለ ተሰግሙ ። " ሊቀ መኳስ ዮሐንስ እንደ ልጂ ፣ ቆንስል ? . . እንደ መንሜ . . . በግከበር . . . በግፍቀር . . . ይዝውም — በመፍ ራት ላይሆን . . . መጻድንትምን በመፈለግ . . . አንፈ በመሳፍንቶች . . እውንም ጠላት ከቢታል . . ትልቅ እንድትሆን ወገኔ እንዲመለጥን . . . . ሰዋቂዎች ፣ ባለሙያዎች . . . ውለታዎን አልረሳም ። እመልሳለሁ . . . " ቱምድርስ ለንግሥት ቢክቶሪያ የሚላክ ደብዳቤ እያጻፉ መሆናቸውን ንብርዬ መጂያው ተገነዘበ ። ሁናቴያቸው እሳዘነው ። ባለፉት ጥቂት ወራት ብዙ ዓመታት ያረጂ ይመስላሉ ። የግንባራቸው መሥመሮች የበለጠ ተጭረጸው ወጥተዋል ። የብይናቸው ዙሪያ ወደ ጥቁረት መቀለሙ በጣም ብርንን ለይቶ ያስታውታል ። እንቅልፍ እጥቶ የመሰንበት ምልክት ነው ።

'የኔው ጣጣ ይሆን ? ወይስ የተዋበች ሕመም መይንስ ደም ሌላ ችግር እንተሚቸዋል ?' ሲል ንብርዬ አሰበና ፣ እንድ ሥውር ኃይል እንደ ሳበው ያህል ሳይታወቀው መደፈት ተራመደ ። አሁንም እየቀንጭራደዱ ንግግ ራቸውን እንደ ቀጠሉ መደ በሩ አቅጣጫ ዘመር ሲሉ ድንገት አዩት ። ግን አልለዩትም ። " ብርቅ ጉዳይ ይዣልሁ ሰው አይግባ እላልኩም ነበር ? " አሉ ትንሽ ቦታከተ በሚመስል ቁጣ ። ንብርዬ ቀጥ ብሎ ቆመ ። በመጠ ራጫቸው ፣ በመመረመርም ትከሩ ብለው አስተዋሉት ።

“ ገብርዬ ! ገብርዬ ነህ ወይስ ምትሃት ነው የሚታየኝ ! ” ሲሉ ጠየቁ ። የምሥጢር ውይይት ይመስል በጣም በለሰለሰ ድምፅ ።

“እረ እኔው ገብርዬ ነኝ አባ ታጠቅ” አለና መለሰ ፣ አሁንም አንድ ኃይል የሳበው በሚመስል ስሜት እየቀረበ ። ቴዎድሮስም እንደዚሁ እቅፈው ለመቀበል የከጀሉ ይመስል፣ ሁለት ክንዳቸውን ዘርግተው ወደ ገብርዬ ተራመዱ ። ግን የገብርዬ መሸፈት ድንገት የተገለጠላቸው ወይም የታወሳቸው ይመስል መላ አካላታቸው ኩምትርትር አለና ቁጥ አሉ ። አቶ መላኩና ቆንስል ፕላውዴን ከተቀመጡበት ተነሥተው ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በቆሙበት ሁለም በመገረም ድርቅ አሉ ።

“ ጥፋ ! ጥፋልኝ ቶሎ ተፈቴ ! ሕይወትህ ሳትጠፋ ! እኔ እንዳንተ አይደለሁም ። ሕይወትህንስ እላጠፋትም ። ብዙ ጊዜ ለሕይወቴ የዳረግሃት ናትና ! እና በፈጠረህ ጥፋልኝ ! ” ሲሉ ቴዎድሮስ ጮሁና ሕይወቱን ሊያድን ሲወጣ ለማየት ያልፈለጉ ይመስል ፣ ፊታቸውን በመዳፋቸው ሸፍነው ወደ ታች አቀረቀሩ ።

ገብርዬ ተንደርድሮ ከጉልበታቸው ሥር ተደፋ ። “ እንግዲያውማ እንደ ተባለብኝ ባጠፋም ኖሮ ትምረኝ ነበር ማለት ነው ! ዛዲያ ያጠፋሁ ሲማር ፣ ባላጠፋስ ደሞ ልትምረኝ አትችልም ! አባ ታጠቅ ፣ ቂጣህን ከእፎቷ ከማውጣትህ በፊት ነገሬን ስማኝ ። እንተ እንደምትለው ፣ ትክክለኛ ፍርድ ለመበየን የከሳሽንም ፡ የተከሳሽንም ቃል ማጣራት ይገባል እና ከቂጣህ ፡ በፊት . . . ”

“እኮ በል ተነሥ ! ማነን ጡረኛ ለማረግ ነው ! ቂጣ አልከኝ ! ግና ምን የተረፈ ቂጣ አለኝና ! አልቋል ። ተሟጦ አልቋል ። ይልቅስ የምትነግረኝ ነገር ታለህ ልስማው !” ፊታቸውን በመዳፋቸው እንደ ሸፈኑ ፣ በመታከት ከወንበራቸው ላይ እንዘፍ አሉ ።

“ የት ልጅምር አባ ታጠቅ ? ”

“ የትም ጀምረው ፡ ብቻ ልስማው ” አሉ ፊቱን ሳያዩ ።

ነገራቸው ። ቆስሎ ጉንደር እንደ ተመለሰ ጋረድና አክሊሉ ሙክት አሊይዘው እንደ ጠየቁት ፡ ከዚያም እየተመላለሱ እንደ ተወዳጁት ስለ ሕልሙና ስለ ፈዛቸው ፡ ስለ ጥርጣሬው ፡ በመጨረሻም ስለ ታንጉት እርግዝናና እምሮት ምንም ሳያስቀር ተረከላቸው።ከታሪኩ ግማሽ ላይ እንደደረሰ ከሩቅ የሐሳብ ዓለም የሚመጣ በሚመስል ድምፅ ተቀምጦ እንዲያወጋቸው አዘዙት ። ከእንድ ጥግ የሚገኘውን ወንበር አምጥቶ ከአጠገባቸው ተቀመጠና ታሪኩን ቀጠለ ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቆንስል ፕላውዴንና ኢቶ መላኩም ዙሪያውን ከበው ቆመው በመገረም አዳመጡት ። ከወደኋኋ ኪዳነ ምሕረት ደብረ ታቦር እንዴት እንደ ደረሰ ከተናገረ በኋላ ፡ “ ይኸው ነው ፡ አባ ታጠቅ ” ሲል አዘዙ ።

ቴዎድሮስ ። እንዲታቸውን ደፍተው ሲያዳምጡ እንደ ነበር በራሱ እክል ላይ ተጠምጥሞ እንደሚወረወር የቆሰለ አባብ ፡ ከመቃመጫቸው ተፈናጠሩ ። ከንፈራቸውን እየነከሱ ፣ ግራ እጃቸውን ከጉራዴያቸው መቁነጥ ላይ አስደግፈው ፣ በቀኝ እጃቸው ቁንዳላቸውን እየጐተቱ ሪዛቸውን እየላሱ ፣ የእዳራቡን ወለል አምስት ጊዜ ያህል ተመላለሱበት ። አንዳንድ ጊዜ እንደ ቆመ ግንድ ባሉበት ድርቅ ይላሉ ። ምንም ነገር የማያዩ ፣ የማይሰሙ ፣ በውስጣቸው የሕይወት እንቅስቃሴ የሌለባቸው ይመስላሉ ። ነገር ግን ፣ በዚያች ቅጽበት ፣ በዚያ ድርቅ ባለ አካል ውስጥ ይህ ነው የማይባል አንድ ዐይነት እሳት የሚንቀለቀል ፣ አንድ ዐይነት እሳተ ገሞራ ለመፈንዳት የሚፈላ መሆኑን በቅርብ የሚያውቁት ጥግ ጥግ ይዘው በመቆም ቃጠሎው በራሱ በረድ እስኪል ጠበቋቸው ። የተሻለው ዘዴ ይኸ መሆኑን ረጅም ጊዜ አብሮ ከመኖር ተገንዝበውት ነበር ። በምክር ፡ ቢቃልመልስ ሊያረጋጉዋቸው የሚችሉት ተዋበች ብቻ ናቸው ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በአዘኔታ ሲያስተውላቸው ፡ ‘ይህ ሰው ዓላማውን እንዲፈጽም ፣ ተዋበች በግድ ታስፈልገዋለች ፡ ታሰበለዚያ ግን ’ የሚል ሥጋት በሐሳቡ መጣበት ። የዲፕሎማትና የታላቋን ብሪታንያን ክብር ለመጠበቅ ተረጋግቶ የቀረው ቆንስል ፕላውዴን ብቻ ነበር ።

ከጊዜ በኋላ ቴዎድሮስ ከወለሉ መኻል ላይ እግራቸውን እንደማቧተር አድርገው ፣ ግራ እጃቸውን ከጉራዴያቸው ሰገባ ላይ አስደግፈው ፣ በቀኝ እጃቸው ጺማቸውን እየጐተቱ ቆሙ ። እሳቱ በረድ ማለት ጀምሮ ሐሳብ ሲተካበት ነው እንደዚህ የሚሆኑት ።

“ እሆሆ ! እኔን የሚገርመኝ የኔው የራሴ ጅልነት ። ሁሉቱ የማይሰ ያዩ ጓደኞቹ መሆናቸውን ፡ ሁለቱም አብረው የዚያን ደደስ ነኝ ባይ ግብጽ ቤት እንደሚያዘወትሩ ከሰማሁ ቆይቻለሁ ። ” ቀደም ሲል የነገረቻቸው ታንጉት ብትሆንም የት ፡ እንዴት እንደ ሰሙት ግን አልገለጹም ። “ ዛዲያ ፡ ጋረድ ወቅሙንም ፡ ችሎታውንም ሳይመጥን ታለኔ ሰው የለም ብሎ የሚንጠራራ አጉል መሆኑን ሳውቅ ፡ ያ አክሊሉ ፡ ግና ከልጅነቱ ጀምሮ ተንኮለኛና መሥሪ መሆኑን ሳውቀው ፡ ሁለቱን ምን አቆራኛቸው ብዬ ማመዛዘንና ነገር ማያያዝ እንዴት ተሳነኝ ! ” ራሳቸውን በቅሬታ ነቀነቁ ።

“ እኔምኮ አጥፍቻለሁ ። ጥርጣሬው እንዳድረብኝ አለመንገሬ ” አለ ገብርዬ ።

“ ጥፋት ነው ፡ ጥፋትም አይደለም ። ግለቱ ፡ ጥርጣሬህን ከመጀመሪያው እንሱን መስለህ ሐሳባቸውን ብታጣራው መልካም በሆነ ነበር ። ታለበለዚያማ ፡ “ ሲያጣሩ ወሬ ሳይገድሉ ጐፈሬ ” እንደሚባለው ባልታጨበጠ አጉል ጥርጣሬ ነገር ማወሳከቱን ብትጠላው መጎፈህ ትሩ ቢመሆኑ ስለሆነ አላጠፋህም ባይ ነኝ ። ” ሃይዲታቸው መልሶ ተቀበለ ።

“ ግራልኝ ታገለሰን ! ጥፋጣሬ ፡ የተረጋገጠ ነው ብሎ የነገረን ያ ቀልማዳ ነው ! ” አሉ ከንፈራቸውን ጐምነከሱ ።

ታከለ አልተገኘም ። ቴዎድሮስ በራሳቸው ሐሳብ ተውጠው ልብ አላሉትም እንጂ ከቀትር ጀምሮ በአካባቢው አልነበረም ። ከመሠረቴ እንጋረድ ከሚራቸው ምሥጢር ሳያስገቡት በስሕተት የፈጸሙው ነገር ቢሆንም ፣ እንዲቀላቀላቸው ሲሉ የቴዎድሮስ ሰይፍ በእንጉቴ ላይ ሳያርፍ ራሱን እንዲያድን መልእክት ስለ ላኩበት ነፍሴን አውጪኝ ብሏል ። ቴዎድሮስ ፣ በታከለ መጥፋት ከግዘንና የባሰውን ከመናደድ ይልቅ በመገረም ከትከት ብለው ሣቁ ። የቤተ መንግሥት ኮረዳ ግጫወት እንጂ ከወንዶች በታ ይውላል ሲሉ ገምተውት እያውቁም ነበር ። ያቀረቡት ፣ የደጃች ጐሹ ዲቃላ ልጅ ስለሆነ ፣ የሀገሬው ሕዝብ እንዲደሰትና እንዲተባበራቸው ሲሉ ብቻ ነበር ። አንድ ዕዳ እንደ ተገላገሉ ቁጠሩት ።

“ እሱም ሰው ሆኖ ! ምንተዳዩ መይሳው ! ‘ ባቴላ አለቀ ቢሉ ፈስ ቀለስ እንጂ ” በማለት የፈዝ ሣቃቸውን ሳይጨርሱ ከበሩ በኩል አዲስ ግርግር መጣ ። ወዲያው የግቢው ዘብ ጮኅላፊ እየተንደረደረ ገባና እንደ መደፋትም እጅ እንደ መንሳትም አለ ። ሰውነቱ በድንጋጤ ይርበደበዳል ፣ ገብርዬን ሲያይ ባሰበት ።

“ ይሞ ምን ጉድ ተፈጠረ ? ጀሮዬ ደግ ነገር ላይሰማ መከልከሉ ነው ልበል ? ”

“ ሰንደቂ — ሰንደቂ ” አለ የዘብ ጮኅላፊው ትንፋሹ እየተቆራረጠ ።

“ እኮ ሰንደቂ ምን ሆነ ? ወይስ ምናረገ ? ”

“ ተጐድቷል — ሙ — ሙ ” የዘቡ ጮኅላፊ መጨረስ አቃተው ።

ባይጨርሰውም ቴዎድሮስ ገባቸው ። ገብርዬ ሰቅጥጥ አለው ። “ እኩ ምን አገኘው ? ” ሲሉ ጠየቁ ።

ዐረፍተ ነገሩ እየተቆራረጠበት የዘቡ ጮኅላፊ የሆነውን ለማስረዳት ሞከረ ። “ መጣና አዳራሽ ካልገባሁ ታባ ታጠቅ ዘንዳ አለ ። ሰክሮዋል መሰለኝ ፣ ያንገዳገዳል ። የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥራል ። እኛ ግን አንደም ሰው አንዳይገባ በታዘዝነው መሠረት ከልክለ ነው አልነው ። እሱ ግን ካልገባሁ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ አስቸገረ ። ሚቅሚቅቱም ፈጠረ ። እረ ተው ! ብንለውም አልመለሰም አለ ። ሰክሮ ነው ብለን ልናባብለው ፣ ልናበርደው ሞከርን ። ሚራሹን ጥሮ ካልገባሁ ብሎ ጉራጌውን መዛ ሁላችንም እያወከ ወደኔ ሲመጣ ፣ ሲመጣ አንደኛው ዘብ — አንደኛው ዘብ እኔን ለማዳን ብሎ . . . ” ንግግሩን እንጠልፍሎ ተወው ።

“ ወጋው እትዬም ። ከሆነ በኋላ ታሱን ምን ትረረዋለህ ? ” አሉት ቴዎድሮስ ፣ “ ግን ምን ነካው እባክቸው ? ”

“ እኔ እንጂ ብቻ የሰከረ ይመስለሻል ” ሲል መለሰ የዘቡ አለቃ ፣ የሠጋው ቁጣ ባለመምጣቱ ቀለል ብሎት ።

“ እርግጥ ጠጥቶ ነበር ” ሲል ገብርዬ ለጠቀ ። “ ግን በርዶለት ስለ ነበር የስካር አይደለም ። ”

ቴዎድሮስ በመገረም ትኩር ብለው ተመለከቱት ።

“ አዎ ! በእው ጦስ ምክንያት ነው ። ”

ነገሩ እንቆቅልሽ እንደ ሆነባቸው ቴዎድሮስ አውንም በአስተያየታቸው ገለጹት ።

“ እኔ ነኝ እባ ታጠቅ ፣ ማንም ሳያውቅ ባጥር ዘልዬ ገብቼ ካንተ ጋር እንድገናኝ ከበሩ ዘበኞች ጋር ግርግር እንዲያነሣ ያደረኩት ። እኔው ነኝ ለሞት የዳረኩት ሰንደቂን ። ” ገብርዬ የተናነቀውን ዕንባ ለመግታት ከንፈሩን ነከሰ አደረገ ።

“ እያፈረድብህም ። እንተማ ምንታረግ ! ባሞንክበት ፣ በታመንክበት ግቢ የሞታሞነው ብታጣ ሰውን ሁሉ መጠርጠር ሙች ይነስህ ? ”

ቴዎድሮስ ፣ በትካዜና በሐሳብ ተውጠው ለረጅም ጊዜ ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ ፣ ታናናኛ እንደ ቆየ ያህል በሰፈው ተንፈሱና ፣ “ ለመሆኑ ወያኒ አገርሞ መሆኑን አንዳች ነግራሃለች ? ” ሲሉ ገብርዬን በድንገት ጠየቁት ።

“እም እባ ታጠቅ ! የልጅነቴ አማሪኛ በላልች እኩ ነው እኔም የሐድኩት ። ”

“ አም ! የልጅነቷ ! ” ቴዎድሮስ እንድ ዐይነት የትካዜ ናዳ የተጫናቸው ይመስል ፣ ሚንቅላታቸውን በእጃቸው ደገፉ ። “ ሌላስ ? ዘመድስ አገኘች ? ”

“ አይ ! አይመስለኝም ። እኒ አላወኩም ” አሰ ገብርዬ ወያኒ እንደ ገባ ሰሞን የከነከነው ነገር እንደገና ትዝ ብሎት ።

“ ወቸው ጉድ ! ” ሲሉ ከራሳቸው ጋር ፣ ከንፈራቸውን በእዘኒታ መጠመና ጉዳዩን ወዲያው ለወጡት ። “ እስቲ ሰውስም የአንተ የወንጀሜንና የልጇን ሕይወት በደኅና ተዘህ ያደረሰልኝን ነጋዴ ነገ ይሸኘውና ላመሰግነው ። በተረፈ እንግዲህ ጀርየ ሌላ ጉድ ሳይሰማ በሱ ወደ የማረፊያችን እስቲ ” ሲሉ አሰናብተው ወደ እልፍኝ ፈቃቸውን መለሱ ።

“ መልክቱን እባ ታጠቅ ? ” ሲል ሲቆ መኳስ የሐገሬ ጠየቃቸው ።

“ መልክቱ ! ” ሲሉ ጠየቁ ጨርሶ እንደ ተረሳ ጉዳይ ፣ “ ከናቶኛ የቁም ነገር መልክት የሚጻፈው ሐሳብ በተሰበሰበበት ፣ መንፈስ በተረጋጋ በት ጊዜ እንጂ በንዲህ ያለ ሁኔታ ሲቆ መኳስ ! ያድርሰን ፣ ረጋ ብለንስ ጨርሰዋለን ። ገብርዬ ግን ተዋበችን ጠይቃት እንጂ ” ብለው ወደ እልፍኝ አመሩ ።

ገብርዬ ለግልቀሰ ይሁን ለመግቸ ፣ ያለየለት ሲቃ እያተናነቀው ተከተላቸው ።

Meysor Bro
t.me/BooksandYou

ክፍል አምስት እስጢፋኖስ ፈረ ።

[illegible] ። እንዲህ ብለው ጠየቁት ። “ጌታ ሆይ ፣ ይህ ሰው ከዚህ ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛ አይደለም ። እንዲሄድ ልንገፋው ይገባል ። ከዚህ ሰው ጋር ለመኖር አንፈልግም ። ይህ ሰው ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ካልሆነ ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ፈልገን እናገኛለን ። ይህ ሰው ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ካልሆነ ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ፈልገን እናገኛለን ። ይህ ሰው ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ካልሆነ ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ፈልገን እናገኛለን ።

[illegible] ። ከዚህ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐረገ

መስላቸው አንዳች በይነት ተፈጥሮ አላቸው ። አሁን ከአልጋ ላይ ውለው በታዩ ። ለሕረሳቸውም ። ለቴዎድሮስም አዘኑ ። ለራሷም ቁም ር ።

ታንኮች ደብረ ታቦር በገቡ ። የመንገዱ ድካም ወጥቶላት ፡ ድን ጋጣው በልርጎት የሆነውን ሁሉ እንደጋና ባታስዘው ከደሮው የባሰ ትካዜ ይሰማት ጀመር ። ትካዜ ብቻ ሳይሆን አውን ጸጸትም ታከሰዘት ። ንዘርጹ ደስ እንዲለው ። ትዳርዋ እንዲጸና ብላ ፡ እንደ ትልቅ ጋጢአት በሚቁጠር መንገድ ልጅ ለማጣት የሠራችውን ሠራት ። ሆነ ፡ ተስፉ አደረባት ። ግን በአዊር ጊዜ ተመልሳ ወደ ቀደሞ ዕድልዋ ገባች ። " ጋጢአት ስለሆነ ወትሮውንስ ቢሆን ባይባረከው ነው እንጂ ትላለች " ከራስዋ ጋር ። ለዚህም ደግሞ ንዘርጹንም ራስዋንም ለሞት አብቅታ ነበር ። ለአርባ ቢል ንዘርጹ ። ከቴዎድሮስ ፊት ለረጅም ጊዜ ባይርቅ ኖር እኒጋረድ መቶ በበብ ያንኑ ነበር ? ቴዎድሮስ ከወሎ እንደ ተመለሰ ፡ ሌላ ሌላውን ስትነግረው ፡ የእኒጋረድና የንዘርጹን ጭውወት ደብታ ባታስቀር ኖሮ ይህ ሁሉ መች ይደርስ ነበር ? ንዘርጹ ፡ ከቴዎድሮስ ጋር ጋሎት ወይም ጦር ሠፈር ሔዶ ታንኮት ብቻዋን ተውድግ ከጸጸት ጋር ይህንን ሁሉ ስታስብ ፡ የምታዋየው ፡ የልብዋን ቁስል የምታሳየው ሁነኛ ሰው ትፈል ጋለች ። ከእጠገብዋ የምታገኘው ይመስል ፡ አንዳንድ ጊዜ ሳይታወቅት ዙሪያዋን ትመለከታለች ። ማንም የለም ። ወይዘሮ ደብሬ ጉንደር ናቸው ። ከዱሮ ጓደኛዋ ጋር ፡ አንድ ጊዜ የጎቃ ብርሌ መስልው ቀርተዋል ። ከለ ገሬው ሰው የምትቀርበው ወዳጅ አላፈራችም ። የምታፈራም እይመስ ላትም ። ከወይዘሮ ደብሬ በቀር። ያውስ በዘርዋ ምክንያት ሳይሆን ይቀራል፤ ጉንደሮችን መጠጋት እንዲቅታት ሁሉ ፡ የዚህ አገር ሰዎች ደግሞ የባ ሰውን የተለዩ ሆነውባታል ። የምታምናቸው ፡ የምትተማመንባቸውና በቅርብ የሚገኙ ተዋበች ብቻ ናቸው ። ከሥቃይ ፡ ከሞት ጋር ሲታገሉ ፡ ራሳቸው ማጽናናትን ፡ ማስታመምን የሚፈልጉ እንጂ የሌላ ሞገትን የሚካፈሉ አልሆኑም ። ከገጽታቸው እንደ ተመለከተችው ፡ ሞትን የሚ ጠብቅ ለሚመስል ሰው እንደዚህ ያለ ነገር ግዋየቱስ መች ይገባል ፣ በዚህ ላይ የሰው ሁላ ገጽታ የሚጨፈግግ ነው ። ከትልቁ ራስ አለ ጀምሮ ደብረ ታቦርን እንደ ግል ጓዳቸው በመያዝ እስከ ትንሹ ራስ አለ ድረስ በእካባቢው ዘብኛ የኖረው ዘመድ አዝማድና ጀሌ ፡ ዘወትር የሚታየው ፡ እናጉሚውን ነፍቶ ግንባሩን አኮሳትሮ ነው ። ሚሽቱም ፡ ወዳጁም እን ደዚሁ ናት ። በሌላው በኩል ፡ ቴዎድሮስ ራት ወደ አለ ሥፍራ ሁለት ሦስት ቀን ሰንብተው ሲመለሱ ፡ መርዶ የሚተበላቸው እየመሰላቸው መላ ሰውነታቸው በሞንቀት እየተኮማተረ ስለሚቆይ ፡ የባለሟሎቻቸውና የሠራ ዊታቸውም ፊት ይህንኑ የሚያንጸባርት ሆኗል ። ሌላው ቀርቶ ወጅ በበዛ በት የማር አገር ፡ እንደ ጉንደር የአዝማሪ ዘፈን አለ መ ስማቷ ታንጉትን ዝር ሚታል ።

በአጠገብ ፈንታ ግን ፡ አንዲት ሴት ቴዎድሮስን እየመረራች ፡ እየረ ገመች ደብረ ታቦርን በታዘበችው ትውላሾች ። ታንኮት መጀመርያ የሰ ማንት ቀን ባለችበት ድርቅ ብላ ነበር ። ቴዎድሮስን እንደዚያ ብሎ ማን ደም ይሔዳል፣ ከቋሰው ድኖ በመጨረሻ በዘመቱበት የመረሰ ታሪክ ስለሆነ ንዘርጹ እንደ ነገራት የሎቋም ሴት ናት ። አብቷ ፡ የመጀች ተድላ መርአዘ ጋዝ ፡ ወንድሟና ባሏ እንደዚሁ የጦር ኻለቆች ነበሩ ። ባልዋ በውጊያ ላይ ይሞታል ። አብቷና ወንድሟ ተማርከው በገበያ ላይ ይሸቅጡባታል ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ ባሎቱት አካባቢ ሳይቀር አዮንት የሚከዘር ልቅሶ ዋነ ታወርድዋለች ። አገር ምድሩ ይሰማዋል ።

" ጠጅም እንዳያምረኝ ድሮ ጠዮቻለሁ
ሥጋም እንዳያምረኝ ቁንጣ ሰቅያለሁ
ቢሻኝ ከወንድሜ ከአባቱ አብላለሁ ።

አንድ አግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ
አንድዶ ለብልቦ አታዮሱ ይፍሯችሁ ።

ሺ ፈረስ ከኋላው ሺ ፈረስ ከፊቱ
ሺ ብረት ከኋላው ሺ ብረት ከፊቱ
ይህን ሳታይ ሞቶች ኮሶ ሻሎ እናቱ ።

ይህንን ሲሰማ ያባፊል ላመሱ
ማናትም ቢሏችሁ ምንትዋብ ናት በሉ ! "

እያለች ታወርድዋለች ።

ተይዛ ከቴዎድሮስ ፊት ትቀርባለች ። ከቁጣ ጋር በመገረም ፡ " በየደረሽበት ቱንሩቱ ታብለወለዋይኛለሽ አሉ ! " ሲሉ ይጠይቋታል ።

" እምና ! " ስትል በድርትና ትመልሳለች ። ምክንያቱን ይጠይቋ ታል ፣ ትንግራቸዋለች ።

ቴዎድሮስ በዙሪያቸው ለንበሩት ሰዎች ፡ " እሠ ! ዛሂያ እንዲህ ሁና ታመስግኝ ነው የምትሉት ? " ይሉና ሴትዮዋን ምረው ድርን ያዙ ላታል ። ምንትዋብ ግን ድርንዋንም እየተቀበለች ፡ ከጮጀም ደብረ ታቦር ድረስ ተከትላቸው በየዕለቱ እዳዲስ ግዮም እያወጣች ፡ አውንም መጎቱን ታወርድባቸዋለች ።

' ስሚ ከምሽታቸው ስም ጋር ሰለ ተመሳሰለ ነው ! የጮርቸች ዋና ስማቸው ምንትዋብ ነበር ። በኋላ ተለውጦ ነው የተለመደው ! ' እያሉ የሚቀልዱ አሉ ።

ሌሎች ምንትዋብን እንምርዋ በነዝን እንደ ተንካ ዕብድ በመቁጠር ነገርዋን እስከዚህ ዋጋ ባይሰጡትም ፡ ታንጉት ግዮሚም ሆነ እንደ ቅባት የሚሰረስር ዜማዋ ሚርት መስሎ ይሰማታል ። ስትጥየ ያደርጋታል ።

እንደ ጉና ተራራ እናት ሞጋግ ከማይለየው ከዚህ የራሷም ሆነ የሙሉው አካባቢ ሰሜት ለመራት አስፈቅዳ ወደ ጐንደር የምትሔድበትን አመቺ ጊዜ ስትጠብቅ ፣ እንድ ቀን ገብርዬ ከጋፋት እንደ ዋለ ሲመለስ ፣ " አባ ታጠት ይፈልግሻል " አላት ።

" አውን ! " ታንጉት እንደ መደንገጥ አለች ።
" አዎ ! "
" ተዳከመች እንዴ ! " ሰትል ጠየቀች ኩታዋን እየደረበች ።
" እሱ ነው እንጂ የባሰ የተዳከመው " አለ ገብርዬ ።
ሰትደርስ ቴዎድሮስ ከአልጋው ራስጌ ቁጋጣ መንበር ላይ ተቀምጠው፣ ሕገን እንደሚያቆላምጥ አባት የተዋበችን እጅ ይዘው ሲያሻሹ ፣ ሲያነ ላብሱ ፣ ሲያስተውሉ አገኘቻቸው ።

" ላሰቸገርሽ ነው እንዳች ! " አሏት ። ንግግራቸውን እስኪጨርሱ ዝም ብላ ጠበቀቻቸው ። " ወረይሉ እንደ ጥሩ ጠበል አለ ይላሉ ። ይገርት መሐዲ ነው ። ዛዲያ አገሩ ሁላ ሽፍታ ሆኖ ሰላሰችገረ ወዲያ ወዲህ ማለቴ ሰለማይቀር ፣ ታጠገብዋ እንድትሆኝላት አብረን እንሒድ ብዬ ነው ። በዚ ያውም ያው ተገብርዬ አትለዩም ማለት ነው ! " አሉ ትካዜያቸውን ሲደ ብቅ ያልቻለ የቀልድ ፈገግታ ለማሳየት እየሞከሩ ።

በዚህ ወይነት ፣ ከዚያ በፊት ደርሰባትና አይታው የማታውቀውን አስጨናቂ ጉዞ በበነጋው ጧት ጀመሩ ።

—2—

መጀመሪያ ለተነሡበት ዓላማ ከጉዞዋቸው ፍጻሜ የደረሱት ከዘጠኝ ወር በኋላ ነበር ።

የተዋበች አስከሬን በግሼን ግርያም ለመጨረሻው ጊዜ እንዲያርፍ ተደርጎ ፣ ሠራዊቱ ከቅጽር ግቢው ወጣ ብሎ ከሚገኝ ደልዳላ መሬት ላይ ሠፍሯል ። ቴዎድሮስ ጸልየው የግይቢቃቸው ይመስል ከቤተ ክርስቲያኑ ቅድስት ውስጥ ቀርተው ፣ ገብርዬና ሌሎች የትርብ ባለሟሎቻቸው ከቅኔ ማኅሌቱ ይጠብቋቸዋል ። ተዋበችን በሚመለከት ዝም ብሎ የሚሠሩት ጉና የሚሆኑትን ከግየት በተቀር ደፍሮ ምክር የሚሰጥ አልነበረም ።

ታንጉት ፣ ለጊዜው የምትሠራው ነገር ሰላልነበር ፣ ከአሳለፉት የሕይ ወት ማዕበል ትንሽ ያረፈች መስሏት ፣ በምሥራቅ በኩል ከዐጸደ ቤተ ክርስቲያኑ ዳርቻ ከጥድ ዛፍ ሥር ተቀምጣ ዙሪያውን ትቃኛለች ። ከአንድ በኩል የእግዚአብሔር አብ ሚዳ ተንጣልሎ ፣ ከሌላ በኩል የእምባሰል ተራራ ጭንቅላት ሰማይ የነካ መስሎ ይታያል ። እዝመራው ፣ ከብቱ ፣ ሽንተረሩ ፣ ዙሪያውን ያለው ትርዒት ሁሉ ውብ ነው ። ታንጉት ግን ዐይንዋ እንጂ ዐይነ ልቡናዋ ይህንን ሁሉ ውብ ትርዒት እያስተውልም

ነበር ። ሐሳብዋ አውንም በአንጻች ወይነት ማዕበል ውስጥ ነበር ። ሰሜታ ምን እንደሆነ በትክክል ሰዎቶ አይታወቃትም ። ጎበኘ ይሰግታል ። ተግላገልኩ የሚል ወይነት አርያታም ይመጣባታል ። ሰው ፣ ሰውን በጨ ናው እንዲህ ያፈቅራል ! ሰትል ትገረምና እንደ ቅናት ልትቀበለው የማትፈ ልግ አንድ ሰሜት ይቆነጥጣታል ። ራሀ ሁሉ ሰሜት ሲፈራረቅባት ፣ መነሻ የሆነው የጎበዋቸው ሀሳቤ ፣ ከፈታ እንደ ተዘረጋ የእግዚአብሔር አብ ሚዳ በሐሳብዋ ተንጣልሎ ይታያት ጀመር . . .

ተዋበች ያረፉት ፣ ቴዎድሮስ ፣ ሰሚሽታቸው ተሰግሚ እየርና ጠበል እየፈሰጉ ፣ እግረ መንገዳቸውንም በጊዘው ሽፍቶባቸው የነበረውን የዐመዱ በሽርን ተክታዮች ግራና ቀኝ በግሰበ ከሥፍራ ሥፍራ እየተዘ ዋወሩ ፣ ግራኝ ሚዳ ከተባለው ሥፍራ ላይ ነበር ። በጊዘው ታንጉት ደን ኒን ውስጥ አልነበረችም ። የተዋበች ያንገሙር ፣ ሠፈሩን በእሪታ ሰታደ ባልቀው ፣ ታንጉትና ሌሎችም ባለሟሎች ተሯሩጠው ገቡ ። ቴዎድሮስ ከንዳቸውን እንዳንተራሱት የተዋበች ሬሳ ፣ ራሳቸው በደን ሆነው ፣ እንዳችም ነገር ሳያዩ ፣ ዐይናቸውን ከፈት ሰፈታቸው ከምንም ላይ ተክ ለው እንደ ጨው ንዎድ ድርት ብለዋል ። ደምዕ እውጥተው እያለቅሱም ። ለጊዘው ዕንባም አይፈሳቸውም ። ዐልፎ ዐልፎ ብቻ በጉቲቱ ሲወሣወዙ የታቀፉትን ሬሳ እሹሩሩ የሚሉ ይመስላሉ ። ድንገት ዙሪያቸውን የቆሙ ትን ሰዎች በእንቅልፍ ልብ ወይነት ሲመለከቱ፡ 'በመጨረሻ ፡ በመጨረሻ — ታታ — አሰችኝ ፣ ታጠት ልትለኝ ኑሮዋል ? ወይስ ታገሥ ?' ሲሉ በእንቅልፍ ልብ አነጋገር ጠየቁ ። ሬሳውን ከከንዳቸው ላይ እንሥተው ያጋግፈው አቆሙዋቸው ። አሁንም ፡ ከምንም ላይ እንዳፈጠጡ ተገት ረው ከቆዩ በኋላ ፣ ድንገት እንደ ተሰበረ ብርሌ ፣ ሰቅሰቅታቸውን ባንደ ሰቀቁት ።

በበነጋው ፣ የቆላው ፡ የደጋው ፡ የሰሚንኛው ፡ የቤጌምድሬው ፡ የጉንደሮች መረግዶ ልቅሶ በየዘርፉ ፡ በየተራው እየወረደ የግራኝ ሚዳና ሌሊቱን ተጉዘው ሊደርሱ የቻሉት የአካባቢው አደባራት ካህናት ጸሎተ ፍትሐት ሲያደርሱ ዋሉ ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ በለቶስተኛው መኝል እየተዘዋወሩ ፡ እየየውን ሲለቁት ፡ ግጥሙን ሲደረድሩት፡ከነግጥሙ የልቅሶውን ዜማ ሲያወርዱት የሕዝቡ አንጀት ተበላ ። በሰቆቃው ተብ ላላ ።

" እጅግ ሥራ ወዋቂ ትናንትና ሞተች ፡

መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች " ብለው ፡ ቀረርቶ በገራው ድምፅ ልቅሰውን ሲያወርዱት ፡ በዚያ የነበረው ሁሉ ተንፈቅፍቆ የሚሚ ሽሽ መሰለ ። ያዘኑት ቴዎድሮስን ፡ ወደም ተዋበችን የሚወዱት ብቻ አል ነበሩም ። ቴዎድሮስን የሚፈሩ ፡ ከዚያም ወልፎ የሚጠሉ ሰዎች እንኳ ፡ ቁጣቸውን የሚያበርድላቸው ፡ ቅጣታቸውን የሚያስምርላቸው በማጣ ታቸው አብረው ሳያለቅሱ አልቀሩም ።

ተዋበች ፡ በጠና ከታመመ ጊዜ አንሥቶ የሸምብራ ቆሎና ንፍሮ እየ
ተመገቡ የከረሙት ቴዎድሮስ ፡

“ እስቲ ጠይቂልኝ ርቃ ሳትሐድ ፣

የሴት ወንድ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ ? ”

ብለው ግጥም እንዳወረዱ ከአጉበሩ ላይ ተደፍተው ተንዘፈዘፉ ።
እነሲቅመኢስ ዮሐንስና እነ ራስ እንግዳ ከአጉበሩ ላይ አስነሡዋቸው ።

በዚህ ዐይነት ሲለቀስና ሕዝብ ሲላቀስ እንደ ዋለ ቀብር ባለመፈ
ጸሙ ፡ እንዲያውም መቃብር ስንኳ ባለመቆፈሩ ፡ ለግላሪግ ግራ የተጋቡት
የግራኝ ሚዳ ደብር አለቃ ቀስ ብለው ፡ ራስ እንግዳን እግከሩ ። በጥቂት
ቅያሚ ለአሮር ጊዜ ታስረው ቆይተው በቅርቡ የተፈቱት ራስ እንግዳ
በበኩላቸው ፈት ለፈት ቴዎድሮስን መጠየቁን ስላልደፈሩ ሊቀ መኳስ
ዮሐንስን እግከሩት ።

ባዶ ሆዱን ሲያለቅስ የዋለው ጎበንተኛ ተደካክሞ ፡ በዳሱም ፡ በያለ
በትም ፡ የተቀመጠው ተቀምጦ ፡ የቆመው ቆሞ ፡ ለየብቻው እየቆዘመ
ዐረፍ ብሏል ። ቴዎድሮስ ከጎበንተኛው መኻል ወጣ ብለው ፡ ከወደ ጻር
በኩል ከእንድ ቋተኛ ላይ ብቻቸውን ተቀምጠዋል ። ሐሳባቸውም ፡ ዐይ
ናቸውም ፡ በዚያ ቦታ የሰም ። ይመልከትም ፡ አይመልከት ከግዶው
አደግስ ላይ ተተክሏል ። የተዋበችን ሬሳ እንደ ታቀፉበት ወቅት ፡ በዚያ
ሥፍራ አሉ – በዚያም ሥፍራ የሱም ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቀስ ብሎ ቀረ
በና ፡ “ አባ ታጠቅ ይህን ያህል መሆንም እያስፈልግም ” አላቸው ።

መልስ አልሰጡትም ። የሰሙትም አልመሰለውም ። ሐሳባቸውም ፡
ዐይናቸውም አድግስ ላይ ፡ ከሩቅ ባዶ ላይ እንደ ተተከለ ቀረ ።

“ አባ ታጠቅ ! ”

ቴዎድሮስ ፡ ከእንቅልፍ በድንገት እንደ ባነነ ሰው ዘወር ብለው ፡
‘ አቤት ’ የሚል መልስ የሰጡት ሦስት ጊዜ ከተጣራ በኋላ ነበር ።
በጩኸት ልቅሶ የግደወጣው ፡ በቃላትና በንግግር የግይገለጸው የዘምታ
ሰቀቀናቸው አስጨንቆአቸው ሊያይ መጠየቅ ከበደው ። “ የቀብሩ ነገር
እንዴት ነው ! ” አሰ ከብዙ ማመንታት በኋላ ።

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ፡ በኋላ ለእነገብርዬና ታንጉት እንደ ነገራቸው
ወዲያው መልስ ስላልሰጡት በጉዳዩ አልገፉበትም ። አንዳንድ ጉዳዮች ፡
ሕይወት ውስጥ ዘልቀው ከመግባታቸው የተነሣ ፡ ባለቤቱ ራሱ እሞ—
በጊዜው ካልወሰዳቸው በስተቀር በሌላ ምክርና ግሳሰቢያ እልባት እንደ
ግያገኙ ያውቃል ። ቴዎድሮስንም እውን ይህንን የመሰለ ሁናቴ ገጥሟ
ቸዋል ። የባሰውን ከግበሳጨትና ከግወረጨት በስተቀር በምክርና
በሐሳብ ሊረዳቸው እንደግይችል ተሰግውና ከሐሳባቸውና ከሠቀቀናቸው
ጋር ተዋቸው ።

ቴዎድሮስ ፡ ሐሳባቸውን ለብቻቸው አምጠው ውሳኔያቸውን ወል
ደው ያደሩ ይመስል በበነጋታው ፡ የተዋበችን አስከሬን በሣጥን አስክት
ተው በመቅደላ አግጣጫ ወደ ጫኻል ወሰ ጉዞው ተጀመረ ።

ከላይ የነሐሰው ዝናም እምብዛም ሳያቋርጥ ይወርዳል ። ከታች
መሬቱ እንዳለ ሞታ ነው ። እቀበት ሲወጡ ወደ ኋላ ያንሸራትታል ።
ቁልቁለት ሲወርዱ ወደ ፊት ያዳልጣል ። ችግሩ ግን ይህ ብቻ አልነበ
ረም ። ቴዎድሮስ ፡ ተዋበች በታራሣ ስትሔድ እንኒ በከብት ላይ ናዱም አልቆ
መጥም ስላሉ ፡ የኮርቻ ከብት የያዘው ሁሉ እንደ ርሳቸው በእግሩ መንገ
ነበረበት ።

በየሥፍራው አደጋ ከሚጥሉ ሽናቶች ጋር እየተዋጉ ፡ የቆሰለ እስኪ
ታክም ፡ የሞተ አስኪቀበር የውሱና የአዳር ዕረፍት እየተደረገ ጉዞው
ቀጥሎ ከብዙ ቀናት በኋላ በሽሎ ወንዝ ደረሱ ። ከዚህም ጥቂት ዕረፍት
ተደረገና አስከሬኑን የተሸከሙት ሰዎችና አብዛኛው ሠራዊት ወንዙን
ለመሻገር ቀድሞ ተነጣ ። መሻገሪያው የበሽሎ ወንዝ በስሩት የተንጣለለ
በትና ረጋ ብሎ የሚወርድበት ሚዳ ቀመስ ቢሆንም ፡ የነሐሰው ከረሞት
ውሃ መጠን እስከ ወገብ ይደርስ ነበር ። ብዙው ሰው ፡ ቃሬዛ የተሸከሙ
ትን ሰዎች ከፈትም ከኋላም ከጉንም ከቦ እየተጠባበቀ ዋና የሚችለው
የግይችለውን እያደፋፈረና እየረዳ ፡ ቀደም ያለው እያቋረጠ መውጣት
ሲጀምር ትርምስና ሁካታ ተነጣ ። ያራሽ ሙላት ድንገት ከወንዙ አናት
በኩል መጥቶ ገና በመሻገር ላይ ያለውን ሠራዊት ያሳጋውና ያጸፋው
ጀመር ። ዋናተኛውና ሽክም የሌለበት እንደ ምንም መዝለቅ ሲችል ፡
ቃሬዛ ከተሸከሙት መካከል ሁለቱ ዋና የግይችሉ ናር ነፍስ ውሂ
ነፍስ ግቢ ሲወራጩ ለቀቁት ። የቀሩት ብቻቸውን መሸከም እቅቷቸው
ከእጃቸው አፈተለከ ። በዚህ ጊዜ ፡ ከወንዝ ወዲህ ግዶም ፡ ከወንዝ ወዲያ
ግዶም ፡ “ እረ ቃሬዛው ! እረ ቃሬዛው ! ” የሚል ጩኸት ሲያስተጋባና
ቴዎድሮስ እንደ ሞር ተወርውረው ወንዙ ውስጥ ሲገቡ አንድ ሆነ ። ሴላ
ውም እየተሯሯጠና እየተዉጨጨኸ ተከተላቸው ። በቅጽበት በሽሎ ወንዝ
በሰው ተሞልቶ ፡ ዋና የግይችለው ብቅ ጥልቅ እያለ ሲደፈቅ ፡ የሚችለው
የሙላቱን ግፊት ለመከት ሲወራጭ ፡ ቃሬዛውን ተከትሎና በውሃውም
እየተገፋ ሁሉም ወንዙ ወደሚወርድበት አግጣጫ ሲነጉ ፡ የበሽሎ
ወንዝ ብርብራ የተጨመረበት ባሕር መስለ ። በመጨረሻ ቃሬዛው አንድ
ሁለት መቶ ክንድ ርቀት ላይ በወደቀ ግንድ ታግዶ ከወንዙ ጥግ ተገኘ ።
በመካከሉ ብዙ ሰዎች በሙላቱ ተወሰዱ ።

ሁሉም በሁናቴው ስለ ተደናገጠና ሙንፈሱ ስለ ተነካ ፡ የፅሰቱ ጉዞ
ፍጹም ጀምታና ጸጥታ የሰፈነበት ነበር ። ዐልር ዐልር በለሆሳስ ከሙን
ጮክሾክ በስተቀር ስለ ደረሰው አደጋ ስንኳ ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚነ
ጋገር አልነበረም ።

ወዲያው ሀሎት በደን በትቪሌን ጥበት ምሳ መብር ሆነ ። ያንኬ ጥዋት እቀዋኛው ሰው የሚታየኝን ቀጣዩን ፡ በምንደነው እንደ ተመሳሌ ። ቀምድርስ ወደሱ እንደ ነጭ ሥራውው ቀን ብዙው ብርቅውን ወደ ቀነቱ አሩት ወጡ ፡ ብርቅውን ከሌሳቸው ጋር ስመጠየት ። በቋር በቋር ሥሚገኝ ቀዳዳ ብቋዊ ። በልም ከሚጮት እንጎንድ ከቀኳሉት ጀበቱቱ ፡ ወደሌሌ ጀመር ከሥቸረጋው ሰማይ ሥር ድቅድቅ ሌሊት ወሰጥ ሰቀናል ። ከቁኑ እየጋ ጀርሰ እሳት ጭመጣጠል እንደ ወገኛል የተቋጠረ ይመ በል ፡ ከመራዊቱ መሬር በንኳኩ አንጎዥም ሰባት ምሌከት አደረጉም ። ቀምድርስ ከእንድ ቁጥያ ጥግ ድንገቱ ዛፍ ከዘሀ ሥሌም ጋር ተፋጠጠው ተቁመው ። ከዘሀ ወደ ጎት ስረጅም ጊዜ ቁመጠው እንደ ቆዩ ኪሶት ከሰጉቱ ጉን የገው ድምፅ እንደ ነፋስ ገውጭ መጠሰሙ ። ድምፁ እየቀረበ ሲመጣ የሰዎት ብዎች ቁውጭት መሆኑ ገደ ። ቀምድርስ ከተቁመጠበት አሌተነቀሳቀሰ ብም ። የተቀገቡት ሰው ቢጠራ የሰበውን ገልዎቅ ፡ ድርቅ እሱ ። ሁሇቱ ብዎች ብኤሰጠሳቸው ሰማሌፍ ቱቀርገው ነበር ። ግን ከቁርፃንው ጥግ የተቁመጠውን ሰው እሰኞ ። ግንም አንቀሌቅሳቸውና እንደማያሰማ ችው የሌማት ቁውውታቸውን ቀጠለ ።

" እረ ምን ያህል ቢመጥት ነው እባክህ ? "

" ሶገን መውደድ አሌሰውም ። ሌክፍት እንጂ ! ሌመሆኑ በጋት ሥሚ ሆን ይመስልሃል በውየ የተመከደው ሰው ? "

" ምኑ ታውቆ ፡ አሌቅርም ቀምድርስ የባሰውን እንዲያገኝ ብሰው ነው መበሰኝ ፡ ተቄጥር እንዲታወት እሌፈሰጉም ። "

" ኤዲያ ! ምን ያዝናል ብሰህ ነው ? "

" ለምን እያገኘንም ሠራዊቱ በውየ ሊወሰድበት ? "

" ቢያንሰግ ኖርን ተመሠረቱ የነበሰበት ሬግ ተሸከም አገር ታገር እያን ከራቱተ በውያ መሳት ሊያበሰርርን ይሰግ ነበር ? "

ቀምድርስ ፡ የበው የውን ንግግር መሠረረ እሰሰሙትም ። መሳ በው ንታቸው ነገር እሳት ውበየ እንደ ተሠመረ የተየ ገል አርር ያሰው ፡ " የበሰበሰ ሬግ " የሚሰውን ቃል ቢሰሙ ነገር ። ጀርዋቸውን ሚመን አቃታቸው ። ተዋበቸ የነበሰበሰ ሬግ ሰመሳል ቢቃት ፣ ሰዎቹ የተፈጥሮ ሚታቸውን አግኗተው አሰኪመሰሱ ድረስ ቀምድርስ ከተቀመጠበት እንደ በድን ያረቀው ቆዩ ። ከዘያ ሰዎቹ ወደ ማደሪያቸው ሲመሰሱ በእንድ ሥውር ጎጆ እንደሚሰብ ኮሳያቸውን አየፍተው ተከተሰዋቸው ።

ቀምድርስ ፡ "የበሰበሰ ሬግ" የሚሰው ቃል በሰዝን ሰዎናቸው እንደ ነው ያንድ እያበተጋባሰቸው ፡ ከገፈረታውን እየነሰሰ ፡ አገኝታችውን በእንጀ ታቸው እየሸሰ በወያሰቸው እንቅሰፍ ዝር ሳያሰ ነን ።

ዙት ሁለቱ ብዎች ተያነው መተቀው ችጭት ተመሰው ። ከሰሳቱ ሰዎች ሁሇገች ሳስ ሆነ ። ሰሆኖ ቀሌ ስትናገው እንደ ተናገረው ቀምድርስ ሰዘ ሀሎታቸው መሰሰት አሇቅታችውም ።

ሰንጨት ተሰገበበው ነው ሁለ ሊገሬም ፡ ቀምድርስ ከተቀመጠበት ቀጠመና ሌቀባበቸ ጉን ጩመ ። ግን ከዘያ በሌሳም አንድ ጊዜ አሌደገመት በዘ ነገር ሰተመሇቸው ሩጩም ከዘያ ነገር አልሠገባቸውም ።

" ፍረቱ ፡ ወደ ፍረዱሌኝ ፡ ወደ ፍርዱሰኝ " አሰ ቀምድርስ ብቸ ሰዮት ስተገበበው ነው ።

" እኔን የገሰህ ምን ይሰኖሌ ? " ሲሰ ወየቁ ።

" ይቅሳሌ " ምሊሌ የብዙ ነው ድምፅ አሰቀጋገ ።

" በምን ይቀሳሌ ? " ቀምድርስ እንደገና ወየቁ ።

" በሞት ። "

" ብልና ሚነት ሰብት አትሌ ይሰኑ እንጂ አንድ አምሳሌ ዋኖው ተዛፀሌ ። ነውም አሇሌሌ ? " ቀምድርስ ከውገሳቸው በገዲጉና በቁግ መቃወሳቸው ሊያበታተሰቅሮ ሬጋ ብሰው ሰመታየት ሞከሩ ።

" ነው እንጂ ! "

" በወሊሠም እኔን የገሰህ ተዋገሾችን ሰዛህ ፡ ተዋገሾችም የገሰህ እኔን ሰደህ ማሰት ነው ። ነውም አደሇሌ ? "

" ነው ። "

" እረ ነው ። "

" ምን ጥርጥር አሰው ? "

" እንጉሊያው ደብ ሰው " አሰ ወደ ከሰሰት ሰው አጀቸውን ዘርግ ተው እያመሰከቱ ። " ትናንት ማታ ተዋገሾችን ያገሰን ነውር ሰድር ሰድግ ሰያ ቢታል ፡ ሰድሰኖል ፡ ወደሰ ትከሇህ ? " ሰሰ በሰውየው ላይ አፈጠጡ ሰት ።

በዘያ ሙቅት ፡ ሰድካም ና ሰድንጋጤ ሰሚት የተናገረው እንጂ ከልሙ አሰመሆኑን ገሌጾ ጥሩቱን እምኖ ም ሕረት ቢጠይቅ ፡ ቀምድርስ ም ን እንደ ሚያሰርጉ እርገጠኛ ያልሆኑ ይመሰል በትገባበት ተመሰከቱት ። ሰመየው ግን ሠርቶ ተሰሩ በመቁረቱ ይሰን በመታገይ ሳያከተባብልም ፡ እምኖ ይቅርታ ሳያጠይቅም ዝም ብሎ ቆመ ።

ይህ ሁኔታው ቀምድርስን የገሰ አብግኖዋቸው ፡ በይሌቸውን መገ ሙ ሰመሰገገር የገጀሰ ከመሰሰ በጋሌ ጥርሳቸውን ነክሰሙ ጉቴት ። እንድ ጊዜ ፍርድ ከመየቁ በዘያው ማሰት አሰበት ።

“ እንግዲያው ፍርድ ስጡኝ ” አሉ ።
“ ምን ጥያቄ አለው ! ይቀጣል ። ”
“ በሞት ይቀጣል ። ”
“ ሞት ይገባዋል ። ”
“ እንገቱን ለሰይፍ ። ”
“ በስቅላት ። ”
“ በድንጋይ ተወግሮ ሊገደል ይታየኛል ። ”

ፍትሕ ለመስጠት ያሰበውም ፣ ቴዎድሮስን ለማስደሰት የፈለገውም እየተነሣ ብያኔውን አሰማ ።

ቴዎድሮስ ፣ ከዚህም ከዚያም የቀረቡትን ትችቶች ከአዳመጡ በኋላ ፣ “ ፍርዳችሁን ከሰጣችሁኝ ፣ በሞት እንዲቀጣ ከፈረዳችሁበት የአገዳደሉን ዐይነት እኔው እወስናለሁ ” አሉ ፡ ሰውዬው አሁንም አንዳችም ዐይነት ፍርሃትና መርበትበት ባለማሳየቱ በንዴታቸው ላይ እየተገረሙ ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ አንዳችም አስተያየት አላቀረበም ነበር ። ቴዎድሮስ ከሌሎቹ ይልቅ የርሱን ምክር እንደሚያዳምጡ ቢያውቅም ፡ በራሳቸው ሐሳብ የሚመሩበት ጊዜ ደግሞ አለ ። በሰውየው ላይ ሞት ለማስፈረድ ወስነዋል ። የፈለጉትን ፍርድ ካገኙ በኋላ ፣ ምናልባት በመ ጨረሻ ምሕረት ያደርጉለት ይሆናል የሚል ግምት ነበረው ። አሁን ሰውየው በሁለት ወታደሮች የፈጪኝ ተይዞ እየተጓዙ ቴዎድሮስ ቀድመው እየመሩ ከመረሩ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው ሜካ ሲወሰድ ሊቀ መኳስ ዮሐ ንስ ፊቱ በርበሬ መስለ ። ከንፈሩን እንደ መንከስ አደረገ ። ከሜካው ውስጥ እስኪሰወሩ ድረስ በዐይኑ ተከተላቸው ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቴዎ ድሮስና ሁለቱ ወታደሮች ተመለሱ ።

የሆነውን ሁሉ ሳይነገረው ዐወቀ ።

ቴዎድሮስ ፡ ከምሳ ያልበለጡ ሰዎች ይዘው በጽሬ ከቨፈቱ ወዲህ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ፣ በዚህ ቀን ጉዞ ፣ ከመሬዊታቸው መካከል ከመቶ የሚበ ልጡ ከድተዋቸው መዋላቸው ማታ መፈር ሲደረግ ታወቀ ። ቴዎድሮስ ግን ፡ በነገሩ የመታከትና የማዘን እንጂ የቁጣ ስሜት አላሳዩም ።

ይህ የመሬዊታቸው መክዳት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አልሆነም ። የመሬዊቱ መ ክዳትና ጉዞውም ቀጠለ ።

አንድ ቀን ማታ ኻውን ፡ ከቨፈቱው አገር እየተንዳ ከመጣው ከብት ታርዶ መሬዊቱ ጥብሱንም ፡ ጥሬ ሥጋውንም ሲመገብ ፡ ቴዎድሮስ የሸምብራ ቆሎ በውኃ ሲያወርዱ ፡ ሊቀ መ ኳስ ዮሐንስ በጎዘኢታ እንደሚያስተውሳቸው ተመ ልክተው ፡ “ ሁኻም በጣም እንዳዘንክብኝና እንደ ታዘብክኝ ፡ አንድና ውሰት የለውም ” አሉት ።

“ በምን አብ ታመጣ ? ” ሲል መለሰላቸው ።

“ እሄሄ ! አሁን ግን ይሙት አጥተኽው ነው የምትጠይቀኝ ? እንግ ሊዞች በነገር ቁጥቦች ናቸው እንደሚባለው ፣ መቸም እንተ ሀገራችንን ወደህ ፣ ኢትዮጵያዊ መሆንህ ባያጠያይቅም ፣ የዘር ጠባይህ አለቅህ ብሎ ነው እንጂ ” አሉት ቴዎድሮስ ፣ ላመል ያህል የትካዜ ፈገግታ እየታየባ ቸው ። “ ሌላው ቢቀር ሰውየውን ስቀጣ ቀይ ፊትህ ምን ያህል በርበሬ እንደ መሰለ ተገንዝቢያለሁ ። ተዚያም ወዲህ እንደ ወትሮህ ለኔ ምክርና እስተያየት ያልከጀልከው ያለም ህኖት አይደለም ። የመራሁት ሥራ ስሕ ተት ቢመስልህ ነው ፣ ይታወቀኛል ፣ ግን አትፍረድብኝ ፣ ወድጀን አይ ደለም ” አሉ ቴዎድሮስ ፣ በቅሬታ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

“ መቸም ‘ ከሰው ስሕተት ከብረት ዝገት እይጠፋም ’ ተብሏል እባ ታጠቅ ። እንግሊዞችም ፡ ‘ የማይሳሳት የማይሠራ ብቻ ነው ’ የሚል እነ ጋገር አላቸው ” አለ ሊቀ መ ኳስ ዮሐንስ በማጽናናት አኳኋን ።

“ እሱማ ነው ። ግን ስሕተትኮ ላያውቁት የሚሠራ ነው ። እኔ ግና ታውቆኛል ። ዛሪያ ምን ላድርግ ? የተዋቡ ነገር ሆነብኝና አላስችል አለኝ ። እህ ፡ ስለ እኔና ስለተዋቡ ከሁለታችን በቀር ማንም በሚገባ ሊገነዘብ የሚችል የለም ። ቢቀልም ግስረዳት በጣም ያስቸግራል ። ተዋበች ለኔ ሚስት ብቻ አልነበረችም ፡ ሁሉ ነገር ናት ” አሉና ቴዎድሮስ የትዝታ ሰመመን እንደ መውሰድ አደረጋቸው ። “ ንዱሕ ፡ ቀና ፍጡር ነበረች ። በአሳቢነቷ ፡ በፍቅርዋ ፡ በርኅራሄዋ ፡ የእናቴና የእናት ሀገሬ ምሳሌ ናት ። ሲከፋኝ የምታጽናናኝ ጋሻዬ ፡ ሳጠፋ የምትመክረኝ መምህሬ ናት ። ዐመሌን ፡ ጉዴን የምትሸፍንልኝ ፡ የምትደብቅልኝ የምሥጢር ሙዳዬ ናት ። እሪ ምኑን ብዬ ልንገርህ ? ” ቡና እቅርባ ከአጠገብ የተቀመጠችው ታንጉት ጭውውታቸውን እንደምታዳምጥ ተመለከቱና ፡ “ እውነቴን አይደለም እንጎች ? ” ብለው ንግግራቸውን ቀጠሉ ። “ ዛሪያ እንደዚህ ያለችመን ፍጡር ላያውቃት ፡ ሳትበድለው ለእፍ በሚከብድ ፡ ሲጀር በሚቀፍ ቃላት ሲያንጓጥ መታገሥ እቀተኝ ። ምሕረት ማድረግ እልመን ልህ እለኝ ። እና እትፍረድብኝ ሊቀ መኳስ ። ”

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ መልስ ወይም እስተያየት አልሰጠም ።

“ በከረምት ሙላት ባንድ ፈት የተዋወን እስከሬን እቨኽሚ ፡ በሌላ ፈት ያገሬን ጥሩቷን እንጂ ልማቷን የማይወድ ወንበዴ እያሳደድኩ ፡ መራዊቴን አገር ሳገር እያገከራተትኩ ማንሳሳቴ ብዙውን ሰዉ ደስ እንዳሰኘ ኸው ይታወቀኛል ። ታስበለዚያማ ፡ መራዊት ከሌላ እሳኸሳ ወደኔ ይገባ ነበር እንጂ ወች ከድቶኝ ያውቅ ነበር ! ዛሪያ እሁንም ቢሆን ወድጀን አይደለም ። በስግይ ነፍሲን ይማርና ተዋበ በሕይወትዋ ቁርው ምኞቷ እያሩሳሌምን መሳለም ነበር ። እኔም ብሆን በሕይወቷ ያልተባኸሳትን ፡ ዲሆን እስከሬንዋን እያሩሳሌም ወስጂ ቀኸው ዚደር ሥልጣን ነበም

ባሳርፈው እወድ ነበር ። ግን አያሩላለም በቱርክ ተይዘ የማይቻል ተሆነ ፣ ሌላው ቢቀር አስከፈንሞን ከየሩላለም የመጣው ማግደ መስቀል በተቀ መጠበቅ በማሸን ማርያም እንዲያርፍ ማድረግ ፣ ልፈጽምላት ፣ ላድርግላት ፣ ላሚላላት የሚገባኝ ትንሽ ነገር መስሎ ስለታየኝ ነው ። ''

'' እም አባ ታውስት ፣ ሰው ለሚያፈቅረው ከዚህም የበለጠ ፣ ከዚህም የከበደ ያድርጋል ። ለሌላው በሕተት መስሎ ቢታይ ፣ ለሌላው ችግር ቢመ ስለው ፣ ለእርስም ትክክል ነው '' አለ ሊቀመኳስ ዮሐንስ ብግጽናናትና ዮንዘናቸው ተከፋይ ብመሆን እኳኳን ፣ ''ግን ደግሞ ነዘንን በልኩ ማድረግ ተገቢ ነው '' አለ መልሶ በምንዘር መልክ ፣ '' በንዘን መኮማተር ራስን መጉዳት ብቻ እንጂ ሚችን አይመልስውም ። መቸም ሰው ሆኖ መሞት አይቀርም ። ብቻ እንዳ ቢቀድም ፣ ካለጊዜው ቢቀሙ ሰቀቀን ላይ ያጥ ላል ። ዛሬያ ከሆነ ብእላ እየተበረታቱ እየተጽናኑ መሔድ በሕይወት ያሉ ሰዎች ተግባር ነው ። ታላበለዚያማ ሕይወት ትርጉም አይኖረውም ። ''

'' ታልክስ ሕይወቱ ከፈል ትርጉሙን አጥቷል ። ለሕይወትሁሉት ትርጉሞች ይገር ነበር ። እንድ ለሀገሬ ያለኝ ዓላማ ፣ ለፃው ተሞቡ ነበረች ። እንዱሞን እንሆ አጥቻለሁ ። በእንደኛው አስከሆነልኝ አዘግማለሁ ። ምክንያቱም ዋናውን ዓላማዬን የምታግዝኝ አርቢ ነበረቻ ! ''

'' ቢሆንም ፣ መንፈስን አለማመክ ፣ አለማስፈሩት ነው ። ጠንኑትን ከመጉናት በስተቀር ምንም አይጠቅም ። ''

'' ግዲለህም ፣ አታስብ ፣ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ። ተሞቡ ተዘላለም ቤትሞ እንድታርፍ ታደርገሁ ፣ የጌም መንፈስ እንደ ምንም ዐረፍ ያልልኝ ይሆናል '' አሉ ቱምድርስ ።

ቱምድርስ ፣ በመሉ ቨናቷል የሚባለውን እየቀጡ ፣ የነመደ ብሽር ቀንደኞች ናቸው የሚባሉትን እየተከታተሉና እየመቱ ፣ የተሞብችን አስከ ፈን እንደረዙ ብዙ መሬት ከተንከራተቱ በኋላ ፣ ግሸን ሲደርሱ በቪህ የሚ ቋጠር መራሞት በየቦታው እየከፍ ቀርተባቸው ነበር ።

በግሸን ማርያም ፣ የቱብሩ ሥን ሥርዓት በሰባት ጉዞ ፍታት የተከ ናወነ ቢሆንም ፣ መራሞቱ በመ ንገድ ብዛት የተናከሙ ፣ የመስ ሕዝብም ፣ እየበረገ ከአትራቢያችው የሚልሽ ሰልነበር ፣ እስከዚህ የደመቀ አልነ ብረም ። ቱምድርስ ግን ፣ እንደ ነገሩ አንድ ከባድ ሽከም የመረደላቸው መሰ ለው ነበር ።

ታንጉት ፣ እንደ ሕልም የሚመስለውን የተሞብችና የቱምድርስ ፣ ''የፍ ቅር መጨረሻ ጉም'' - ሴላ ትርጉሚ ሰላሳችልት ፣ እንድ ጊዜ ያዝ ታል መቁቶ ቁት ነበር - በሐጎብሞ ተጉላ ስትጨርስ ከዚህ በኋላ ፣ የሚሰው ጥያቄ መሞባት ። ያም ታሞዝኝ አርቢ ነበረች ብሏል ! እኔስ እንዳግዘው ሥች ወሰ ቀኝ ! እንደሚያሳድጉት ልጅ በጾነት ከመቁመር በስተቀር ። ሊገዥ እጥቶ

እንጻነከስ ይቀር ይሆን ! መይስ ተሞብችን መይስ የተሞብችን ፍቅር የሚተ ካለት ያገኛል ! ቢያገኝ ይስ ይላታል ! ይከፋታል ! ስሚያ አለየለትም ። በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ስዓሞን ነበር ፣ ከእላሞ በርከት ያለ የሰው ኩቤ የቀሰቀሰት ። ቱምድርስና የቅርብ ባለሟሎቻቸው አርቢ ወደ ተቀመጠች በት አማጣሜ በሙ ምጣት ላይ ነበሩ ።

— 3 —

ቱምድርስ ፣ ፈታቸውን ወደ ደብረ ታቦር ካዞሩበት ከግሸን የብዙ ላም ንታት መንገድ ርቆ ፣ በጉንደር ከተማ ፣ ጠጉሬ ልውጥ ፣ ቀለሙ ልሙጥ ፣ በተለዩ ስሜት ፣ ለተለየ ዓላማ ስለ ተሞብች ሞትና ፣ ስለ ወደፊቱ የቱምድ ርስ የጎቅር ዕድል እንደዚሁ ታስባለች ። እሷም ሚስስ ርዚንታል ናት ።

ቱምድርስ ፣ ሥልጣን ከመያዛቸው በፊት ሆነ በኋላ ክርስትናን እንስብካለን በማለት ፣ በሃይማኖት ስምና ልዩ ልዩ ጥናት ለማድረግ ከመጡት መካከል ፣ ሚስተርና ሚስስ እስተርን ፣ ሚስተርና ሚስስ ፍላድ ፣ ሚስተርና ሚስስ ሮዚንታል የተባሉት የስኮትሽ ሚስዮናዊ ማኅ በር አባላት ይገኙበታል ። ሚስተር እስተርን ቀደም ሲል መጥቶ ከሔደ በኋላ ሁለቱን ሌሎች ባልና ሚስት ያመጣቸው በሁለተኛዉ ጉዞው ነበር ።

ቱምድርስ ፣ ገና ራስ አሊ ቤተ መንግሥት ከነበሩበት ጊዜ እንሥቶ ስለ ወጭ እንር ሚስዮናዊያን ሮቸርጣፊ አመለካከት ነበራቸው ። ምክንያታ ቸው ፣ ሃይማኖትም ፣ ሀገርም የሚመለከት ነበር ። ራሳቸው እጥብቀው የሚያምኑትን የእርቶዶክስ ተሞሕዶ ሃይማኖት በሚመለከት ረገድ ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፣ ከአፈሶን ጉባኤና ከቅዱስ ቁርሎስ ጋር በመተባበር ፣ ሥነን ከመለኮት ነጥሎ ፣ እካልና ባሕርይን ከፋፍሎ ፣ የስ በኬ ንስጥሮስንና ተኪታሮቹን መርታቲን ፣ በኋላም በመርቅያን ፣ በዐርክ ልያን ፣ በር ማው ጋጋ በልየን ቀኖማዊ እንግሽነት በኬልቂዶን የወሰኑ ትን ሁሉ እንደምታመግዝ ያምናሉ ። ያምንቢታል ። የሀገርን ሰላምና ደኅ ንነት በሚመለከት ረገድ ፣ በአጼ ዩስንዮስ ዘመነ መንግሥት ጴጥሮስ ፕጴዝ የተባለው ሚስዮናዊ ባስፈጨው የኳቶሊክ እምነት ምክንያት የተ ነሣው የእርስ በርስ ጦርነት ፣ በጉጂም በቢጌምድር ፣ በትግሬና በላስታ ብዙ ሺህ ሕዝብ ያስደጀ መሆኑን ፣ በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የብዙ ሰው ደም ማፋሰሱን ፣ እንድ ጊዜ እዘዞ በተባለው የኦጨጌው መናፈሻ ሥፍራ ላይ ብቻ በብዙ ሺህ የሚቁጠሩ የተዋሕዶ ያይማኖት ተከታዮች ልመጨፍጨፋቸው ምክንያት መሆኑን አሮምሪው ያወ ቃል ። የኦክሙች ኢትዮጵያን ለማንሣት ዓላማ እይተው ሥልጣን ቢያዙበት ወቅትም ቢሆን ፣ ዋንት ብርቱው የሕዳት ፣ በኋላ የመጡት ሚሲዮናውያን ፣ ንዩም ከጎም ይሚጋጨት ፣ ከርስቲያን ከክርስቲያን በማለት የሚያደርሱት ጉዳት እንደ ተመለ ነበር ። ይሁን ሁሉ በሚገባ በመገንዘባቸው ቱምድርስ ሚስዮናውያንን ሁሉ የሚመልከቱት በተዛቻም ሲሆን ከፍ ሲል ቩሥንት ፡ ጀት ሲልም በንቀት ነበር ። እንድ ጊዜ ቆንስል ፕጳውሊን ምክንያቱን

ቢጠይቃቸው ፣ በሃይማኖት ምክንያት በየዘመናቱ የደረሰውን ጥፋት ከተረኩለት በኋላ ፣ "ባዲያ አውንም የሆነ አንደሆነ ፣ ይኽ ሁሉ አልበቃን ብሎ ነው ፣ ተመልሰን ታጥቦ ጭቃ የምንሆነው ! አሁንም ቢሆን ለግሙ ፣ ለግተራሙሉ ፣ እንአራት ወይና ጉሹ መቸ አንሱኝና ነው ተዉግሪ በጥባጭ ከባሕር ግዶ የግስመ ጣው ?" ብለውት ነበር ።

የታወቁት የትኔ መምህር አራት ወይና ጉሹ ፣ የቅባቶች አፈ ጉባኤ ነበሩ ። በወቅቱም ከሞላ ጉደል በአንድ ፈት በቅባቶችና በጸጎች ፣ በሌላ ወገን በተዋሕዶች መካከል በየንዳግቴና በየደብሩ የሃይማኖት ትምህርት ከፍተኛ ክርክር እየተካሔደ ነበር ። በዚህ ላይ ፣ 'እንኳን ዘንቦብኽ እንዲያውም ጨዛ ነሽ' እንደሚባለው ፣ የሀገር አንድነት ገና ላይጸና ፣ የሽፍታውና የጸጥታው ችግር ሳያገስ ፣ ባዕዳን ያመጡት የሃይማኖት ሁከት እንዲሠመር ቴዎድሮስ አይፈልጉም ። 'ሳይቸገር ጢፍ ብድር' መሆኑን ያውቁታል ።

ያም ሆኖ ፣ ክርስቲያኑን እንደገና ቂደር እናጥምት አስካላሉ ድረስ ፣ በሕዝበ — ክርስቲያኑ መኻል ንብተው ባዕድ መሠረተ — እምነት እንስበክ አስካላሉ ድረስ ፣ ወይም በሀገርና በመንግሥት ጉዳይ ላይ ልባቸውን ለቂም ፣ ሐሳባቸውን ለተንኰል ፣ እንደበታቸውን ለበደል አስካላነሡ ድረስ ፣ ቴዎድሮስ ሚስዮና ችን በግልጽ እይታወሙም ነበር ። እንዲያውም የቱርክን የወረራ ሥጋት ከአስልምና ሃይማኖት መ ስፋፋት ጋር የተያያዘ አድርገው ስለሚገምቱት ለዚህም ኑግራኝ ጀምሮ ብዙ ታሪክ ምክንያት አላቸው — በተወሰነው አካባቢ አስላሞችንና አረመኔዎችን እያስተማሩ ክርስትና እንዲያጠምቁ ፈቅደውላቸዋል ።

እነ ሚስተር እስተርን የመጡት የኦሪት አማንያን የተባሉትን ፈላጶች ለማጥመቅ ነበር ። ቴዎድሮስም ፣ ሀገርና መንግሥትን በሚመለከት ረገድ ፈላጶችን እስከዚህአሳባቢ አድርገውባይቈጥሩዋቸውም ፣ከአራትነታቸው አንዳችም ዐይነት ክርስቲያንነት ሳይሻላቸው አይቀርም በማለት እስተርን ፣ በጀንዳ ፣ በትክል ድንጋይ ፣ በቸቸላ የጀመረውን ሥራ እንዲ ቀጥል ፈቀዱለት ።

ቄስ ሄንሪ እስተርን ግን በተወሰኑ ሥፍራዎች ፣ በሃይማኖት ተግባር ብቻ የሚወሰን ሰው አልነበረም ። በሃይማኖትና በሃይማኖታዊነቱ ፍጹማዊ እማኝ ነበር ። ከዚህም የተነሣ ራሱን ፍጹም ትክክለኛ ፣ ፍጹም ጻድቅ ፣ ፍጹም ሰማዕት አድርጎ ያያል ። በየትም ሥፍራ ፣ በምንም ጉዳይ ራሱ የሚፈጽመው ተግባር ትክክለኛ ፣ የርሱን ትክክለኛነት መቃወም ግን ኃጢአት መስሎ ይሰማዋል ።

ለዚህ ስሜቱ መነሻ ነበረው ። በእስኮትላንድ የድንች ረሃብ እልቂት ከቤተሰቦቹ መካከል ተርፎ የወጣ ነበር ። ይህንንም እግዚአብሔር ለትልቅ ሥራ መርጦት እንደ ፈጸመው ተአምር ይቈጥረዋል ። ከዚያም በሚስዮን

ትምህርት ቤት በኩል ወልፎ የቅሰና መንመላዕት ሲደርብ ፣ ክልጅነት ትዝታ ከወረሰው ምሬቱ ጋር አማምር የያዘውን የአስኮትሽ ግልፍተኛ ነቱን አላወለቀም ነበር ። ራሱን ከሰው በላይ አድርጎ በሚገምትበት የሐዋርያዊነት ስሜት ወደ የውን አገር ተጉዞ በዐረቦች አስልምና ሥር የንበሩትን አይሁዶች በእምነት ብቻ ሳይሆን ፣ በእካል ነጻ ለማውጣት ባደረገው ሙከራ ተይዞ ይታሰራል ። የታሰረው በዘላኖች ሠፈር ነበር ። በቴምር ተክል አካባቢ በተተከለ ድንኳን ፣ ያመራ የመሰለ እሳት እየተንቀለቀለ ፣ ጉራዴ እየተመዘዘ ሲታጣበት ፣ ሲርከበርበት ፣ አሁን ከአሁን እገተ ተቀንጠሰ እያለ ዐይኑን ከደና ሲጠብቅ ፣ ሞፍሮውና ፉከራው ጋብ እያለ ይሔዳል ። አብዛኞቹ ተዳከሙው ፣ ዝለው በየአሉበት ተጋድመዋል ፣ ተዝለፍልፈዋል ፣ ጉራዴያቸውን ፣ ጅራፋቸውን በተዘረጋ ክንድ እንደ ዉበጡ ። እስተርን ብድግ ብሎ ነፍሴን እውጭኝ ይፈተስ ኳል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ደግስቆ የሚሔድ የነጋዴ ቡድን አግኝቶ ፣ ለሀገሩ እንደገና በሌላ አገር ሥራውን ለመቀጠል ይበቃል ።

ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። ሴሎችንም አመጣ ። ነገር ግን በዐረብ አገር የሕይወቱን መትረፍ ፣ እንደ ተአምር ስለሚቈጥረው ፣ የሴሎችን ነፍስ ከማጣን ይልቅ ስለ ራሱ ከመታብር መውጣት ፣ ጉልቶ ይሰማዋል ። ብዙ ጊዜ የሚያወራውም ስለዚሁ ነው ። ለእንደዚህ ያለው ተአምራዊ ታሪክ እድናቂ የሚገኘው በከተማ ስለሆነም ፣ ከተመ ደቡለትና ከእቋቋማቸው የሚስዮን መንደሮች ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ የሚተመጠው በጉንደር ነበር ። ቴዎድሮስ ደግሞ ፣ ስንኳን አውሮፓዊ ሚስዮን ቱርቶ ፣ ኢትዮጵያዊ መኳንንቱም ቢሆን ያለ ምክንያት ጉንደር የሚተመጥ ለው እይመጹ ፣ 'ወይ ጋለሞታ ሲያጫውት ነው ፣ ወይ ተንኩል ሲያደራ ነው' የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው ። ሚስተር እስተርን አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፈው ከእቡን ስላግ ጋር ለመሆኑ ወሬ ደርሷቸዋል ። የጋፋት ሰዎች ስለ እነእስተርን የንጉሥዋቸው ምናልባት የተጋነነ ሊሆን ቢችልም ልብ የሚከነክኑ ነጥቦች ነበሩበት ። ነገር ግን ፣ ከስንቱ ጋር ተጣልቶ በሚል ስሜት ወልፎ ወልፎ እየገሠጹትና እየተቆጠቡ እንደ ዎ ንም ችለውት ፣ ታግሠውት ኖረዋል ።

ሚስስ ሮዜንታል ደግሞ ፣ ሕይወቷ ከእነስተርን ሚሲዮናዊ ሕይወት ጋር የተቈናጀው ፣ በሃይማኖታዊ ስሜት ፣ ወይም በሐዋርያዊ መንፈስ አልነበረም ። ሕሃን ሆና ስንኳ ፣ እንደ መሰሎቿ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አይማርካትም ነበር ። ሌሎች ልጆች እሑድ መጥቶ የነጭ ልብሳቸውን ለብሰው ቤተ ክርስቲያን የሚሔዱበትን ጊዜ በጉጉት ሲጠብቁ፣ ሮዜንታል ስለ እሑድ የምታልመው ፣ ከቲአትር ቤት ጋር በተያያዘ መንገድ ነበር ። ግን የሚስባትና የሚማርካት ተውኔቱ ሳይሆን በተለይ ለሴቷ ተዋናይ ተመልካች የሚሰጠው እድናቶት ነበር ። ከዚህም የተነሣ ፣ ወጣትዋ ሮዜንታል ኻያ ዓመት እስኪሞላት ድረስ እየተፈራረቀ ካደረባት ብዙ ዐይነት ምኞት ዋናው ፣ በድፍን አውሮፓ ስሟ የተጠራ ተዋናይ መሆን

ነበር ። ተውኔት ትምህርት ቤት ገብታ ሞክረች ፣ አልሆነላትም ። አስተ
ማሪው አንድ ሳምንት ከፈተናት በኋላ ፣ ‘ያንቺ ችግር ምን መሰለሽ ፣
ቲአትር ከመጫወት ይልቅ በሐሳብሽና በስሜትሽ ሰራስሽ ነው የምታ
ጨበጭቢው ’ ሲል አሰናበታት ። ከዚያም አንድ ልዑል አግብታ ልዕ
ልት ለመሆን ተመኘች ። ስንኳን ልዑል ደኅና ከበርቴ ባል አላጋጥማት
አሰ ። ያልተሳካ ምኞት ፣ ወደ እውን ያልተለወጠ ሕልም ፣ ብስጭትጭት ፣
ትብጥብጥ እያደረጋት በሔደበት ወቅት ነበር ከሚስተር ሮዜንታል ጋር
የተገናኘችው ። በውበቱም ሆነ በቁመናው ያማርከኸል ፣ በፍቅር ‘ይመ
ድቅልኛል’ ብላ ያሰበችው ወንድ ዐይነት አይደለም ። አፉ የገጉት የመ
ሰለ ነው ። ስብከት የሚያሰግበት ድምፁ ሳይቀር ያለልክ እንደ ተወጠረ
ጅግት ሲጠጥ የሚል ይመስላል ። ሚስዮኑ ከሚከፍለው አበል በቀር
ሌላ ሀብት የለውም ። ነገር ግን ፣ ለስብከቱ ወንጌል ኢትዮጵያ ወደሚባል
የጥቁር ሕዝቦች አገር እንደሚሔድ ሲነግራት ፣ ስተተጨ ምኞቷ መካሻ
ዕድል የቀረበላት ሆኖ ተሰማት። ነጭ ልዑል ልታገባባትችል በደንቆሮጥቁር
ሕዝብ መካከል እንደ ልዕልት ኻ ከበራለች ። በግሩም ተዋናይነቷ የሚያጨ
በጭብላት ፣ የሚያደንቃት ፣ ‘ፈርግዋን የሚለዎ ናት’ ተመልካች በእው
ሮታ ባታገኝ ፣ በአነብሮት የሚሰግድላት ጥቁር ሕዝብ ይኖራታል ። ብዙ
ዓመታት ቆይታ እንደገና ወደ ሀገርዋ ስትመለስም ፣ እስከ ዓለም ዳርቻ
ተጉዛ ስለ ፈጸመችው ገድል፣ስለ አዳነችው ነፍስ ስትተርክ ሰው ሁሉ በአድ
ናቆት ያዳምጣታል ። ሚስተር ሮዜንታልን እግብታ ወደ ኢትዮጵያ የመ
ጣችው ለዚህ ስትል ነበር ።

ወደ ኢትዮጵያ ከመጣች በኋላ ያጋጠማት ሁናቴ ግን ፣ እንደ ገል ፍር
ክስክሱን እወጣባት ። ሚሮንቱስ ከለበሰው ደሃ ገበሬ አንሥቶ ፣ የሚያደ
ንቃት ፣ የሚሰግድላት ቀርቶ አንዳችም የተለዩ ግምት የሚሰጣት ሰው
አላገኘችም ። በንጣትዋ ፣ በአለባበስዋም እንደ ጉድ አይተዋት ፣ ተቀላል
ደው ፣ ተሣሥቱው ፣ ገልመጥ ገልመጥ ብለው ተመልክተው ያልፉዋታል።
መጀመሪያ ላይ ፣ ምናልባት ቀደም ሲል በረቦችንና ቱርኮችን በማየታቸው
በቆዳ ፍካት አንድ መስያቸው ቢሆን ነው ስትል ራስዋን አጽናናች ።
ከየት አገር እንደ መጣች ፣ ግን እንደሆነች ፣ ለምን ከፍተኛ ተግባር እንደ
መጣች ቀደም ሲል ከሚስዮናች ጋር ቆይተው አንዳንድ የእንግሊዝኛ
ቃላት በሚሞክሩ አስተርጓሚዎች አማካይነት ማስረዳት ጀመረች ።
አላስደነቃቸውም ። ከሩቅ አገር የመጣች ፣ ላገሩ እንግዳ ፣ ለሰዉ ባዳ
በመሆንዋ ያዘኑላት ይመስል ብቻ ከንፈራቸውን ይመጡላታል ። ከራሳቸው
ዝቅ አድርገውም ባይሆን ከራሳቸው ቅንጣት ያህል ከፍ አድርገው እንደ
ማይመለከቱዋት ሲታወታት ትበሽቃለች ። ትበግናለች ። ግን ሕልሟ
ሁሉ እንደ ጉም በንኖ መቅጀቱን መቀበል ስለማትፈልግ ምርጥ ቀሚሷን
ከነመደረቢያ ካባው ትለብስና ፣ እንደ ምኞትዋ ልዕልት ፣ ቁጥ ፣ ጅንን ፣
ኮስተር ብላ መሔድ ስትጀምር ፣ ጉምጉምታው ፣ ሣቅን ለማፈን ይመስል
አፍን በመዳፍ መክደኑ ይበዛል ።

በንዴት ምክንያቷን ትጠይቃለች ። “ ምን ነክት ሲትዋዋ ፣ የሙተሜ
ልጅ መጣለች እንዴ እንደዚህ የደረቀቸው ፣ ” ብለው እንደሚቀልዱ
ይነግራታል ፣ እርር ትላለች ።

ተሰፋ ባለመቁረጥ የምትፈልገውን ከበሬታ ለማግኘት ስትል ወደ
ሌላው ሚፍ አቀራረብ ትሔዳለች ። መናኛ ለብሳ ፣ ራስዋን ሸፍና ጉንበሰ
ብላ አንገቷን በመድፋት ፣ የጥቁር ሕዝብ ነፍስ ለማዳን ሕይወትዋንና
የድሎት ኑሮዋን የሠዋች ለመምሰል ትሞክራለች ። ውጤቱ ካሰበችው
የተገላቢጦሽ ይሆንባታል ። ‘ እረ ይች የውሎ አገር እንግዳ እንጀትዋ
ታተፎ ልትወድቅ ምንም አልቀራት ! ’ ከጥራጥሬ እስከ ሙክት ድረስ
ምግብና መጠጥ ይላክላቸዋል ። ከዚያኛው ያላነሰ ያናድዳታል ።

‘ ያደቦች ፣ ምንም የማይገባችሁ ፍጹም ያደቦች ’ ትላለች ፣ ከራ
ስዋ ጋር ። ከመብሸቅዋ የተነሣ ፣ እርሷ የሚሰማትን የበላይነት ሊረዱት
አለመቻላቸውን ከድንቁርና ዐልፎ እንደ ወንጀልም ልትቈጥረው ይቃጣ
ታል ። ሌላው ቀርቶ ፣ ብዙ ጊዜ አብራቸው በመገኘት እንዲከተሉዋትና
እንዲያጅቡዋት የምትፈልገው ፣ በክርስቲያኖች ዘንድ ዝቅ ተብለው የሚ
ታዩት ፈላሾች እንኳ የተለየ አክብሮት አያደርጉላትም ። ልታስተምራ
ቸው ፣ ልታሰሪዳቸው የምትፈልገውን ነገር በትሕትናና በጥሞና አዳም
ጠው ፣ ዐልፎ ዐልፎም ፈገግታ እያሳዩ ያለ አንዳች መርበደበድ ወደ
የግል ሥራቸው ይበተናሉ ። የፈረንጁን ጥልፍ ሥራ ስታሳያቸው በበኩ
ላቸው ፈትል ይዘውላት ያቀርባሉ — ሊያሳዩዋት ፣ ሊያስተምሩዋት ።
ሹራብ ሥራ አሳይታቸው ስትጨርስ እየመሩ ወደ ሙንደሩ ሽማኔ ይወስ
ዱዋታል ፣ እኛም እሰን የማለት ዐይነት ። ከእርስዋ ችሎታ ጋር ውድድር
መያዛቸው ያበግናታል ።

በዚህ ሁሉ የመንፈስና የስሜት ቁስለት ላይ ፣ ሮዜንታል ከባልዋ ጋር
ያላት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አስደሳችና እርክ አልነበረም ።

ሚስተር ሮዜንታል ፣ ዱሮውንም ከተፈጥሮው ደመ ሞቃት አፍቃሪ
አልነበረም ። ለአንድ ሚስት የሚሆን ኃይል ባያጣም ፣ ጉንፋን የሚያዘ
ወትረው ፣ ብዙ ጊዜ ስለሆድ ሕመሙ የሚያወራ ፣ አካሉ ኮሰስ ያለ ሰው
ነው ። ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ ወዲህ ደግሞ ሐሳቡና ስሜቱ ፣ በሙንፈሳዊና
በፖለቲካዊ ተልዕኮው ላይ ስለ ተጠመደ ፣ ከሚስቱ ጋር ለፍቅር የሚሰ
ጠው ጊዜ እያነሰና እየተራራቀ ሔደ ። የተፈጥሮ ፍላጎት ጨርሶ አይጠፋ
ምና ዐልፎ ዐልፎ እርሱ ሲያሰኘው ፣ ደግሞ እንዳጋጣሚ ሚስስ ሮዜንታል
ተበሳጭታ ፣ ተብሰክስካ የዋለችበት ጊዜ ይሆናል ። በመደሰትና በግስ
ደስት ፈንታ ፣ ሌላ ብሽቀቷን እርሱን በማመናጨቅ ትወጣዋለች ። ደግ
ነቱ ስሜቱን የሚገታ ሰው ስለሆነ እስከዚህም አይማረርም ። ችግሩ እርሷ
ባሰኛት ጊዜ ደግሞ እርሱ ደክሞታል ፣ ሌላ ሐሳብ ይዞታል ፣ ወይም የሆድ
ሕመሙ ተነሥቶበታል ። እንደ ተታጠለች ታድራለች ። በዚህ ዐይነት
በሐሳብዋና በስሜቷ ውስጥ አንዳንድ ነገር መምጣቱ የማይቀር ነበር ።

ከአንድ መንገድ ወይም ከሌላ ትደርሳለች። ጉልማሶች፣ ልብሳቸውን እጥበው እስኪተው እየተጫወቱ ገላቸውን ቢታጠቡ ታሻሽለች። ከሌት ሆነ ጉመልከታለች — ከውሃው ጋር እንደ ዓሣ የሚያንሸራርት ወይም ቆሳ፣ በብርሃን ፍርግም ያለ ገላ። ሲደፋፈሩ፣ ወተ ሲራጩ ወይም ሲደርቁ ሰው ይያችው እይያችው ገደ ያሳችው አይመስልም። በነሳችው አያፍሩ በጉም። ከፍ ብለው ወተ ከሚቀዱት፣ ገት ብለው እንደሀሁ ሰብል ከሚ ያተቡት ሴቶች ጋር በንካ እይተፋፈሩም። እንዲያውም በራቁ እየተወራሩ ይቀሳቀሳሉ። ርዜንታል መቀሳቀል ያበሻታል። ያ ወይም የሚያፋረቅርት የጉልማሳ ገላ፣ ከርስዋ ንጭ ገላ ጋር ሲመጋጋ እንደ እይባ ጎበር ተሰም ውበት በተቱ ቢሰሳሰዋም ይታያታል። ከንፈርዋን እየነከሩ ፈገፋ ሲረጅም ገጽ ትቱግሰዋል።

ወይም ደግም በውርግ፣ በድግስ፣ እንደ መዕቀልና ጥምቀት በመሳ ሰስት ቀመት በዓሳት ላይ ትንሸልች። ይፈኑ እንደ ግዕይል የመርጓል፣ እስ ከጪታውና ጭፋርው ይቀልጣል። ሙሀሪትና በጉልማሶች መካከል፣ መጣጣቂ፣ መጨቀቅ፣ መጨራመሙ፣ መሳረቱ፣ በእይባና በቁመግ በቀልድ መመታታቱ ይሰባታል። አውርፓ ላለች እንደ ሰማችውና እንደ ገመተችው ከከብቶች ሥራ የማይሻል የአረመኔዎች ናካል ሥጋ እስኔ ደም አይደለም። ወግና ባሕል፣ ፍቅርና መተሳሰብ ያለበት የሕይወት ውበት ነው። የሕይወት ማዕም፣ የሕይወት ጀጋ ነው። በዚህ የሕይወት መ በት ውስጥ እርያም ተካፋይ መሆን ያስቸታል። ውነቱው እየቀመሰና እየደጋገመ ሲሔድ፣ በመጨረሻ ራስዋን መግታት እስኪያቅታት በእል ምርዋ ውስጥ ቅሠት መሰል ልዩ ልዩ ትርጓት እየፈጠረ ያብውሰጣታል።

መበከሪም ወር የእንተጀያ ያጋውንና ወያና ያጋውን ያዘ ተፈጥ ርንና በጪ፣ ፈነ የሚሰበት ጊዜ ነው። እንደ መልሀም የተተ ቁልል ገላመታ ሴት እንደ ቀለቸበት ገደኛ ተተ መሰሎ ከሚገመሰወበ ጻመና በሰተቀር ሰማዩ ገልጧል። ዕልር ዕልር ዝናም ይተጓል። ብርቱ ዝናም ሊሆን ያች ላል። ግን የመበከሪም ዝናም ግንም እያመሰወም። ግንም እያማርሪውም። እሠመሪ እፈሩት መዲያው ሰላ ሰለሆነ። እንሳያውም ልጆች ከዚች እየወጡ በሩገደት ያተባሰትል። መሪቱ፣ በእጀት እሠመሪ፣ በእሰባና በለመሰመ ዕፅዋት ፈነቷል። መገው፣ ምንጩ፣ እያመሪ መልድ ይጀል። የሰውም ሊት ከተፈጥር ጋር እብር ፈነቷል። የንውዳ ንውት ዕሰት፣ ' የንውን ምንጮት ውጣ፣ የንገር ምንቸት ግሳ ' ተብሎ እንደ ተሠፈረሪው ውስ፣ ልጆም በዋቂውም በእጀት ምንብ መዋዜቷል። ሥሪ በጣም የማያሰባበት፣ የመመገኖ ጊዜ ነው። የእረም ሥሪ በእውሳኖው እብትቷል። ከተቂቱ በሰተቀር እሠሪውም ሃና እልደረሰም፣ እብሳኖው ሥሪ በልጆች የማከናወን ሰብልን ከሌሎችና ከአሪዊት መሰጠት ነው።

በእንተጀያ፣ መበከሪም፣ የውበት፣ የተስፋና የደስታ ወር ነው። ለደግስ የሚሆነው ሰብል ገና ተሰብበበ ሰለልገባ፣ በመበከሪም ወር

ውው መርግ ባይጸረገም የቅሪል የልገስና የመስተል ደግስ እስ። ከልሎች ወራት በመበከሪም ወርስት ብሎ የሚታይ ሌላም የደስታ ምንገያት አለ። ቂጥሎም ወር ጀምር አጀመሬ ተሰብስቦ እየገባ በሥሬ ለገታ የፍቅር ጨዋታ ስሚጀመር፣ በጥር ወር መርግ ስለሚወጣ ደውን በሰለ ምሥል ሊኖ የሚገኙት ከልሎች ወራት ይልት በመበከሪም የሚወጸሩት ሕዋናት በርክት ይሰው። የማርፈሻው ደግስና የዐራስ ጥረው በጪታው መወን በመ በከሪም ወር ተረናረፍ ይሳል። ከዚህ ከሌሎናት ልደት ጋር ተያይዞ በተ ለይ በሌላንች ይንደ በመበከሪም ወር የሚወዛ ሰለ በዓል አስ — የማዜረት በዓል።

ግዜረት በሌላንች ዘንድ፣ እንደ ክርስትና ውስ ደግስና መገሌሳዊ ሥን ሥርዓት የያዘ ባሕል በመሆኑ፣ እያንዳንዱ ቤተሰብና መንደሩ ሥርዓቱን ስሚት ያከብረዋል፣ ይሌደመዋል። እነሚከተር እስተ ርነ ወር ክርስትና የመሰጠዋቸው ሌላንች በንኳ ደህንን ባሕል ሊተዉት አልቻለም። በዕለት ቀን መገሠር ሕጽንን አደነኛ ቁስል ሊያመጣበት የሚችል ከመሆኑ በላር፣ በክርስትና የደግናት እንደግግደሌልግ ሲንገሩ ቀየው፣ "ሥጋዎ አዝ የማንቱ ክርስቲያንና ችስ ይገገሩ የስ!" የሚል መልስ ያሰማሉ። ሚስተናች አሰምነው ግስቀረት እንደማይችሉ ሲገ ጩ፣ የማዜረት ሰዓላቸውን እንዳሳዛቸው እንዲሳተስ ተሠቁዋቸው። እንዲያ ውም ከሚጨ በኋላ ወደ ክርስትና ከመ ሰጡዋቸው የሌላንች በተሰብ የማዜረት በማል ሊሥ ሌላቸው እየተመሩ ይገኙ ጀመር። ሚስጢ ርዜንታል፣ ሰመ ጀመ ሪያ ጊዜ ከአንተጀያዊ ወገን ጋር የተሰናንችውም በእንደዚህ ያለ የማዜ ረት በማል ላይ ነበረ።

ደሰኛ ተርተው እርጂ ብቻቸን የተገገኙበት ምክንያት እውን በትክክል ትሠ እደሳትም። የሰመተውንም ርም ረሰታቸለች። ሌላውን ውናቱ ግን በሚገባ ታሪታ ውሰዋለች።

የማዜረቱ ሥርዓት ተሌጽሞ፣ ድግሱ ተበልቶና ተመግቶ፣ ጊዜው መጀቅረት ሩቅ እብኖው ተጋባዥ እየመሪት ከሌጂ በጋል፣ በጣም ቀሪል የሆኑት ሲቶች ብቻ ቀሩ። እነሱም ምግቱ ስዐይን ያህ ሲያደርግ እረቂን ደጋግሰው ያዘው ወደ ሴሰው ትንሽ ጉጀ ሌጂ። ግብር ወዛ። ውጫ ጊዜ ነው። ሌሰኞች የሰጡት ተግባራችውን ከመጭ በኃር ቢፈጽሙም፣ እር ጅን የሚያለሌጂ ሰዚው ተሰሰ በተዘጋጀችው ጎጆ ውስጥ ነው። በዚያም ሲያውሩና ምንገም ምንገም ሲያደርጉ፣ ሪዘም ላለ ጊዜ እንደሚቆዩ ርዜ ንታል ታውቃሰች። ያን ጊዜ ተሰናብታ መ ሌጂ ትችል ነበር። ግን ከመ ጠቅታና ከወርጋሚው የከሚት ውጀት ጋር፣ የሚከቡን መሬር ቅርብ ስለሆነ ያን ጊዜም የሚሥጋን ነገር የለም በማል ሰበብ ተቀምጫ ቀረች፣ ከልጄ አባት ጋር በጉጀው ውስጥ ብቻችውን።

ከውጭ በመሰ ሠሬት የተገማሰለው ብርያን ገርበብ ባለው በር በኩል ለፈ እረት ግዕዘን ፈጥር በመገኘት ከመጀ። ብሬትና ከም ደጀው

እሳት ጋር ተቀላቅሎ የፈጠረው አጠቃላይ ጎብረ ብርሃን በአውሮፓ የቲያትር መድረክ ላይ እንዳየችው ምሥጢራዊ የሚመስልና በምሥጢራዊ ነቱም የሚስብ እንዳች ዐይነት ትርዒት አስፍኗል ። የልጁ አባት እንደ ባለቤትነቱ በድግሱ ላይ አቀመማው ከበሩ ትይዩ ስለሆነና ጢፎችም በዚ ያው አካባቢ ስለ ተቀመጡ ፣ አጠቃላዩ ብርሃን እንደ ድባብ ከብ ሠርቶ ዐር ፎበታል ። ከበሩ ጥቂት ፈቀቅ ብላ የተቀመጠችው ሚስስ ሮዜንታል ሁለ ም ከወጡ በኋላ ፣ ዐይንዋ በዚያ ድባብ ውስጥ ተተክሎ ቆየ ። የሕፃኑ አባት ግድግዳውን እንደ ተደገፈ ቋንጃውን ወደፊት ዘርግቶ ተቀምጧል ። ዐልፎ ዐልፎ ዐይኑን ወደ ሚስስ ሮዜንታል ጣል ከማድረግ በስተቀር አብዛኛውን ጊዜ ዝም ብሎ ወደ በሩ ነበር የሚመለከተው ። ግን በተለይ እንዳች የተወሰነ ነገር የሚያይ ደግሞ እይመስልም ። 'ምናልባት በሐሳብ ነው የሚያየው ። ምን እያሰበ ነው ? ምን እየጠበቀ ነው ? ወይስ የሚጠብቀውን እያሰበ!' ስትል ሚስስ ሮዜንታል በሐሳብዋ ጠየቀች ። 'እየጠበቀ መሆን አለበት' አለች ፣ እሁንም ደግማ በሐሳብዋ ። በፈላሾች ባህል መሠረት ሴት ነፍሰ ጡር ከሆነች ፣ ወይም አደፍ ስትሆን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነውርና ክልክል መሆኑን ታውቃለች ። ከወለደች በኋላም የግዝረቱ ሥነ ሥርዓት እስኪፈጸምና እናቲቱም ለተወሰነ ቀን እስክትጸዳ ድረስ እንደዚሁ ነው ። ዛሬ ይሆናል እንግዲህ የመጀመሪያ ቀናቸው የሚል ሐሳብ መጠባትና ልብዋ በኃይል ይመታ ጀመር ። በጣም የተራበ መሆን አለበት ። ቀን ፣ እጀ ጠባቡንና ሱሪውን ጠቅለል ጠቅለል አድርጎ ጠቡቱን ሲያርድ ያየችው ፈርጠምጠም ያለ አካሉ በአእምሮዋ መጣ ። ገና ሁለት የወለደ ጉልማሳ ነው ። እስከዚህ መልክ መልካም እይደለም ። ግን አሁን ለሚስስ ሮዜንታል የሚታያት መልኩ አልነበረም ። ረጅም ጊዜውንስ ። (ምን ያህል ተርቦ ይሆን ?) የደረት አጥንቷን የሚሰብር እስኪ መስል ድረስ ልብዋ እየደለቀ ሳይታወቃት እንደ ደመ ነፍስ ተነሥታ ከጉኑ ተቀመጠች ።

"አባት መሆን እንዴት ነው ? " አለችው የምትናገረው ጠፍቷት ፣ ከራሰዋ የወጣ በማይመስል ድምፅ ።

"እህ ?" ሲል መልሶ ጠየቃት ፣ ጥያቄዋ እያናገሮት ። ግን ከሁናቴዋና ቀደም ሲል ከተገነዘበው እመለካከቷ፣ እዝግሚያዋ ተሰምቶታል ። ስሜቷ ወደ እሱም መጋባቱ የማይቀር ነበር ።

"ማለቴ - ማለቴ" ቃላቱም ድምፅዋም ጠፋባት ።

"እህ ? " ቋንጃውን እንደ መሰብሰብ አደረገ ።

ሊንጣ የፈለገ በማስመሰል ፣ "የለም - የለም ቁጭ በል" ስትል እጁ ዋን ከጭኑ ላይ ጣል አደረገች ።

ሲፈንዳ ደርሶ ነበር ።

ሴቶቹ ሲመለሱ ያገኙዋቸው በዚያው ሥፍራ ላይ በሌላ ዓለም ውስጥ እንደ ሆኑ ነበር ። ደግነቱ ጸጉር መናጨት ቀርቶ እምብዛም ግር ግር አልተነሣም ። በምንተፍረት ቱሚዩን እያስተካከለች ከቤት ስት ወጣ በመገረምና በትዝብት ብቻ ተመለከቷት ።

ለወንዶቹ ሚስዮናውያን ይነግሩበኛል ፣ ወይም ባልና ሚስቱ ይፋ ቱና ጉዳዩ ይፋ ይወጣል በማለት ሰሞኑን ጥቂት ሥጋት እድሮባት ነበር። ግን ምንም ነገር አልደረሰም ። ባልዋና ሚስተር እስተርን ወይም ሌሎች ሚስዮናውያን ምናልባት ነገሩን ሰምተውም ቢሆን ያልሰሙ ነበር የመ ለሱት ። እሷም ቢሆን በሆነው ነገር አልተቆጨችበትም ። ለእሮር ጊዜም ቢሆን ይህ ነው ወደማይባል የደስታ ዓለም ደርሳ ተመልሳበታ ለች ። ታዲያ ይኸ ምን ያስቆጫል ? እንዲያውም ፣ ከዚያው የሕፃን አባት ጉልማሳ ጋር እንዳለፈው ጊዜ እጅ ተናንጅ እንዳይያዙ ጠንቀቅ ባለ መን ገድ ብትደጋግመው አትጠላም ነበር ። ለክፋቱ ሆን ብሎ የሚሸሻት ይመ ስል ድጋሚ ዕድል አላጋጥማት አለ ። አዳዲስ ዕድል ግን እየቆየ መጣላት።

ስለ እርዷ ሲወራ ወይም ስትታማ አልሰማችም ። ግን ወንዶች ስለ እርዷ ያላቸው አመለካከት አዲስ ዐይነት መሆኑ ግልጽ ነበር ። ዐይ ናቸውን የሚተክሉባት ፣ በማባበል ፣ በፈገግታ ፣ በግምገማ መልክ ሆነ ። ብዙ ጊዜም አስተያየታቸው በጥቅሻ የታጀበ ነበር ። እንደዚሁም ፣ ብቻ ዋን በሆነችበት ሥፍራ ብቸኛ ወንድ እያዘወተረ ያጋጥማት ጀመር ። እድፍ የሚጠባበቃት ይመስል ፣ ድንገት ብቅ ብሎ ፈገግታ የተመላበት ሰላምታ ያቀርብላታል ። ጭውውት ይቀጥላል ። ፍላጐቱ ከውናቴው ያስታውቃል ። ሚስስ ሮዜንታል ይህንን ሁሉ ወደደችው እንጂ አልጠ ላችውም ። እንዳፈረሰ ዲያቆን ፣ ዐይነ ጥላዋ ድንገት እንደ ተገፈፈላት ኮረዳ ፣ እንዴ የጀመረችውን ቀጠለችበት ።

ይህ ሁሉ የተወሰነ ወሲባዊ ርካታ ሰጣት ። ሌላው ምኞቷ ግን እንደ ተንሳፈፈ የማይጨበጥ ጻመና እንደሆነ ቀረባት። 'ንግሥት ባትሆን ፣ ልዕል ትም ባትሆን ፣' በቤተ መንግሥት አካባቢ ከሚታዩት ወይዛዝርት ልቃ ፣ ደምቃ መከበር ትፈልጋለች ። አገርዋ ስትመለስ ምን ትተርካለች ? ከአንድ ገበሬ ጉልማሳ ጋር በፍትር ተገናኝው ብላ ! መኳንንቱ ፣ ወሬ ዋን ሰምተው ንቀዋትም ይሁን ጠጉረ ልውጥ እልፍኝ የማስገባቱን ሐሜት ፈርተውት ፍላጎታቸውን በግልጽ አያሳዩም ። የራሳቸውን አገር ሴት ሲፈልጉ ጉተት ጉንተል ያደርጋሉ ። ከእርዷ ላይ ግን ከተልድና ከፈገ ግታ ፣ እንዲያም ሲል ሌላ በማያይበት ጊዜ ከተቅሻ አያልፍም ። ሮዜን ታል ከፈለገችና ከልብ ካሰበችበት ፣ ደመቅ ያለ ግብግ ተደርጎ ብዙው መኳንንት ፣ ከሞቅታ ዐልፎ ጥንብዝ በሚልበት ጊዜ እንደ መጀመሪያዉ ፈላቫ ስሜቱ የሚያሸንፈው መኮንን እንደማታጣ አሳምራ ታውቃ ዋለች ። ውጪቲስ ? ለወሲብ ርካታ የሚፈጸም አንድ ነገር ነው ። ለሌላ ዓላማ የሚሆን ደግሞ ሌላ ነው ። እንዲያውም ከተራው ሰው ጋር መነ

ካካቷ ፣ በመኳንንቱ ዘንድ እንዳች ወይነት የባሕል ልዝም እንዳደረገባቸው ሁሉ ፣ ከመኳንንቱ ጋር መነካካቷ ደግሞ ፣ ትልቁን ምኞቷን ሊዘጥ ፣ ስባት እንደሚችል ይሰማታል ። አትፈልግም ።

ሮዜንታል ፡ አባ ታጠቅ ስለሚባል ጀግና የሰማችው ገና ተዋበችን ይዞ በቋራ እንደ ሸፈተ ነበር ። ታሪኩ ራሱ ፣ በእንግሊዝ ልብ ወለዶች መጻሕፍት ያነበበችው ወይነት ሆኖ ተሰማት ። ደሃው ጀግና ፣ ልዕልቷን ከቤተ መንግሥት መንጥቆ ወሰዳት ። ልዕልቲቷም በጀግንነቱ ትወደው ነበርና ደስ አላት ። ከዚያም በእንግሊዝ ልብ ወለድ ታሪክ እንዳነበበችው ፣ ''ሮቢን ሁድ'' እገሬው ገበሬው ወደደው ። ሮዜንታል ስለ አባ ታጠቅ ካሣ አስደናቂ ጀብዱ ከዚያም ከዚያም ስትሰማ ፣ ያደረባት አስተሳሰብ ጥንት ያለመችውን ልዑል ብቻ ሳይሆን ፣ ከልዑል ጋር የጀግና ፍቅር አብሮ የሚሰጣትን ስሜት ነበር ። ከዚያም ሥልጣን ይዘው ጉንደር ላይ የመገናኘት ዕድል አጋጠማት ።

ሚስስ ሮዜንታል ፣ ከሌሎቹ የውጭ አገር ሰዎች ጋር በእልፍኝ አስከ ልካይ ጉንደር ቤተ መንግሥት ገብታ ቴዎድሮስን በቅርብ ከተዋወቀችበት ጊዜ አንሥታ ያላት አመለካከትና ስሜት ፣ ልትለየውና ልትገልጸው የማትችል ዝብርቅርትና ውስብስብ ወይነት ሆነባት ። የምታደንቃቸውን ያህል ትፈራቸዋለች ። ፈጣሚታቸው የሚያስደስታትን ፣ የሚማርካትን ያህል እዚያው በዚያው መልሶ ያናድዳታል ። ይህ ንዴትም ፣ ጥላቻ ወይም በቀል ወደሚመስላት ስሜት ሊቃረብ ይቃጣዋል ። ቴዎድሮስን በሚመለከት ረገድ ፣ እርሷን በቀጥታ የማይነካ በሚመስል ጉዳይ ስንኳ ስሜቷ ይነካል ። ይለዋወጣል ። ስለ ቴዎድሮስ ያላትን የሕሳብ ሕልም ፣ በእንቅልፍ ሕልሟ የናረችበት ጊዜ አለ ። በእውን ግን አል ሆነም ። ዘወትር የምትሰማው ስለ ቴዎድሮስና ስለ ተዋበች የማይታመን ፍቅር ነው ፣ በልብ ወለድ መጽሐፍ እንዳነበበችው ወይነት ። ከዚያም ቆይታ ቆይታ ስለመቁረባቸው ተነገራት ። ምንድን ነው የጋብቻ ቁርባን ? ከባልና ሚስቱ እንዳቸው በሞት ካልተለዩ በስተቀር ፣ ከሥስተኛ ሰው ጋር የፍቅር ግንኙነት የማያደርጉበት ታል ኪዳን መሆኑን ሲያስረዷት ማመን አቃታት ። የሮማ ካቶሊኮች ምንኩስና ይገባታል ። አፍሪካ ውስጥ በጥቁር ሕዝቦች መካከል ሊኖርና ሊፈጸም መቻሉን ማመን ግን አቃታት ። ልታምነው ብትችልም እበሽታት ፣ አናደጻት ። ከእንግዲህ ስለ ቴዎድሮስ እንዳችም ስሜትና ዓላማ ሊኖራት አይችልም ። ነገር ግን የምኞቱኛ ሕይወት እስካለ ድረስ ምኞት አይሞትም ። ስሜትና ልብ እስካለ ድረስም ስሜት አይሞትም ። ሮዜንታል ሁለቱም ነበራት ፣ ኢት እስካለ ድረስም ስሜት አይሞትም ። ሮዜንታል ሁለቱም ነበራት ፣ ኢት ዮጵያ ውስጥ እስከ ቆየች ድረስ በተስፋ የሚያናፍት ። በመካከሉ ግን ሁለቱንም የሚያጠፋ የሚስተር እስተርን ሙሳኔ መጣ ።

ከመሠረቱ የሚስተር እስተርን ሙሳኔ ብቻ አይደለም ። የቴዎድሮስም ጭምር ነው ።

